«የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች የተፈጠረውን ችግር በመቀራረብ እንጂ በመለያየት አይፈቱትም»

- ዶክተር ዳባ ጩፋ
የሕግ አማካሪና ጠበቃ



ገጽ 6

የፕላኔታችንን የጤና ጠንቅ

ገጽ 8


# አዲስ ዘመን

እፕድ

81ኛ ዓመት ቁጥር 288 ሰኔ 18 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!






## ‹‹የመንግሥት አካላት ለጥቃት የተጋለጡ ወገኖችን በመለየት ደህንነታቸውን ሊያስጠብቁ ይገባል››

-ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ
የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ምክትል ዋና ዳይሬክተርና
የኢሶዴፖ ሊቀመንበር

ዘላለም ግዛው



አዲስ አበባ፡- በየደረጃው የሚገኙ የመንግስት አካላት በተለያዩ አካባቢዎች ለጥቃት የተጋለጡ ወገኖችን በመለየት ደህንነታቸውን ሊያስጠብቁና ጥቃት እንዳይደርስባቸው ሊከላከሉላቸው እንደሚገባ የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ምክትል ዋና ዳይሬክተርና የኢትዮጵያ ሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲ (ኢሶዴፖ) ሊቀመንበር ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ አሳሰቡ፡፡

ፕሮፌሰር በየነ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ «ብሶትና ብሽቀቱን ለመተንፈስ ያህል እንጂ በማውገዝ መፍትሄ አይገኝም፡፡ የዚህን ችግር ምንጭ በመገንዘብ መንግስት ልዩ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል» ሰሞኑን በወለጋ በንጹሃን ዜጎች ላይ የደረሰው አይነት ጥቃት እንዳይደርስ ለመንግስት አካላት ምክር ስለግስ ቆይቻለሁ ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ጥቃት ሊደርስ የሚችልባቸውን አካባቢዎች ለይቶ ትኩረት መስጠት እንደሚገባ፤ ሊጠቃ የሚችል ማህበረሰብ ስላለ ልዩ ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው ወገኖች ደህንነት መጠበቅ እንደሚያስፈልግም ነው የተናገሩት፡፡

በንጹሃን ዜጎች ላይ የሚደርሰውን ግድያና ጥቃት ማውገዝ ብቻውን አይበቃም፣ ውግዘት ማንንም አያስፈራም፣ ድርጊቱም በውግዘት ብቻ የሚመለስ አይደለም፡፡ ድርጊት ፈጻሚዎቹ ሃይማኖት ኖሯቸው እንዳይኮነኑ የሚፈሩ የሞራል ከፍታ ያላቸው አይነት አይደሉምና ሲሉም ነው የገለጹት፡፡

‹‹የመንግሥት አካላት… ወደ ገጽ 4 ዞሯል







## “በገዳ ሥርዓት ወንድምን መግደል አስጸያፊና የሚወገዝ ተግባር ነው”

-አባ ገዳዎች



ጉጅ አባ ገዳ ጂሎ መንደሆ



የመጫ አባ ገዳ ወርቅነህ ተሬሳ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- በገዳ ሥርዓት መሰረት ወንድም ወንድሙን መግደል አጸያፊ በመሆኑ ወንድሙን የገደለ ሰው ከጎሳው ተለይቶ ሰባት ወንዝ ተሻግሮ እንዲኖር እንደሚደረግ አባ ገዳዎች አስታወቁ፡፡ በቅርቡ በምዕራብ ወለጋ በዜጎች ላይ የደረሰውን ግድያም አውግዘዋል፡፡

የአባ ገዳዎች ጥምረት አባል እና የመጫ አባ ገዳ ወርቅነህ ተሬሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በገዳ ሥርዓት ወንድም ወንድሙን መግደል አጸያፊ ድርጊት ነው፡፡

በኦሮሞ ባህል እርስ በእርስ መታኮስ ከገዳ እሴቶች ጋር የሚጣረስ መሆኑን የገለጹት አባ ገዳ ወርቅነህ፤ በገዳ ስርዓት መሰረት ወንድሙን የገደለ ሰው ከጎሳው ተለይቶ ሰባት ወንዝ ተሻግሮ እንዲኖር ይደረጋል ብለዋል፡፡ በስርዓቱ መሰረት የማስታረቅ ስራዎች ካልተሰሩ በስተቀር ጉዳይ ወደ ኅብረተሰቡ እንደማይቀላቀልም ገልጸዋል፡፡

… ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ ኦባንግ ሜቶ

### ለተፈጸሙ ሰብዓዊ ጥቃቶች ፍትህ መስጠት፣ መሰል ጥቃቶችም እንዳይደገሙ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል

ገጽ 4




ገጽ 9

### የአገር ጉዶች፤ የንጹሐን ደም ባለ እዳዎች

# የአዛውንቷን ስቃይ ያቃለለው የበጎ ፈቃድ አገልግሎት

**ዳግማዊት ግርማ**

ወ/ሮ አረጋሽ መርጊያ ይባላሉ፤ በጠይም ፊታቸው ላይ ለዕድሜያቸው መግፋት ምልክት የሆነው ሽበት ሺህ ውበት ሆኗቸዋል። ማንኛውም ልጅ እናቴ እያለ ሊጠራቸው የሚያስችል በእድሜ የተረጨት የእናትነት ፀበል ሞገስ ሰጥቷቸዋል። ኑሯቸው የሞላ ባይሆንም በሀዘኔታና በየዋህነት የተሞላ ፊት አላቸው።

የኑሮ ፈርጣማ በትር ቢያርፍባቸውም በተመስገንና በያልፋል ተስፋ በዚህች ምድር ላይ ሃያ ሰባት ሺህ ሁለት መቶ ቀንና ሌሊቶችን (80 ዓመታትን) አሳልፈዋል። ለምለሙ ማህጸናቸውም አስራ አንድ ልጆች ፈርቶበታል።

ስምንት ልጆችና ሁለት ባሎች በሞት ሲነጠቁ ምንም ማድረግ ያልቻለችው ህይወት ደመኛቸው ናት። ህይወት የምትባል ነገር ፍትሀዊ ልትሆንላቸው አልቻለችምና በእርሳቸው መዝገበ ቃላት ላይ ፍርደ ገምድል የሚል ስያሜ ተለግሷታል።

ባንዷ ቀጭን የህይወት መስመራቸው ላይ ብዙዎች መጥተው ሄደዋል፤ በደሳሳ ጎጃቸው ውስጥ እልፍ ደስታና ሀዘን ተፈራርቋል፤ ስምንት ከማህፀናቸው የወጡ የስጋቸው ቁራጭ የአጥንታቸው ፍላጭ የሆኑ ልጆቻቸውን ብቻ ሳይሆን አቶ አሸናፊ ተፈራና አማረ ለማ ወርቅ የተባሉ በተለያየ ጊዜ ያገቧቸው ሁለት ባሎቻቸውንም በማይቀረው ሞት አጥተዋል።

አዲስ አበባ ሾላ ገበያ ተብሎ በሚጠራው ስፍራ ተወልደው እዛው አርጅተዋል። በዚሁ ሰፈር ተሞሽረው አግብተዋል፤ ፍቅርን ከድህነት አይተውበታል። ስምንት ልጆቻቸውንም በእዚሁ አካባቢ ቀብረዋል። የረጅም ዓመት ባለቤታቸውንና የእርሳቸውን ሀዘን ቢያስረሳኝ ብለው ያገቧቸው ሌላኛው ባለቤታቸውንም ያጡት እዚሁ ነው።

ወጣት ሳሉ ወጣትነት በለገሳቸው ጉልበታቸው ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን በህይወት ለማቆየት በየሰው ቤት በሰራተኝነት ተቀጥረው ሰርተዋል። እስከ አሁኑ እድሜያቸው ድረስም ጠላ እየጠመቁ አረቄ እያወጡ የህይወትን ቋጠሮ ሲፈቱ ከርመዋል።

ከተደራረበው ችግራቸው በላይ የገፋው እድሜያቸውን ታኮ የመጣባቸው በሽታ የገፋ ቀናቸውን አከፍቶባቸዋል። የኩላሊት ሳምባና ጨጓራ በሽታቸው እህህ እያስባለ እያስቃተታቸው ነው።

በዚህ ሁሉ ተደራራቢ ችግር በበረታ መከራ ውስጥ ሆነው ህይወት ቢከብዳቸውም ሰው እየኖረ እንዳለው



ወ/ሮ አረጋሽ መርጊያ

እኔም እንዳመጣጡ እየኖርኩ እገኛለሁ ይላሉ። አሁን በወር ከሚያገኟት የጡረታ ስድስት መቶ ብር ውጪ ጧሪ ልጅ የላቸውም። በዚህ ከባድ ጊዜ ላይ ነው መንግስት በክረምት በጎ አድራጎት ተግባራቱ ቤታቸውን አድሶ ያስረከባቸው።

አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን በጎ ፈቃደኞችን በተዘጋጁ ፕሮግራሞች በማሳተፍ የሚከወነው የክረምት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት 570 ሺህ የከተማዋን ነዋሪዎች ተጠቃሚ የሚያደርጉ የበጎ ፈቃድ ስራዎች ማከናወን የሚያስችል ግብ ቀርፆ ተፍ ተፍ ካለ ወራት ተቆጥረዋል።

ለመርሀ ግብሩ ስኬታማነት ሁሉም ባለድርሻ አካል እንዲሁም በጎፈቃደኞች፣ ባለሐብቶች፣ የሙያ ማህበራትና የመንግስት ሰራተኞች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ ሲቪክ ማህበራት እና ሌሎች ለበጎነት የሚሰሩ አካላት ለዚህ እቅድ ተግባራዊነት የእርዳታ እጆቻቸውን እንዲዘረጉ በሚጠበቅባቸው በዚህ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ብዙዎች እልፍ ችግሮቻቸውን አልፈውባቸዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፍቃድ ኮሚሽኑ አማካኝነት ሁለት ቢሊዮን ብር በላይ የሚገመት ገንዘብን የመንግስት ወጪን ለመታደግ በሰራው እንቅስቃሴው ከሶስት ሺህ አራት መቶ በላይ ቤቶችን ለማደስ ቃል ገብቶ ስራውን ከጀመረ ከራርሟል።

የካ ክፍለ ከተማ ወረዳ ስምንት በሁለት ወራት ውስጥ ሀያ ስድስት የአቅመ ደካማ ቤቶችን ሲያድስ በወረዳው ቀጣና ስምንት ልዩ ስሙ ቄማ ተራ በመባል የሚታወቀው የእማማ አረጋሽም ሰፈር የዚሁ እድል ተጋሪ ሆነና ቤታቸው ታደሰላቸው።

በሀዘን ጎናቸው ደቆ የቆየው እማማ አረጋሽ በቤታቸው መታደስ እጅግ አመስግነዋል። "ቤቴ የፈራረሰ ነበር፤ በክረምት ደግሞ ከዝናቡ ጋር ተዳምሮ ኑሮን እጅግ አስቸጋሪ አድርብኝ ቆይቷል። አስቸጋሪነቱንና የቤቱን ችግር አይተው እነዚህ በጎ ሰዎች አድሰውልኛል። ቤቱ ተጀምሮ እስከሚያልቅ ድረስ እያመሰገንኩኝ ነው፤ ቤቴ ይሰራል ብዬም አላሰብኩም ነበር። ይሄን ቀን ስላሳየኝ ፈጣሪን አመሰግናለሁ። ቤቱን ለማደስ ላሰበውም ላሰራውም ምስጋና ይድረስ! ጤናቸውን ይስጣቸው፤ እኔን በእድሜ ያንበሸበሸ አምላክ ለነሱም ረጅም እድሜን ይስጣቸው፤" ሲሉ ቃል አልባ ሆነው ምስጋናቸውን በአዛውንት ምርቃታቸው አቅርበዋል።

# የሀገርን ድንበር ለማስጠበቅ የድንበር ደኅንነት አስተዳደር ስትራቴጂ መንደፍ እንደሚገባ ተጠቆመ

**ሞገስ ተስፋ**

<u>አዲስ አበባ፡-</u> የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ለማስጠበቅና ሉአላዊነትን ለማረጋገጥ የድንበር ደኅንነት አስተዳደር ስትራቴጂ መንደፍ እንደሚገባ ተጠቆመ። ኢትዮጵያ ከሚያዋስኗት ጎረቤት ሀገራት ጋር ያሉት ድንበሮች በአግባቡ አለመካለላቸው ስጋቶች መሆናቸው ተገልጿል።

በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት "የድንበር ደህንነትና አስተዳደር አገራዊ ስትራቴጂ አስፈላጊነት" በሚል ርዕስ የፖሊሲ ምክክር መድረክ ከትናንት በስቲያ በኢንተርሌክዠሪ ሆቴል በተዘጋጀበት መድረክ ላይ የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ደሳለኝ አምባው እንደገለጹት፤ ድንበር ዜግነትንና ሉዓላዊነትን የሚይዝ፣ የአገር መለያ ሆኖ የሚያገለግል ዓለም አቀፍ ወሰን ነው።

እንደ ዶክተር ደሳለኝ ገለጻ፤ ድንበሮች የገንዘብ ልውውጥ፣ የታሪፍ እና የግብር ወሰንን የሚያሳዩ መሰረታዊ የሀገር መለያዎች ሲሆኑ ሐይቆች፣ ተራሮች፣ ወንዞች፣ ባሕር፣ አየር እና መሬት ብሔራዊ ድንበሮች ይሆናሉ።

የድንበር ደኅንነት በዋናነት የአንድ አገር ወሰንን ከሕገ ወጥ የመሣሪያ ዝውውር፣ አደንዛዥ ዕፆች፣ ኮንትሮባንድ እና ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር መከላከል ማለት ነው ያሉት ዶክተር ደሳለኝ፤ በሌላ መልኩ ሕጋዊ የሆኑ የሰዎችና የንግድ ልውውጥንና ዝውውርን መፍቀድ እንደሆነ ተናግረዋል።

በመሆኑም የድንበር ደኅንነት ብሔራዊ ሉዓላዊነትን፣ ኢኮኖሚያዊ ብልጽግናን እንዲሁም ቀጣናዊ ደኅንነትን ለማምጣት ወሳኝ መሆናቸውን ገልጸዋል።

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ በአገራት መካከል ያሉ ታሪካዊ ቅራኔዎች፣ የድንበር አለመካለሎች፣ የግዛት



ዶክተር ደሳለኝ አምባው

ጥያቄዎች እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች የድንበር ደኅንነትና አስተዳደርን በጋራ ለመምራትና ለመቆጣጠር እንዳይቻል እንቅፋት ሆኗል።

ኢትዮጵያ የምትገኝበት የምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና በተለይም የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ የድንበር ደኅንነት ስጋቶች በይበልጥ የተጠቃ እና ውስብስብ ችግሮች ያሉበት አካባቢ ነው። የአፍሪካ ቀንድ በሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር፣ የዕፅ ዝውውር፣ ድንበር ተሻጋሪ ሃይማኖታዊና የብሔር ግጭቶች፣ የታጠቁ መንግሥታዊ ያልሆኑ ኃይሎች የሚንቀሳቀሱበት ቀጣና ነው። በሌላ በኩል ያላለቀ የድንበር አለመካለሎች፣ የብሔርና የሃይማኖት ትስስር በቀጣናው አገራት መካከል



ዶክተር ግዛቸው አስራት

መኖር በአገራቱ መካከል የድንበር ግጭቶችና ጦርነቶች ማስከተሉን ገልጸዋል።

በቀጣናውም ይሁን በኢትዮጵያ እስካሁን ድረስ ሊጠቀስ የሚችል የተቀናጀና የተደራጀ የጋራም ይሁን የተናጠል የድንበር ደኅንነት አስተዳደር የለም። በአንጻሩ በአፍሪካ ቀንድ አገራት ውስጣዊ አለመረጋጋት ያሉባቸውና የእርስ በርስ ግጭቶች የሚበዙበት ቀጣና ነው። ስለዚህ በአገራት መካከል የተቀናጀ እና የተባበረ የድንበር ደኅንነት እና አስተዳደር ስትራቴጂ ያስፈልጋል። ኢትዮጵያ እንደ ሀገር በቀጣናው ያሉ ውስብስብ ችግሮችን ለመቅረፍና የዜጎቿን ደኅንነት እና የሀገሪቱን ሉዓላዊነት ለማስከበር የበኩሏን መወጣት እንድትችል የድንበር ደኅንነት አስተዳደር ስትራቴጂ መንደፍ ያስፈልጋታል ሲሉ ዋና ዳሬክተሩ ገልጸዋል።

የድንበር ደኅንነት አስተዳደር ምንነትና አስፈላጊነት አስመልክቶ ጥናታዊ ጽሁፍ ያቀረቡት በውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት የሰላምና ደህንነት ከፍተኛ ተመራማሪ ዶክተር ግዛቸው አስራት እንደገለጹት፤ የአንድ አገር የህልውና ምንጭ በግልጽ የሚወሰነው ባለው የግዛት መስመር ውስጥ ነው።

ወሰንን ከህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር እንቅስቃሴ መጠበቅ፣ ከአደንዛዥ እጽ ዝውውር፣ ኮንት

ሮባንድና ህጋዊ ካልሆነ መሳሪያና አሸባሪዎች ዝውውር መቆጣጠር የወሰን ማስጠበቂያ ዘዴ ነው። ይህን ለማድረግ በተቋማት መካከል ትብብርና ቅንጅት ያስፈልጋል።

በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የድንበርና ድንበር ተሻጋሪ ጉዳዮች የሚኒስትሩ አማካሪ የሆኑት አምባሳደር ኢብራሂም ኢድሪስ ‹‹የድንበር ደኅንነት አስተዳደር ስትራቴጂ ፣ ዓለም አቀፋዊ፣ አህጉራዊ እና ቀጣናዊ ልምዶችን›› በሚል ርዕስ ባቀረቡት ጥናታዊ ጽሁፍ ተሞክሮዎችን በመዳሰስ የኢትዮጵያ የድንበር ደኅንነት አስተዳደር ስትራቴጂ ሊቀስማቸው ስለሚገቡ መልካም ተሞክሮዎች አቅርበዋል። የአገር ዳር ድንበርን ለማስጠበቅና ሉአላዊነትን ለማረጋገጥ የድንበር ደኅንነትና አስተዳደር ላይ በትኩረት መስራት ያስፈልጋል ብለዋል።

ከተለያዩ የአገሪቱ ዳር ድንበርና በዘርፉ እውቀት ያላቸው ተሳታፊዎች በድንበር ደኅንነትና አስተዳደር ዙርያ ምክክር መደረጉ በተለይ የድንበር ውዝግቦች ሲፈጠሩ በምን መልኩ መፈታት እንዳለበት ገንዛቤ እንዲኖር የሚያስችል ነው ብለዋል።

# ሀገርን ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ ውጤታማ የምርምር ሥራዎች ማከናወን እንደሚገባ ተገለጸ

ሞገስ ተስፋ

አዲስ አበባ፡- ፓርላማውን ጨምሮ በኢትዮጵያ ያሉ ተቋማት አገርን ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ የሚያስችል ውጤታማ የምርምር ስራዎችን ማከናወን ይጠበቅባቸዋል ሲሉ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ አቶ ታገሰ ጫፎ ገለጹ።

አቶ ታገሰ ጫፎ ትናንት ለሁለት ቀናት የሚቆየውን ሁለተኛውን የፓርላማ የምርምር ኮንፈረስ ባስጀመሩበት ወቅት እንደገለጹት፤ የጥናትና የምርምር ስራ ተቋማት በሚሰሩት ስራ ላይ ውጤታማ እንዲሆኑና የአገርን ዕድገት ለማረጋገጥና የተሳለጠ አሰራር እንዲኖር አስፈላጊ ናቸው።

የሩቅ ምስራቅ ኤዥያ አገሮች ከነበሩበት መካከለኛ ገቢ ወደ ከፍተኛ ደረጃ የደረሱት ወሳኝ ተቋም በመገንባት የምርምር ስራዎችን በማቀናጀት በሰሩት ውጤታማ ተግባር ነው ያሉት አቶ ታገሰ፤ በሌላ በኩል የላቲን አሜሪካ አገሮች መካከለኛ የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ የቆሙበት ዋናው ምክንያት በምርምርና በቴክኖሎጂ ስራዎቻቸውን በማዘመንና ለዛ የሚሆን ተቋም መገንባት ባለመቻላቸው መሆኑን ለአብነት ጠቅሰዋል።

እንደ አቶ ታገሰ ንግግር፤ የፓርላማ የምርምር ኮንፈረንስ በተልዕኮው ዙሪያ ባሉ ጉዳዮች ምርምር በማድረግ ስራዎችን በማዘመን ሌሎች ተቋማትን በመከታተል ሂደት ውጤታማ እንዲሆኑ ለማስቻል ሲሆን፤ ለዚህም የምርምር ኔትወርክ ተቋቁሞ በቅንጅት እየተሰራ ነው። ፓላርማው በራሱ የምርምር አጀንዳዎችን በመቅረጽ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር እንዲሁም ቋሚ ኮሚቴዎቹ ከራሳቸው ተልዕኮ ጋር በተያያዘ የምርምር ስራዎች እንዲከናወኑ እያደረጉ መሆኑንም ተናግረዋል።



አቶ ታገሰ ጫፎ



ዶክተር ሳሙዔል ክፍሌ

ፓርላማውን ጨምሮ በኢትዮጵያ ያሉ ተቋማት አገርን ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ ውጤታማ የምርምር ስራዎችን ማከናወን ይጠይቃል ያሉት አቶ ታገሰ፤ ለዕድገት ማነቆ የሆኑ ጉዳዮችን ለመፍታት የምርምር ስራዎች አጋዥ ናቸው ብለዋል። በምርመር የተገኘው ውጤት ተግባራዊ ለማድረግ በትኩረት መስራት እንዳለበትም ጠቁመዋል።

ህግ አውጪው አካል አገሪቱ አሁን በደረሰችበት ደረጃ ልክ የሚያስፈልጉ የአሰራርና የአደረጃጀት ለውጥ በማድረግ አስፈጻሚውና ህግ ተርጓሚው ተልዕኳቸውን እንዲወጡ ለማስቻል መስራት ያስፈልጋል ሲሉ አፈ ጉባኤው ተናግረዋል።

በትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ሳሙዔል ክፍሌ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ የምርምር ኮንፈረንሱ አገራችን አሁን ካለችበት ሁኔታ በጽኑ የተሳሰረ፤ በብዙ ጥናት መደገፍ እንዳለበትና ሰፊ ውይይት ማድረግ እንደሚያስፈልግ የሚያመላክት ነው።

የአገረ መንግሥት ግንባታ እንዲሳካ ፓርላማው ያለው ሚና ከፍተኛ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ የተሻሉ ተቋማት እንዲፈጠሩ ማድረግ፣ የሕዝብ አኗኗር እንዲለወጥ፣ ስርዓት እንዲኖር ፣ ዜጎች ዋስትና እንዲኖራቸው፣ ተቋማት ተጠያቂ እንዲሆኑ ለማድረግ ፓርላማው በአሰራሩ፣ በህግ አወጣጡ፣ በአፈጻጸሙ እንዲጠናከር ለማድረግ የምርምር ስራዎች አስፈላጊ መሆናቸውንም ገልጸዋል።

የምርምር ስራዎች የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ ማየትና ማገናዘብ ይኖርባቸዋል ያሉት ዶክተር ሳሙኤል ፤ፓርላማው አስፈጻሚውን የመቆጣጠር አቅሙ እንዲያድግ ከተፈለገ ራሱ ፓርላማው የሚጠናከርበት ስራ መስራት ይጠበቅበታል ብለዋል። ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ስራውን በከፍተኛ ኃላፊነት እንደሚደግፍ ጠቁመው፤ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ይህን መሰል የምርምር ስራ በከፍተኛ ኃላፊነት እንዲሰሩም ጥሪ አቀርበዋል።

በፓርላማው የምርምርና የጥናት ኮንፈረንስ « ውጤታማ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የዳኝነት አካል ግንኙነት ለዲሞክራሲያዊ መንግሥት ግንባታ፣ ፓርላሜንታዊ ቁጥጥር፣ ተጠያቂነት፣ የውጭ ፖሊሲና ዲፕሎማሲያዊ ተዋንያን፣ ስልቶች፣ ፈተናዎችና የወደፊት አቅጣጫዎች" በሚሉ ጉዳዮች ዙሪያ ምሁራን ጥናታዊ ጹሁፎች አቅርበዋል። በዚህም በምርምር ሥራዎች ፓርላማው ራሱን ለማዘመንና ለውጥ ለማምጣት አመላካች ናቸው። ምክር ቤቱ አዳዲስ የምርምር ግኝቶችን እና ምክረ ሐሳቦችን በመቀመር፣ ለሚያወጣቸው ሕጎች በግብዓትነት እንደሚጠቀም ምሁራኑ በጥናታዊ ጽሁፋቸው አመላክተዋል።

# "ለሌብነት ሲባል የሚደረገው መዝገብ የማጥፋት ወንጀል ህዝቡን የከፋ ምሬት ውስጥ ከቶታል"

-ዶክተር ዳባ ጩፋ
የህግ አማካሪና ጠበቃ

ማህሌት አብዱል

አዲስ አበባ፡- በፍርድ ቤቶችና በአንዳንድ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ለሌብነት እንዲመች ሲባል ሆን ተብሎ የግለሰቦች መዝገብ የማጥፋት ወንጀል ህዝቡን የከፋ ምሬት ውስጥ የከተቱት መሆኑን የህግ አማካሪና ጠበቃ ዶክተር ዳባ ጩፋ አስታወቁ። በኦሮሚያ አንዳንድ አካባቢዎች የሚስተዋለው የፀጥታ ችግር የፍርድ ቤቶችን ሥራ ሙሉ ለሙሉ በማስቆሙ ነዋሪዎች ፍትህ የማግኘት መብት ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ማድረጉን አመልክተዋል።

የህግ አማካሪውና ጠበቃ ዶክተር ዳባ ጩፋ ከአዲስ ዘመን ጋር በነበራቸው ቆይታ እንዳመለከቱት፤ በፍርድ ቤቶች ፤ ከክፍለ ከተማ እስከ ቀበሌ ድረስ ባሉ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሆን ተብሎ የሚደረግ የነዋሪዎች መዝገብ ማጥፋት ሂደት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበራከተ መጥቷል። ይህም ተገልጋዩን ህብረተሰብ ለእንግልት እና ለከፋ ምሬት የዳረገ ከመሆኑም ባሻገር ህዝቡ በመንግስት ላይ ያለውን አመኔታ እያሳጣው ይገኛል።

‹‹ በተለይም ፍርድ ቤቶች ላይ ሆን ተብሎ መዝገብ ጠፋ ይባላል፤ ተገልጋዩ ህብረተሰብ የገዛ መዝገቡን ለማግኘት ከአራት ጊዜ በላይ እንዲመላለስ ይደረጋል›› ያሉት ዶክተር ዳባ፤ ይህም የፍርድ ሂደቱን በከፍተኛ ደረጃ ያስተጓጎለው መሆኑን አስታውቀዋል። ‹‹እኔ የደንበኞቼ መዝገብ በተደጋጋሚ ጠፋ ተብሎ በጊዜው የሚያስፈልገውን መረጃ መሰብሰብ ባለመቻሌ ፍርድ ያለአግባብ እንዲዛነፍብኝ ሆኗል›› ሲሉ በግላቸው ያጋጠማቸውን አብነት አድርገው ጠቅሰዋል።

ይህ አይነቱ አሰራር አሁን አሁን እየተለመደ በመምጣቱ ደንበኞች ሳይወዱ በግዳቸው ጉቦ እንዲሰጡ መደረጋቸውን አንስተውም ‹‹ይሄ ግልፅ የሆነ ሌብነት ነው። ይህ አይነቱን ሌብነት ከወዲሁ በእንጭጩ ካልቀጨነው ወደ ነውጥ ይሄዳል። ህዝባዊ



አመፅ ያመጣል›› በማለት ስጋታቸውን አስቀምጠዋል። አክለውም ‹‹ሰው መብቱን ከተነፈገ ዝም ብሎ ቁጭ አይልም፤ የትና ማን እንዳጠፋበት ያውቃል፤ ከዚያ በኋላ ስርዓት አልበኝነት ይመጣል። አንዱ በሌላው ላይ ይነሳል፤ መገዳደል ይከሰታል›› ብለዋል።

ልክ እንደፍርድ ቤቱ በየክፍለ ከተማው፤ ወረዳውና ቀበሌ ላይ በዚህ አይነቱ የሌብነት አሰራር መጠመዳቸውን አንስተው ‹‹ከመዝገብ ቤት ሰራተኛ ጀምሮ እስከ ከፍተኛ አመራር ድረስ ባሉ የመንግስት ባለስልጣናት መዝገብ ይሰርቃሉ፤ የፍርድ ቤት ውሳኔን ያስገለብጣሉ፤ ምክንያቱም እጃቸው ረጅም ነው›› በማለት ጠቁመዋል።

ይህ አይነቱ የሌብነት መንገድ መጠኑ እየሰፋ የሄደው በዋናነት በአመራሩ ችግር ምክንያት እንደሆነም አስረድተዋል። ‹‹በተለይ አዲስ አበባ ላይ የሚታየው የአመራር ብቃት ማነስ ሳይሆን የስነ-ምግባር ችግር ነው›› ያሉት ዶክተር ዳባ፤ ይህም የፖለቲካ ስርዓቱ እንዳይረጋጋ ካደረጉት ነገሮች መካከል በዋናነት የሚጠቀስ እንደሆነ ተናግረዋል።

ዶክተር ዳባ አያይዘውም በኦሮሚያ ክልል በአንዳንድ አካባቢዎች የሚስተዋለው የፀጥታ ችግር የፍርድ ሂደቱን እያስተጓጎለው መሆኑን አመልክተዋል። ከሁለት ዓመታት በላይ ሸኔ በክልሉ በሚፈፅመው የሽብር ተግባር አብዛኞቹ የፍትህ ተቋማት መዘጋታቸውን ጠቁመው ‹‹በተለይም በምዕራብ ኦሮሚያ ባሉ በርካታ የገጠር ወረዳዎች መንግስት ያለ እስከማይመስል ድረስ በፀጥታ ችግር ምክንያት ፍትህ ሙሉ ለሙሉ ተቋርጧል›› ብለዋል።

እንደእርሳቸው ማብራሪያ፤ የፀጥታ ችግር ባለባቸው አካባቢዎች በርካታ ፍርድ ቤቶች፤ ፖሊስ ጣቢያዎች በመዘጋታቸውም አገልግሎት እየሰጡም አይደለም። በአካባቢው የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ፍትህ የማግኘት፤ በሰላም የመኖር ህልውና ተጠብቆ የመኖር መብታቸው አደጋ ውስጥ ወድቋል። ይህም ማህበረሰቡ ፍትህ የማግኘት ህገ-መንግስታዊ መብቱ እንዳይከበር ምክንያት ሆኗል። ይህ ደግሞ ህዝቡ በመንግስት ላይ ያለው አመኔታ እንዲሸረሸር ያደርገዋል።

‹‹የሁሉም ስልጣን ባለቤት መንግስት ነው፤ ስልጣኑን ተጠቅሞ የሕዝብንና የሀገርን ደህንነት የማስጠበቅ፤ ፀረ-ሰላም ሃይሎች ላይ አስፈላጊውን ርምጃ የመውሰድ ኃላፊነት አለበት›› ያሉት የሕግ አማካሪው፤ ህዝቡ ሀገርን እንዲያስተዳድር ቀጥተኛ ውክልና የሰጠው ለመንግስት ቢሆንም በአሸባሪ ቡድኖችና ሀገር አዋኪዎች ላይ የሚወሰደው ርምጃ የላላ መሆኑን አስረድተዋል።

ሰላም የሁሉም ነገር መሰረት መሆኑን የተናገሩት ዶክተር ዳባ፤ በመሆኑም መንግስት በህዝብ የተሰጠውን የሀገርን ሰላም የማስጠበቅ ኃላፊነት በሚገባ ሊወጣ እንደሚገባ አስገንዝበዋል። ህብረተሰቡም የፀረ ሰላም ኃይሎችን እንቅስቃሴ በማጋለጥ ከመንግስት ጎን እንዲቆም ጠይቀዋል።

# ስተፈጸሙ ሰብዓዊ ጥቃቶች ፍትህ መስጠት፣ መሰል ጥቃቶችም እንዳይደገሙ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- ያለጥፋታቸው ለተገደሉ ንጹኃን ዜጎች ፍትህ በመስጠት መሰል ጥቃቶች ዳግም እንዳይከሰቱ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ በተለይ ከመንግስት ብዙ ነገር እንደሚጠበቅ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቹ አቶ አባንግ ሜቶ አመለከቱ።

አቶ አባንግ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤አሁን አሁን በኢትዮጵያ በንጹኃን ዜጎች ላይ የሚፈጸም ጥቃት እየተለመደ መምጣቱ ለወደፊትም መሰል ጥቃቶች እንደማይፈጸሙ እርግጠኛ መሆን አዳጋች ሆኗል።

ቀደም ሲል በአፋር፣ በደቡብ፣ በአማራ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ የንጹኃን ግድያ ሳያበቃ ሰሞኑን ደግሞ በጋምቤላና በተለይ ደግሞ በኦሮሚያ ክልል በሰላማዊ ዜጎች ላይ የተቃጣው ጥቃት እንደብሔር ሳይሆን እንደሰብዓዊ ፍጡር በእጅጉ የሚያሳዝንና አንገት የሚያስደፉ ክስተት ነው ብለዋል።

“በየትኛውም አካባቢ ጥቃት የደረሰበት ዜጋ ኢትዮጵያዊ በመሆኑ ሁላችንም ይሰማናል፣ ወንድም በወንድሙ ላይ በጭካኔ ሲነሳ ሁላችንን ይነካናል” ያሉት አቶ አባንግ፣ የእያንዳንዱ ሰው ሞት የሁሉም ጉዳት ከመሆኑም በላይ ለሌላውም የሚተርፍ መዘዝ መሆኑን በመገንዘብ አሁን ላይ በማንነት ጥቃት ምክንያት እንደ አገር ለመፈንዳት ጫፍ የደረሰውን የእርስ በእርስ ጦርነት ለመቀልበስ ከተፈለገ ሁሉም የወንድሙ ጠባቂ መሆን እንደሚያስፈልግ አስገንዝበዋል።

እንደ አቶ አባንግ ገለጻ፤ ኢትዮጵያውያን




**አቶ ኦባንግ ሜቶ**

ለአያሌ ዓመታት በሰላም አብረው በመኖር ሀገር እንዳስረከቡን ከታሪክ ተምረናል፣ እኛም ወግ ደርሶን ለማየት ችለናል፤ አሁን ላይ ግን የፖለቲካ ሰዎች ምንም የፖለቲካ ትርፍ በሌላው ነገር ስለፖለቲካ ምንም የማያውቁ ንጹኃን ዜጎች ላይ በማነጣጠር የሚወስዱት ኢ. ሰብዓዊ ጥቃት ለሀገሪቱ አሳሳቢ ችግር ነው።

በሀገሪቱ ማንነትን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች በአንድ አካባቢ ብቻ ሳይሆን ተለዋዋጭ ባህሪ በመያዝ በአሁኑ ጊዜ በሁሉም አካባቢ በሚባል ደረጃ የሚከሰቱ ችግሮች በመሆናቸው የሁሉም ርብርብ የሚጠይቅ ችግር ነው ያሉት የሰብዓዊ መብት ተሟጋቹ፣ እውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ አሁን ባለው ሁኔታ ግን የአንዱ ጉዳት ለሌላው እምብዛም ትርጉም የማይሰጥ ሆኖ ሲታይ እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ የሚያፍሩበት ድርጊት መሆኑንም አልሸሸጉም።

“የጠላቶቻችን ዓላማ ስስ ብላታችንን በማጥናት በተለይ በማንነት እንድንጨራረስና እንድንበተን ተግተው እየሰሩ ነው” ያሉት አቶ አባንግ፣ ከዚህ አንጻር ሰሞኑን አንጻራዊ ሰላም ያለበትና ህዝቡ በሰላም አብረው የሚኖርበት ጋምቤላ ክልል ሸኔና በክልሉ የሚንቀሳቀሱ ታጣቂዎች በቅንጅት ከፈጸሙት ጥቃት ጋር ተያይዞ በንጹኃን ላይ እንዲደርስ ከማድረግ ባሻገር አብረው የመኖር ባህል አደጋ ላይ ለመጣል የሄዱበት ርቀት ቀላል አለመሆኑን አመልክተዋል።

እንደ አቶ አባንግ ማብራሪያ፣ እስካሁን ለጠፋው የሰው ሕይወት ፍትህን ማረጋገጥ ካልሆነ በቀር መመለስ አይቻልም። ዋናው ነገር ግን አሁንም ቢሆን ከፍተኛ ስጋት ውስጥ ያሉ ዜጎችን መታደግ ነው። ገዳዩም ሟቹም ኢትዮጵያዊ ከሆነ ይህንን ለሁሉም የሚተርፍ ችግር ኢትዮጵያውያን በጋራ መፍትሄ ማበጀት ያለው ጊዜ አሁን ነው። መንግስትም ቢሆን የዜጎችን ደህንነት ለመጠበቅ መንግስታዊ ኃላፊነቱን በተገቢው ሊወጣ ይገባል።

## “በገዳ ሥርዓት ወንድምን...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ችግሮችን ለመፍታት በኦሮሞ ስም የሚታገል ሁሉ ለገዳ ሥርዓት እሴቶች በመገዛት ራሱን ከዚህ አይነት አፀያፊ ድርጊት ሊያርቅ እንደሚገባውም ጠቁመዋል።

በሕግ አስከባሪ ኃይሎች እና በታጣቂ ኃይሎች መካከል ጦርነት ሲካሄድ የሕዝቡ ሰላም እየደፈረሰ መሆኑን ጠቅሰው፤ ለደፈረሰው ሰላም መፍትሄው በጋድሳ ኦሮሞ ስር ተሰብስቦ በመነጋገር መፍትሄ ማበጀት ነው ብለዋል።

ጉጂ አባ ገዳ ጂሎ መንደሆ በበኩላቸው፤ በገዳ ሥርዓት መሰረት ወንድም ወንድሙን መግደል ክልክል ነው ብለዋል። እንደ ገዳ ስርዓት እሴት ወንድሙን የገደለ ሰው ሰባት ወንዝ ተሻግሮ ከማህበረሰቡ ተለይቶ እንዲኖር ይደረጋል። ገዳ ስርዓት የወንድማማቾች ግድያን የሚያወግዝ ብቻ ሳይሆን በማንኛውም ሰው ላይ የሚደርሰውን ግድያ አይቀበልም።

የማንኛውም ሰው ግድያ ከልቤ ያሳዝነኛል ያሉት አባ ገዳ ጅሎ፤ በአገኙት አጋጣሚ በተለያዩ መገናኛ ብዙኃን አማካኝነት ጫካ ገብተው መንግስትን ለሚዋጉ ኃይሎች ከመንግስት ጋር ተነጋግረው መፍትሄ እንዲያበጁ መልዕክት መላከቸውን ገልጸዋል።

ኅብረተሰቡ በሠላም እጦት እየተቸገረ ነው ያሉት የጉጅ አባ ገዳ፤ ሠላም ለማስፈን ሁሉም በመነጋገር ለሠላም እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮችን በማስወገድ መፍትሄ ማስቀመጥ አለበት ብለዋል። ኅብረተሰቡም ሠላም እንዲመጣ የበኩሉን ሁሉ ሊወጣ ይገባል ብለዋል።

[redacted]

## ‹‹የመንግሥት አካላት

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ድርጊቱን የሚፈጽሙት የንጹሃንን ደም መተዳደሪያቸው ያደረጉ የፖለቲካ ነጋዴዎች የሰው ደም እያፈሰሱና ሕይወት እያጠፉ ለእነርሱ ቤት ስራ እየሰሩ ናቸው ብለዋል። ሁልጊዜ ትልቅ ጥያቄ በሚያስነሳ ሁኔታ በመቶዎች ተገደሉ ሺዎች ተፈናቀሉ ሲባል መስማት ያሳዝናልም ነው ያሉት።

መንግስት ጥበቃ የሚያስፈልጋቸውን አካባቢዎች ለይቶ የሀገር መከላከያ ሰራዊት በማሰማራት ሊጠብቅ ይገባል። የሰው ሕይወት ከጠፋ በኋላ ማዘን ትርጉም የለውም። ጥፋት ያደረሱ ኃይሎች አቅማቸውን አጎልብተው ጥቃት ለማድረስ አይመለሱምና አሁንም ጥንቃቄ ሊደረግ እንደሚገባ አመልክተዋል። ድርጊቱ በእጅጉ መንፈሴን የነካ ጉዳይ ነው። ይህ ጥቃት በቸልታ መታየት የለበትም። በሰላም የሚኖር ንጹህ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ለእዚህ አይነት አደጋ ሊጋለጥ አይገባም ብለዋል።

# ስመኸር እርሻ ከ155 ሺህ ኩንታል በላይ ምርጥ ዘር ስአርሶ አደሩ ተደራሽ መሆኑ ተጠቆመ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን ለመኸር እርሻ 155 ሺህ 348 ኩንታል የተለያዩ ምርጥ ዘሮችን ለአርሶ አደሮች ማሰራጨቱን አስታወቀ። በአገሪቷ የምርጥ ዘር ግብዓት እጥረት ችግርን ለማቃለል ትኩረት አድርጎ በመሥራት ላይ መሆኑንም ኮርፖሬሽኑ አስታውቋል፡፡

የኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽንና ማህበራዊ ጉዳዮች አገልግሎት ኃላፊ ጋሻው አይችሉህም፤ ለኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት እንደገለጹት፤ ኮርፖሬሽኑ በ22 የሰብል ዓይነቶች 69 የሰብል ዝርያዎችን በማባዛት ለአርሶ አደሮች ተደራሽ በማድረግ ላይ ይገኛል ብለዋል። ኮርፖሬሽኑ መሬት፣ በኮንትራት ሰፋፊ እርሻ እና በአርሶ አደር መሬት በድምሩ 14 ሺህ 608 ሄክታር መሬት ላይ ዘር ማባዛቱን ተናግረዋል።

ለዘንድሮው የመኸር እርሻም አባዝቶ ካዘጋጀው 280 ሺህ ኩንታል በላይ ምርጥ ዘር እስካሁን 155 ሺህ 348 ኩንታል ለአርሶ አደሩ ተደራሽ ማድረጉ ተገልጿል። ኮርፖሬሽኑ በአገር ደረጃ በየዓመቱ ከሚያስፈልጉ የምርጥ ዘር ፍላጎት እስከ 30 በመቶውን እያቀረበ መሆኑንም ጠቁመዋል።

ለ2014 የመኸር እርሻ ከ3 ቢሊዮን ብር በላይ ዋጋ ያላቸውን የአፈር ማዳበሪያ፣ አግሮ ኬሚካሎች፣ የእንስሳት መድኃኒት እና የኬሚካል መርጫ መሣሪያዎችን ለተጠቃሚዎች ማቅረቡንም ገልጸዋል።

በተጨማሪም የእርሻ መሣሪያዎችን ከውጭ በማስመጣት የሽያጭ እና የኪራይ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን ተናግረዋል።

ኮርፖሬሽኑ ለመጪው የምርት ዘመን 365 ሺህ ኩንታል ምርጥ ዘር ለማባዛት ማቀዱንም ጠቁመዋል።

በኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን የአዳማና አሰላ ቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጆች፤ ምርጥ ዘር እና የተለያዩ ኬሚካሎች ለአርሶ አደሮች እየደረሱ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የአሰላ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት የአርሶ አደሮችን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ እስካሁን 30 ሺህ ኩንታል ምርጥ ዘር ማሰራጨቱን ገልጿል፡፡

በተጨማሪም 50 ሺህ ሄክታር መሬት የሚሸፍን 15 ሺህ ኩንታል የጤፍ ዘር ተዘጋጅቶ ለአርሶ አደሮች ሊከፋፈል መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የአዳማ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤትም እስካሁን ከ100 ሺህ ሊትር በላይ ኬሚካል ለአርሶ አደሮች ማሰራጨቱን አስታውቋል።

አሁን ላይ 20 ሺህ ሊትር ኬሚካል የመድኃኒት ክምችት መኖሩንም ጠቁመዋል፡፡

ኢዜአ ያነጋገራቸው አርሶ አደሮችም የተሻሻለ ምርጥ ዘር በመጠቀማቸው ምርታማ እያደረጋቸው መሆኑን ገልጸዋል።

ምርጥ ዘር ከመጠቀማቸው በፊት ከ1 ሄክታር መሬት 18 ኩንታል የስንዴ ምርት ሲያገኙ እንደነበር አስታውሰው፤ ምርጥ ዘር ከተጠቀሙ በኋላ ግን ምርቱ በእጥፍ ማደጉን ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን ወደ አገር ውስጥ የሚገባ ማዳበሪያ ብቸኛ አስመጪ ሲሆን ግዢ ከተፈፀመው ውስጥ እስካሁን 92 በመቶ ማዳበሪያ ወደ አገር ውስጥ መግባቱን እና ጂቡቲ ወደብ መድረሱን አስታውቋል፡፡

ለምርት ዘመኑ ወደ አገር ውስጥ ገብተው ለአርሶ አደሮች ከተሰራጩ አግሮ ኬሚካሎች በተጨማሪ በአሁኑ ጊዜ 300 ሺህ አግሮ ኬሚካሎች በኮርፖሬሽኑ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች መኖራቸው ተጠቁሟል፡፡

የቅዳሜ መጽሄት

# አገልግል



ፎቶ፦ በፀሐይ ንጉሤ

## ‹‹የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች የተፈጠረውን ችግር በመቀራረብ እንጂ በመለያየት አይፈቱትም››

- ዶክተር ዳባ ጩፋ
የሕግ አማካሪና ጠበቃ

ገጽ 6



የጊዜን ጥቅም የተረዳው የጊዜሸወርቅ የስኬት መንገድ

ገጽ 13



እንደወርቅ በእሳት...

ገጽ 16

ከአ.አ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# ምላሽ ሲያገኝ የተቃረበው የ1997 የቤት ተመዝጋቢዎች ጥያቄ

**ሶሎሞን በየነ**

በመጀመሪያው የቤት ምዝገባ ማለትም በ1997 ዓ.ም ተመዝግበው ነገር ግን እስካሁን ቤት ያልደረሳቸው ምን ያህል ሰዎች አሉ? ከነዚህ ውስጥ የሚጠበቅባቸውን ቁጠባ የቆጠቡ ምን ያህል ናቸው? የነዚህ ሰዎችስ ቀጣይ እጣ ፈንታቸውስ ምን ይሆን? የሚሉ ጥያቄዎች ዙሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን የቤት ማስተላለፍ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ለሆኑት አቶ አውራሪስ ከበደ የሰጡን ማብራሪያ እንደሚከተለው ተሰናድቷል።

እንደአቶ አውራሪስ ገለጻ፤ በመዲናዋ የሚስተዋለውን የቤት አቅርቦትና ፍላጎት ልዩነት ለማጣጣም እንዲሁም የቁጠባን ባህል ለማበረታታት በመጀመሪያ ምዝገባ በ1997 እና በዳግም ምዝገባ በ2005 ዓ.ም አጠቃላይ ወደ አንድ ሚሊዮን የሚጠጋ ቤት ፈላጊ ተመዝጋቢ ነበር። ከዚህ ውስጥ ዕጣ ወጥቶለት ቤቱን ተረክቦ ከምዝገባ ቋቱ ላይ የተቀነሰ ሰው አለ። በአንጻሩ ደግሞ በራሱ መንገድ የቤት ፍላጎቱን አሟልቶ ወይም በተለያየ ምክንያት ቁጠባውን አቋርጦ ከምዝገባ የወጣ አለ። በዚህም አሁን ላይ አጠቃላይ ወደ 600 ሺ ሰው ቤት ፈላጊ ተመዝግቦ የሚጠብቅ ሰው እጃችን ላይ ይገኛል። ከዚህ ውስጥ በመጀመሪያ ዙር ምዝገባ በ1997 ዓ.ም ተመዝግበው ቤት ያልደረሳቸው 43 ሺ ቤት ፈላጊዎች ይገኛሉ። በ1997 ባለሦስት መኝታ ቤት የተመዘገቡ ሁሉም ቤታቸውን ተረክበዋል። የቀሩት ባለሁለት፣ ባለአንድና ስቱዲዮ ተመዝጋቢዎች ናቸው።

ሆኖም አንድ ቤት ፈላጊ ቤት ፈላጊ ነው ተብሎ የሚወሰደው ለቤት ልማት ፕሮግራሙ የተቀመጠውን የቁጠባ መጠን ሲቆጥብ ነው። የሚጠበቅበትን ቁጠባ መቆጠብም ግዴታው ነው። ማለትም አንድ ተመዝግቦ ቤት በመጠባበቅ ላይ ያለ ግለሰብ በ40/60 የቤት ልማት ፕሮግራም ከሆነ የተመዘገበው 40 በመቶውን (በወር 2500 ብር)፣ በ20/80 ከሆነ 20 በመቶውን (በወር 520 ብር) እንዲሁም የተመዘገበው ስቱዲዮ ከሆነም የሚጠበቅበትን ቁጠባ ለ60 ወር ወይም ለአምስት ዓመትና ከዛ በላይ መክፈል ይጠበቅበታል። ምክንያቱም የቤት ልማት ፕሮግራሙ አንደኛው ዓላማ የተመዝጋቢዎችን የቁጠባ ባህል ለማበረታታት ነው። ሁለተኛው ዕጣ የሚወጣላቸው የቤት ዕድለኞች እጣው ሲወጣላቸው ቅድመ ክፍያውን ሳይቸገሩ እንዲያሟሉ ነው። ሌላው በተዘዋዋሪ ከቤት ልማት ፕሮግራሙ ባሻገር ለአገሪቱ የቁጠባ ሥርዓትና ኢኮኖሚ ዕድገት አስተዋጽዖ አለው። ስለዚህ ተቋሙ የሚጠበቅበትን ቁጠባ እየቆጠበ ያለ አካልን ነው "ተመዝጋቢና ቤት ፈላጊ" ብሎ የሚያስበው። ነገ ላይም ግንባታቸው የሚጠናቀቁ ቤቶችን ለነዚህ ግለሰቦች ነው ዕጣ አውጥቶ የሚያስተላልፈው።

ነገር ግን በመጀመሪያ ዙር ምዝገባ በ1997 ዓ.ም ተመዝግበው ቤት ካልደረሳቸው 43 ሺ ቤት ፈላጊዎች ውስጥ የሚጠበቅባቸውን ቁጠባ በአግባቡ እየቆጠቡ ያሉ 23 ሺ ገደማ ናቸው። ይህ መረጃ ከሶስት ወር በፊት ከባንክ የተወሰደ ስለሆነ የቆጣቢዎች ቁጥር ከፍና ዝቅ እንደሚል ግምት ውስጥ ይግባ። ቀደምያሉ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ደግሞ ቁጥሩ ከዚህ በእጅጉ ያንሳል።

በመሆኑም 20 ሺ ገደማ የሚሆኑት የሂሳብ ደብተራቸው አለ፣ ተመዝግበዋል፣ ከምዝገባው አልወጡም፣ አንድ ወር ወይም አንድ ዓመት ሊሆን ይችላል ወ.ዘ.ተ የተወሰነ ብር ቆጥበዋል። ነገር ግን እነዚህ ለቤት ልማት ፕሮግራሙ የተቀመጠውን የቁጠባ መጠን ስላልቆጠቡ ለቤት ፍላጎቱ ብቁ አይደሉም። ቤት ፈላጊ የሚባለው የሚጠበቅበትን ቁጠባ የቆጠበ ወይም ሙሉውን የቆጠበ ነው። ስለዚህ በመመሪያው መሰረት ለ60 ወር ወይም ለአምስት ዓመት የሚጠበቅበትን ቁጠባ ያልቆጠበ በቀጣይ ዕጣ ሲወጣ ዕጣ ውስጥ አይካተትም። ቤቶቹ የሚተላለፉት የሚጠበቅባቸውን ቁጠባ ለቆጠቡ እንደሆነ አቶ አውራሪስ ያስረዳሉ።

በመመሪያ ቁጥር 3/2011 ላይ የ1997 ዓ.ም ዝቅተኛ ገቢ ወይም 20/80 የቤት ልማት ፕሮግራም ተመዝጋቢ ቤት ደርሷቸው እስካላለቁ ድረስ ለአዲስ ተመዝጋቢ ማለትም በ2005 ዓ.ም ለተመዘገበ እጣ እንደማይወጣ በግልጽ መደንገጉን አቶ አውራሪስ ጠቁመው፤ በቀጣይ እጣ የሚወጣባቸው ቤቶች ተግባራዊ የሚደረገው በዚህ መመሪያ መሰረት ነው። በመሆኑም አዲስ እጣ የሚወጣባቸው ቤቶች መጀመሪያ የሚተላለፉት በነባር በ1997 ተመዝግበው የሚጠበቅባቸውን ቁጠባ እየቆጠቡ ላሉ ቤት ፈላጊዎች በሙሉ ይሆናል። ከዚህ አኳያ በጀት ዓመቱ ሳይገባደድ በነባር በ1997 እና በዳግም ምዝገባ በ2005 ዓ.ም ተመዝግበው እየቆጠቡ ላሉ ቤት ፈላጊዎች 30 ሺ (በ4060ና በ2080 የቤት ልማት ፕሮግራሞች) አዲስ እጣ የሚወጣባቸው የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ለማስተላለፍ እቅድ ተይዞ እየተሠራ ነው። ስለዚህ በተያዘው እቅድ የቤቶቹ ግንባታ ተጠናቆ ለቦርድ ይቀርባል። ቦርዱ ዕጣ የሚወጣበትን ቀን፣ የቤት አይነት፣ የቤቶች ብዛትና የማስተላለፊያ ዋጋውን ሲወስን ዕጣው ለቤት እድለኞች የሚወጣ ይሆናል።

ሌላው አንድ ሰው በነባር በ1997 እና በዳግም ምዝገባ በ2005 ዓ.ም ተመዝግቦ ዛሬ ላይ በሕይወት ላይኖር ይችላል። ከዚህ አንጻር በመመሪያ ቁጥር 3/2011 ላይ ተመዝጋቢው አካል በሕይወት ከሌለ 18 ዓመት ያልሞላቸው ልጆች ካሉ ብቻ እጣውን ይወርሳሉ በሚል ተቀምጧል። ነገር ግን ከ18 ዓመት በላይ ያሉ ልጆች እንዲሁም ባል የሚስቱን፣ ሚስት የባሏን ንብረት የመውረስ ሕገ መንግስታዊ መብት ጋር ስለሚጣረስ "ዕጣ አይወረስም" በሚለው ላይ የፌዴሬሽን ምክርቤት ትርጓሜ ሰጥቶበት ዕጣ ይወረሳል የሚል ትርጓሜ በመመሪያው ተካቷል። ሆኖም ዕጣ ይወረሳል ሲባል ምዝገባውን ይወረሳል ማለት አይደለም። እጣው የሚወረሰው ዕጣው ከወጣ በኋላ ዕጣው የወጣለት ሰው በሕይወት ባይኖር ቤተሰቦቹ በፍርድ ቤት አሳውጀው የሟችን እጣ መውረስ ይችላሉ። ስለዚህ የሟች ቤተሰቦች አስፈላጊውን ቁጠባ በሟች ስም በተከፈተው ዝግ የቁጠባ ሂሳብ እየቆጠቡ እጣ እስኪወጣ ይጠብቃሉ። እጣው ሲወጣ የወራሽነት መብታቸውን በፍርድ ቤት አስከብረው መውረስ እንደሚችሉ አቶ አውራሪስ ይናገራሉ።

አድራሻ፡-

ስልክ የቢሮ ኃላፊ 0115575790
የጽ/ቤት ኃላፊ 0115575741
የሞ/ኮ/ስ/ዘ/ም/ቢ/ኃላፊ 0115575748
የታ/ጉ/ዘ/ም/ቢ/ኃላፊ 0115575608

የህግ ማ/ዘ/ም/ቢ/ኃላፊ 0115575604
Facebook page: Addis Ababa revenue bureau
Web site: http//aarevenue.gov.et
P.O. Box 27400 code 1000

የላቀ ገቢ ለአዲስ አበባችን ብልፅግና!

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# ‹‹የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች የተፈጠረውን ችግር በመቀራረብ እንጂ በመለያየት አይፈቱትም››

ዶክተር ዳባ ጨፋ
የሕግ አማካሪና ጠበቃ

ማህሌት አብዱል

በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን ግንደበረት ወረዳ ነው ተወልደው ያደጉት። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን ጊፕሬ በተባለ ትምህርት ቤት የተማሩ ሲሆን ሁለተኛ ደረጃ ግንደበረት እና የቀድሞው አምቦ መስከረም ሁለት ትምህርት ቤቶች ተከታትለዋል። አምቦ እርሻ ኮሌጅ ገብተውም በእርሻ መምህርነትና አጠቃላይ እርሻ ትምህርት መስክ ሰልጥነዋል። አምቦ ቢዝነስ ኮሌጅ በሕግ ዲፕሎማዎችን አግኝተዋል። ከዩኒቲ ዩኒቨርስቲ ገብተው የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን እንዲሁም አምቦ ዩኒቨርስቲ ደግሞ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በሕግ የትምህርት መስክ ተቀብለዋል። በመቀጠልም ሲድስታር በሚያስተባብረው በቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን ተጨማሪ የማስተርስ ዲግሪያቸውን እንዲሁም ገሊሳ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ በሊደርሺፕና ማኔጅመንት የትምህርት ዘርፍ የዶክትሬት ዲግሪያቸውን ሠርተዋል።

ለረጅም ዓመታት በተለያዩ መንግሥታዊ ተቋማት ውስጥ አገልግለዋል። ከእዚህም መካከል በኦሮሚያ ፖሊስ አምቦ ከተማ የፖሊዝ አዛዥ ሆነው ለአራት ዓመታት እንዲሁም በምዕራብ ሸዋ ዞን ማኅበራት ማደራጃ መምሪያና በትምህርት ቢሮ ለአራት ዓመታት የሕግ ባለሙያነትና ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ሆነው መሥራታቸው ይጠቀሳል ። ካለፉት 13 ዓመታት ወዲህ ደግሞ በፌደራልና በክልል ፈቃድ አግኝተው በሕግ አማካሪነትና ጥብቅና ሥራ ላይ እየሠሩ ይገኛሉ። በእነዚህ ዓመታትም በሕወሓት በግፍ ለታሰሩ የፖለቲካ እስረኞችን ጥብቅና በመቆም በርካቶችን ነፃ ያወጡት እኚሁ ሰው በዚህም ሽብርተኞችን ትረዳለህ በሚል ዘብጥያ ወርደው ለሦስት ወራት በስቃይና በእንግልት ቆይተዋል። ዶክተር ዳባ ጨፋ የዛሬው የዘመን እንግዳችን ናቸው። በወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳይ ያደረግነውን ቆይታ እንደሚከተለው ይዘን ቀርበናል።

**አዲስ ዘመን፡- ለእስር የዳረገዎትን አጋጣሚ ያስታውሱንና ውይይታችንን እንጀምር?**

**ዶክተር ዳባ፡-** እንደምታስታውሽው ለውጡ ከመምጣቱ በፊት በኦሮሚያ የተለያዩ ቦታዎች ሕዝባዊ ተቃውሞ ተነስቶ ነበር። ኅብረተሰቡ ከ27 ዓመታት የሕወሓት የጭቆና ቀምበር ለመላቀቅ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ሲያደርግና ጥያቄዎችንም ሲያነሳ ነበር። በእነዚህ ጥያቄዎች ውስጥ እኔም ተሳትፌ ነበር። የነበረው ሥርዓትና አስተዳደር ዘይቤ ኅብረተሰቡን ያማከለ አልነበረም። እስራት አለ፤ ግርፋት አለ። ኅብረተሰቡ እምቢታውን ሲገልፅ እኔም ጩኸቱን ተጋርቻለሁ። በተጨማሪ ደግሞ በወቅቱ በኦሮሚያ ውስጥ በርካታ ወጣቶች ታስረው ነበር። በመሆኑም ለ264 የኦሮሚያ ወጣቶች ነፃ የጥብቅና አገልግሎት በ28 መዝገብ ላይ የሽብር መዝገብ ቆሜ 182 የሚሆኑትን ነፃ አውጥቻለሁ። ያንን ክርክር በማካሂድበት ሰዓት በወቅቱ የነበሩት የወያኔ ሰዎች ለአሸባሪ የቆመ ሽብርተኛ ነው በማለት ከችሎት ወስደው ለሶስት ወራት ጦላይ አስረውኛል። ለሶስት ወራት ጦላይ በስቃይ ካቆዩኝ በኋላ ያለምንም ክስና አንድም ቀን ፍርድ ቤት ሳያቀርቡኝ ነው በነፃ የለቀቁኝ። በወህኒ በቆየሁባቸው ጊዜ ድንጋይ መሬት ላይ ነበር እተኛ የነበረው፤ የሚጠጣ ውሃ አልነበረም። በዚህ ምክንያት ለከፋ የኩላሊት ሕመም ተዳርጌ ነበር። ለአንድ ወር ያህል ደም ነበር ስሸና የነበረው። በኋላ በግሌ ባደረኩት ሕክምና ማገገም ችያለሁ ።

**አዲስ ዘመን፡- ለታሰሩበት የተሰጠዎት ምክንያት አልነበረም?**

**ዶክተር ዳባ፡-** በግሌ ምንም አልተነገረኝም፤ ግን የታሰርነውን ሁሉ በጅምላ ሕዝብ ለአመፅ ቀስቅሳችኋል፤ ወጣቱ ለመንግሥት ተገዢ እንዳይሆን አነሳስታችኋል ይሉን ነበር። በተለይም በወቅቱ አነጋጋሪ የሆነው የአዲስ አበባ ማስተር ፕላን ጉዳይ ክልል ከተሞች ድረስ ዘልቆ ለነበረው የተቃውሞ እንቅስቃሴ እኛ እንዳስተባበርን አድርገው ነበር ሲናገሩን የነበረው። እርግጥ ነው የሕዝብ ጥያቄ ነበር፤ ሆኖም ነውጥና ረብሻ ይደረግ የነበረው በእዛው በመንግሥት መዋቅር ውስጥ በነበሩ ሰዎች መሪነት ነው። ሕዝቡ እንዳደረገው ለማስመሰል የተለያዩ ጥረቶች ይደረግ ነበር። ለምሳሌ በወቅቱ ኦነግ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሽብርተኛ ተብሎ ተፈርጀ ነበር፤ የኦነግ ባንዲራ የግለሰቦች ቤት ውስጥ ያስቀምጡና የብርበራ ትዕዛዝ አውጥተው ‹‹የኦነግ ባንዲራ ተገኝቶብሃል›› ተብለው በርካቶች እንዲታሰሩ ተደርገዋል። እኛም ይህንን ድርጊታቸውን ነበር የተቃወምነው።

**አዲስ ዘመን፡- ከዚህ ተነስቶ የለወጡ መምጣት በሰብዓዊና ዲሞክራሲ መብቶች መከበር ላይ ምን ውጤት አስገኝቷል ብለው ያምናሉ?**

**ዶክተር ዳባ፡-** እንግዲህ ያንንም ሆነ አሁን ያለውን መንግሥት በደንብ እንደሚያውቅ ሰው አንፃራዊ የሆነ ለውጥ እንዳለ አምናለሁ።ፍፁም የሆነ ለውጥ መጥቷል ባይባልም መሻሻል አለ፤ ይህንን መካድ አይቻልም። መሻሻሎቹ ቀጠሉ፤ አልቀጠሉ የሚለው ነገር ሌላ ጉዳይ ነው። ለምሳሌ በፊት ሰው በአደባባይ ወጥቶ መናገርም ሆነ ሃሳብ መግለፅ አይችልም ነበር። በመንግሥት መዋቅሩ ውስጥ ያለው አካል እንኳን እንደልቡ ሃሳቡን እየገለፀ የሚሰራበት ምህዳር አልነበረም። እነዚያ ነገሮች ተሻሽለዋል። የተገኙ መሻሻሎች እንዳሉ ሆነው የሚቀሩ ብዙ ነገሮች አሉ። ችግሮቹ በአብዛኛው ካለፈው ሥርዓት የተሻገሩ ናቸው። በሌላ በኩልም ሰዎች ሃሳባቸውን እንዳይገልፁ አፍኖ ይዞ የነበረው ሥርዓት ነፃ ሲለቀቅ ሌላ ችግር ፈጠረ። ታፍኖ የነበረው ሁሉ አሁን ላይ መረን ሆነ። ከፋፋይ የሆኑ ሃሳቦች ተፈጠሩ፤ ቀድሞ የነበረው ችግር ራሱ ሌላ አዲስ ችግር ወለደ። አሁን እንደምናየው የሕዝብ አስተሳሰቦች ተከፋፍለዋል።

**አዲስ ዘመን፡- የሕዝብ አስተሳሰቦች ተከፋፍለዋል ሲሉ ምን ማለትዎ ነው?**

**ዶክተር ዳባ፡-** ለምሳሌ አሁን ላይ ሕዝቡ በሶስት ሃሳቦች የተከፈለ ይመስለኛል። አንደኛው በአንድ ሀገር የሚያምንና ከ80 በላይ የሚሆኑ ብሔር ብሔረሰቦች በእኩል የሚኖሩባት አንዲት ኢትዮጵያ መኖሯን የሚያምነው የኅብረተሰብ ክፍል ሲሆን፤ ሁለተኛው ኢትዮጵያ አንዲት ሀገር ብቻ የሚለውን ሃሳብ በመቀበል ብሔር ብሔረሰቦችን የማያከብር አቋም የሚያራምድ ነው። ሶስተኛው ደግሞ ብሔርን ወይም ክልልን እንደሀገር የሚቆጥር ሲሆን ይህ ደግሞ ለኢትዮጵያዊነት ቦታ የማይሰጥና ኢትዮጵያ የምትባለውን ሀገር በዓይናችን አንይ የሚሉ ናቸው። ለምሳሌ ወደ ኦሮሚያ ክልል ብንሄድ ኦሮሚያ ሀገር እንደሆነች፤ ኢትዮጵያ ራሱ ኦሮሚያ እንደሆነች የሚናገሩ ሰዎች አሉ። እነዚህ ሁለት ሃሳቦች ጫፍ የረገጡ ናቸው። ሁለቱም ሃሳቦች የዘነጉት ነገር አለ። የራሳቸውን ብሔር ከፍ አድርገው ሲያወሩ የሌላውን ቢያንስ በልኩ ማሞገስ አለባቸው። እነዚህን ፅንፍ የረገጡ ሃሳቦችን በዋናነት የሚያራምዱት በአብዛኛው ሊሂቃን የምንላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ናቸው። ማኅበረሰቡ ውስጥ ግን እንዲህ አይነቱን ነገር እምብዛም አናገኘውም። ከዚያ ይልቅም በመንግሥት መዋቅር ያሉ ሰዎችም ሊኖሩበት እንደሚችሉ እገምታለሁ።

በአጠቃላይ ከዚህ ቀደም ታጭቆና ታፍኖ የነበረው ስሜት መረን ሲለቅ እንዲህ አይነት መከፋፈሎችን ፈጠረ። ስለዚህ እነዚህ ፅንፍ የረገጡ አስተሳሰቦች ወደኋላ እንድንመለስ እያደረጉን ነው። ምክንያቱም ምንም እንኳን ከ80 በላይ ብሔረሰቦች ቢኖሩንም ዓለም አቀፍ ኅብረተሰብ የሚያውቀን በኢትዮጵያ ነው። ኦሮሚያም ሆነ ትግራይ አልያም አማራ ክልል የሚታወቁት በኢትዮጵያ እንጂ ራሳቸውን ችለው እንደወጡ ሀገራት ተደርገው አይደለም። ይህም ቢሆን ግን አሁን ድረስ ትግራይን፤ ኦሮሚያንና አማራን ‹‹ሀገር›› የሚሉ ሰዎች አሉ። ይህንን አስተሳሰብ የሚያራምዱ የኅብረተሰብ ክፍሎች ኢትዮጵያን በዓይን ማየት የማይፈልጉ ናቸው። ይህም ለዘመናት የኖርንበት ተቻችሎና ተከባብሮ የመኖር እሴታችን ለፅንፈኝነት ቦታውን እንዲለቅ አደረገ። አሁን ላይ ኅብረተሰቡ እርስ በርስ መቀባበል፤ መከባበርና በጋራ ለመኖር የማይፈልግበት ሁኔታ ተፈጠረ። በነገራችን ላይ ይህ የልዩነት አስተሳሰብ ወደ



ፎቶ፡ ፀሐይ ንጉሴ

አንድ መሰብሰብ ባለመቻላችን ነው ሀገር እየታመሰች ያለችው። ምክንያቱም ሀገር ማለት ኦሮሚያ ወይም አማራ ክልል ማለት አይደለም፤ ሀገር ማለት ኢትዮጵያ ናት። ይህ ሆኖ ሳለ ሃሳቦች ሲሸነሸኑ ታሪኮቻችን ትርክት ሆኑ፤ የነበረ እንዳልነበረ ተተረከ፤ ያልነበረ እንደነበረ ተነገረ። ሰው እውነቱን መዋጥ አቃተው። ውሸቶች እየተነባበሩ ሲሄዱ የእኛን ታሪክ ዋጡት። ለምሳሌ የእኛ ታሪክ ተብሎ ከሚጠቀሱ ነገሮች አንዱ አብሮ ተቻችሎ መኖር ነው። እነዚህን አስተሳሰቦች መሰብሰብ ያለመቻላችን ነው እንደሀገርና እንደ አንድ ሕዝብ እንዳንረጋጋ ያደረገን።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያዊነት ለእርስዎ ምንድን ነው?**

**ዶክተር ዳባ፡-** ለእኔ ኢትዮጵያ ሀገር ናት። እኔ ከኢትዮጵያ ውጭ ሌላ ሃገር የለኝም። ኢትዮጵያ ሃገሬ ብቻ ሳትሆን የትም ብሄድ የምታወቅባት መለያዬ ናት። እንደ አንድ ብሔረሰብ ደግሞ ብሔሬ ኦሮሞ ነው። ትውልዴም ኦሮሚያ ክልል ነው ፤ሃገሬ ግን ኢትዮጵያ ናት። ኢትዮጵያ ለእኔ ብቻ ሳትሆን የ80 ብሔር ብሔረሰቦች እናት ናት። አቅፋ የያዘችን እሷው ናት። እኔ የሚሰማኝም ሆነ የማውቀው በዚያ ልክ ነው። በነገራችን ላይ በአሁኑ ወቅት በሃሳብ ፈርሰን በአካል ብቻ ነው ያለነው። እሱንም ጭምር ለማጥፋት ነው እያተራመሱን ያሉት። እኔ ተማሪ ሆኜ የነበሩት ዘፈኖች ስለሃገር ፍቅርና ስለተቃራኒ ፆታ ፍቅር ብቻ ነበር።የሕዝቡ ሃገራዊ ስሜት ተመሳሳይ ነበር። አሁን ላይ ያሉት ዘፋኞች ግን ብሔር ላይ መንጠልጠላቸው ሳይበቃቸው መንደርና ቀበሌ ድረስ ወርደው በመዝፈን ሃገራዊ ስሜት እንዲጠፋ አድርገዋል። እነዚህ ዘፈኖች ሕዝቡ ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ ቀላል አይደለም። ኢትዮጵያ የምትባለውን ሃገር በሃሳብ ሸረሸሯት። አብሮ የመኖር መስተጋብራችን ጠንካራ እንዲሆን ኪነ-ጥበቡ የነበረው ሚና ቀላል አልነበረም። አሁን ደግሞ አብሮነቱ እንዲሸረሸርም ከፍተኛ አስተዋጽዖ እያበረከተ መሆኑን ሕዝቡ የተገነዘበው አይመስለኝም።

በመሠረቱ የ27 ዓመቱ ትውልድ ልዩነቱን ብቻ አስቦ እንዲኖር ተደርጎ ነው የተቀረፀው። ልዩነትን አንግበው መቀራረብን እንዲያመጡ ይደረግ የነበረው ጥረትም በእኔ እምነት ከንቱ ድካም ብቻ ነበር። አሁንም ቢሆን የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች የተፈጠረውን ችግር በመቀራረብ እንጂ በመለያየት አይፈቱትም። ችግር የሚፈታው አንድ ላይ በመሆን ነው። ሁሉም በየራሱ ክልል አጥር ስር ተቀምጦ ችግር አይፈታም። ምክንያቱም ከችግሩ በላይ የአብሮነት ስሜቱ በጣም ረጅም ነው። ስለዚህ በጋራ ሆነን እንደቀድሞ ተባብረን ነው ፅንፈኝነት ያጣቡንን ሃገር የማፍረስ ሴራ መታገል የምንችለው።

**አዲስ ዘመን፡- ከዚህ ቀደም በፍትሕ ሥርዓቱ ላይ የነበረው የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት አሁን ላይ ሙሉ ለሙሉ ቀርቷል ማለት ይቻላል?**

**ዶክተር ዳባ፡-** እንግዲህ በ27 ዓመታት ውስጥ ሦስቱ የመንግሥት መዋቅሮች የድርሻቸውን በአግባቡ እንዳይወጡ በግልፅ ነበር የፖለቲካ ጣልቃገብነት ሲደረግባቸው የነበረው። ለዚያም ነው የሕዝብ ማዕበል ተነስቶ ሥርዓቱን ከመነቅነቅ እስከ ማፍረስ የደረሰው። አሁን ላይም ቢሆን ችግሩ ሙሉ ለሙሉ ተቀርፏል ማለት አይቻልም። ምክንያቱም አሁንም ቢሆን ሕግ የሚያወጣው ፖለቲከኛው ነው፤ ይህም የሆነው ያሸነፈው የፖለቲካ ፓርቲ መንግሥት ስለሚያቋቁም ነው። የዚህ ዘመን ችግር ሕጉን የሚመራው ፖለቲካው በመሆኑ ነው። እንደድሮው በቀጥታ ጣልቃ ባይገባም ፖለቲካው ሕጉን ተቆጣጥሮታል። መሆን የነበረበት ግን ሕጉ ፖለቲካውን መምራት ይገባው ነበር። ፓርቲውም ቢሆን መንግሥት ሲመሠርት ይገዛኛል፤ እገዛበታለሁ ብሎ ያወጣውን ሕግ ማክበር አለበት። የፍትሕ ተቋማት ነፃነታቸው ተጠብቆ እንዲሠሩ ማድረግና ማክበር ይገባዋል። ፖለቲካው ለወጣው ሕግ የማይገዛ ከሆነ ፖለቲካው ራሱ የተረጋጋ አይሆንም።

**አዲስ ዘመን፡- ከፖለቲካው ባሻገር ብሔርተኝነቱም በፍትሕ ተቋማት ዘልቆ መግባቱ ፍትሕ እንዳይሰፍን ያደረገው መሆኑን አንዳንድ የኅብረተሰብ ክፍሎች ይናገራሉ። እርስዎ በዚህ ሃሳብ ይስማማሉ?**

**ዶክተር ዳባ፡-** እኔ በበኩሌ በብሔረሰብ ዳኝነት ላይ የተፈጠረ ችግር አላየሁም። ግን እንደነገርኩሽ

### ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ



ፖለቲካው በፍትሕ ሥርዓቱ ላይ ዘልቆ በመግባቱ ከአንዳንድ ግለሰቦችና ኢንቨስተሮች ጋር ችግር ያለባቸው ፖለቲከኞች የፍትሕ ሥርዓቱ እንዲዛባ ሊያደርጉ ይችላሉ። ምክንያቱም አሁንም ፖለቲካው ነው ሕጉን እየመራው ያለው።ይህም ሲባል ለምሳሌ በፍትሕ ሥርዓት ያለፈ አንድ ተጠርጣሪ ፍርድ ቤት ነፃ ብሎት ካበቃ በኋላ በፖለቲካ ባለስልጣናት ትዕዛዝ እንዳይፈታ የሚደረግበት ሁኔታ አለ። እኔ እንደእውነቱ ከሆነ እገሌ የእገሌ ብሔር አባል ነው ተብሎ ነፃ የሚለቀቅበት ወይም የሚታሰርበት ሁኔታ በግሌ አልገጠመኝም። ይሁንና ካለፈው ሥርዓት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ኢንቨስተሮች አሉ፤ በተለይም በወቅቱ ከነበሩት የሕወሓት ሰዎች ጋር ባላቸው ግንኙነት በማጭበርበር ያፈሩት ሃብት ሊኖር ይችላል። እነሱንም ቢሆን ሕግ እንጂ ሊዳኛቸው የሚገባው ፖለቲካው አይደለም። ይህም ሲባል እነዚህ ሰዎች የመደመጥ፤ መብታቸውን የማስከበር ፤ አቤቱታቸውን የማቅረብ ፤ ውሳኔ የማግኘት መብት አላቸው።

እንዳልኩሽ ግን ወደ ፍርድቤት የሚሄዱ ጉዳዮች የፖለቲካ ትርጉም ይሰጣቸዋል ወይም በፖለቲካው ይቃኛሉ። አልያም ከአመለካከት ችግር የመጣ ተደርጎ በማካተት ፍትሕ እንዳያገኝ ይደረጋል። ስለዚህ በእኔ እምነት በፍትሕ ተቋማት ያለው የብሔር ውግንና ሳይሆን የፖለቲካ ውግና ነው። እርግጥ ነው አንድ ቦታ ላይ በፖለቲካ አመለካከት እየተባለ ሳይጣራ ታስረው ለረጅም ጊዜ የሚቆዩ ዜጎች አሉ። ለምሳሌ ሶስት ወርና አራት ወር ምርመራቸውን ማጓተትና ፍትሕ ሳያገኙ እንዲቆዩ የሚደረግበት አጋጣሚ አለ። ይህም የሆነው አስቀድሜ እንዳልኩሽ ፖለቲካው ሕጉን ስለሚመራው ነው። ፍርድ ቤት የለቀቃቸው ሰዎች መልሰው ሲታሰሩ እናያለን። በመሆኑም ይህንን ውዝግብ ማርገብ የሚቻለው ፖለቲካው ራሱ ለሕጉ ሲገዛና በሕግ ሲመራ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ማንኛውም ዜጋ ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሶ የመሥራት፤ የመኖርና ሃብት የማፍራት መብት ሕገ-መንግሥቱ ያጎናፀፈው ቢሆንም የክልል ሕጎች ግን ከሌላ የሃገሪቱ አካባቢ የመጡ ዜጎችን የሚያገልበት ሁኔታ አለ። እርስዎ ይህ ዓይነቱ የሕግ መጣረስ ምን ችግር አምጥቷል ብለው ያምናሉ?**

**ዶክተር ዳባ፡-** የእኛ ሃገር የብሔር ብሔረሰቦች ሰነድ ሕገ-መንግሥቱ ነው። ሕገ-መንግስቱ ላይ የተቀመጡና የሕገ-መንግሥቱ ዋና ዋና ምሰሶዎች ተብለው የሚጠቀሱ ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች አሉ። ክልሎች የሚያወጧቸው ሕጎች ሕገ-መንግሥቱን ሳይጣረሱ መውጣት አለባቸው። ተጣርሰው ከወጡ ከሆነ ተቀባይነት የላቸውም። ይህንን በሚጣረስ መልኩ ሕግ ያወጣ ማንኛውም የመንግሥት አካል ተጠያቂ ነው። ይህንን ደግሞ ሕገ-መንግሥቱ በግልፅ አስቀምጦታል። በዚህ ረገድ ተጣርሰው የወጡ ብዙ ሕጎችን ማንሳት ይቻላል። ለዚህ ደግሞ የመሬት አዋጅ፤ የተለያዩ የሙያ ማኅበራት አዋጅ መጥቀስ እንችላለን። ለምሳሌ የእኛ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበርን የሚመለከተው አዋጅ ከሕገ-መንግሥቱ ድንጋጌ ያፈነገጠ ሃሳብ ይዞ ነው የወጣው። ሕገ-መንግሥታችን መደራጀት መብት ነው ብሎ ነው እንጂ ግዴታ ነው ብሎ አልደነገገም። የጠበቆች ማኅበር አዋጅ ግን ‹‹ማንኛውም ጠበቃ የጥብቅና ፍቃድ ሲያወጣ የመደራጀት ግዴታ አለበት›› ብሏል። ይህ ፈፅሞ ከዋናው ሕጋችን የተጣረሰ ነው።

በተመሳሳይ የመሬት አዋጁም የሕግ መጣረስ አለበት። አንድ ሰው መሬት 15 ዓመት ከተቀመጠበት፤ ሃብት ካፈራበት በኋላ ሕገወጥ ተብሎ በግሬደር የሚታረስበትና ግለሰቡም የሚፈናቀልበት ሁኔታ አለ። በዚህ መልኩ የብሔረሰብንና የብሔርን መብት የሚጣረሱ በርካታ ሕጎችና አዋጆችን መጥቀስ እንችላለን። በመሠረቱ በትክክል ሳይጣረሱ የወጡ ሕጎችም ቢሆኑ ወደታች በተሄደ ቁጥር አስፈፃሚ አካላት በሚፈጥሩት ችግር ምክንያት ተዛንፈው የሚቀርቡበት ሁኔታ አለ። ግለሰቦች በሚፈጥሩት ችግር፤ ትንኮሳ በማድረግና አንዱ ሌላውን እንዲጠራጠር በማድረግ የሚፈጠሩ ነገሮች አሁን ያለንበትን ችግር መንስኤ ሊሆን ይችላል ።

ሌላው አሁን ላለንበት ችግር ዋነኛ ምክንያት ነው ብዬ የማስበው በየትኛው የመንግሥት ኃላፊነት ላይ የተቀመጠ ጠቅላይ ሚኒስትሩንም ጨምሮ የሚፈፅመው ስህተት ወንበሩ ላይ በመቀመጡ ያጠፋው ጥፋት ተብሎ መወሰድ ነው እንጂ ያለበት ከእሱ በስተጀርባ ያለው ብሔረሰብ ተጠያቂ ሊሆንም፤ ሊወቀስም አይገባም። አማራ ወይም ኦሮሞ ስለሆነ ተብሎ ምንም የማያውቀውን ማኅበረሰብ ከአጥፊው ጋር በማላተም የሚፈጠረው ችግር ነው አስቸጋሪ እየሆነ ያለው፤ ትልቁ እሳት ይሄ ነው። አቢይ ጠቅላይ ሚኒስትር ነው፤ መጠየቅ የሚችለው ራሱ በስልጣን ዘመኑ በሠራቸው ሥራዎች ነው እንጂ ወክሎ የመጣውን ብሔረሰብ ሊሆን አይገባም። መንግሥትም ቢሆን ትኩሳቱን ማብረድ ያልቻለው ሁሉንም ነገር በብሔር መነፅር የሚያይና የሚለካ በመሆኑ ነው። ይህም የብሔር ብሔረሰቦች አንድነት እንዲጠፋና እርስበርስ ጥርጣሬ ውስጥ እንዲገቡ ያደርጋል። በአጠቃላይ ዋናው ሕጋችን ሕገ-መንግሥቱ ነው ብለናል፤ ከዚያ በኋላ የሚወጡ ሕጎች የሚጣረሱ ከሆነ ዋጋ የላቸውም። ክልሎች የሚያወጡት ሕግ ሌላውን በሚጎዳ፣ በሚነቅፍና ዝቅ በሚያደርግ መልኩ የሚወጣ ከሆነ ኢ-ሕገ መንግሥታዊ ነው።

ለምሳሌ አንዳንድ ቦታ ላይ ተደራጅተው መሬት ለመውሰድ የሚጠየቁ ነገሮች አሉ፤ መታወቂያ ይጠየቃል፤ ነዋሪነት ይጠየቃል። መሬት ወስዶ ቤት ሠርቶ ለመኖር የዚያ አካባቢ ተወላጅ መሆን ብቻ መስፈርት ሊሆን አይችልም፤ ሰው መሆን በቂ ነው። አንተ ከዚያኛው ክልል ነህ እዚህ መኖር አትችልም የሚባለውን ነገር ሕገ-መንግሥቱን የሚጋጭ ነው። ይህ አይነቱ አካሄድ ኢ-ሕገመንግሥታዊ ከመሆኑም ባሻገር አብሮነትንም የሚሸረሽር ነው። እንዳነሳሁልሽ የእኛን የጠበቆች ማኅበር አዋጅ ጉዳይን ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ለማቅረብ ዝግጅት እያደረግን ነው። የሚገርመው ኦሮሚያ ላይ ብቻ 1ሺ700 ጠበቆች አሉ፤ እኔ የማኅበሩ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል ነኝ። ከዚህ ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆነው በፌደራል ደረጃ የሚሠራ ነው። ተደራጅቶ መሥራት መብት ነው፤ ሕገ-መንግሥቱ ግዴታ አላደረገም።ይሁንና በግዴታ ካልተደራጀን የጥብቅና ፈቃዳችን እንደሚሰረዝ ነው የተነገረን። እንግዲህ እኛ የሕግ ባለሙያዎች ሆነን ሳለ ሕግ ተጣርሶ ኢ-ፍትሐዊ ነገር ከተፈፀመብን፤ ሌላው ሕዝብ ላይ ምንአይነት ግፍ ሊሠራ እንደሚችል መገመት አይከብድም።

**አዲስ ዘመን፡- ሰሞኑን ጠቅላይ ሚኒስትሩ በምክር ቤት ተገኝተው ካነሷቸው ዋና ዋና ችግሮች መካከል የፍትሕ ሥርዓቱ በተለይ ሕግ ተርጓሚዎቹ ላይ እየተስፋፋ የመጣው የሌብነት ወንጀል ነው። በእርስዎ እይታ ይህ ችግር በተጨባጭ አለ? ካለስ በምን መልኩ ነው ከዚህ ችግር መውጣት የሚቻለው?**

**ዶክተር ዳባ፡-** በጣም ከባድ ጥያቄ ነው፤ ችግሩም ከባድ ነው። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዚህ ጉዳይ ላይ አፅዕኖት የሰጡበት ምክንያት አላቸው። እኛም የምናውቀው እውነት ነው። በዚህ ዘርፍ ላይ በጣም ትልቅ የሚባል ችግር ነው ያለው። ችግሩ እንዳይፈታ ያደረገው ደግሞ በቦታው ላይ እነዚህን ሰዎች የሚያስቀምጠው ራሱ መንግሥት መሆኑ ነው። የሚያስቀምጣቸው በራሱ መስፈርትና መለኪያ ነው። እንደእኔ እይታ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከገለፁትም በላይ በጣም ውስብስብ የሆነ ችግር ነው ያለው። በነገራችን ላይ ሌብነት ማለት በቀጥታ ገንዘብ ከመሰብሰብ ጋር ብቻ አይገናኝም። ለምሳሌ የሥራ መግቢያ ከጠዋቱ 2 ሰዓት ከ30 ሆኖ ሳለ እንዲሁም ፍርድ ቤት ሥራን የሚሠራው በቀጠሮና በሰዓት እንደሆነ እየታወቀ አንድ ዳኛ ባለጉዳይን 4፡00 ሰዓት ቀጥሮ እሱ 5፡00 ሰዓት ይመጣል። ይሄ አንዱ ሌብነት ነው። እነዚህ ባለጉዳዮች ምንአልባትም ከጋምቤላ ወይም ከኢሉአባቦራ ሁለትና ከዚያ በላይ ቀናት መንገድ ላይ አድሮ መጥቶ ይሆናል ፍርድ ቤት የተገኘው። መዝገቡ ላይ የሚሰጡ የዳኝነት አሰጣጥ ሂደቶች ናቸው። መዝገቦችን ያለገደብ አራትና አምስት ጊዜ ለምርመራ መቅጠር ይህም ሌላው ሌብነት ነው። ሰዎችን በዘመድ ሲጠይቋቸው በጓሮ ተገናኝተው ፍትሕ ማዛባት በስፋት ይታያል። በቀጥታ በገንዘብም ተደራድሮ የሚደረግ ነገር ሊኖር ይችላል። እኔ ራሴ ሥራዬም ሆነ ውሎዬ ፍርድ ቤት ነው፤ ብዙ የሚደርስብኝ ግፍ አለ። በተለይ መዝገብ ጠፋ በሚልና ቀጠሮ በማብዛት እኔንም ሆነ ደንበኞችን የማንከራተት ሁኔታ በተደጋጋሚ ያጋጥመኛል።ይህ ሁኔታ ደግሞ ደንበኞቼ በእኔ፣ በፍትሕ ሥርዓቱና በመንግሥት ላይ ያላቸውን እምነት ጭምር እንዲያጡ አድርጓል።

በአጠቃላይ አሁንም ቢሆን የፍትሕ ተቋማት ካልተጠናከሩ ችግሩ የበለጠ እየከበደ ነው የሚመጣው። በነገራችን ላይ ኅብረተሰቡን በቅንነት ማገልገል የሚፈልጉ ጎበዝና ጠንካራ ዳኞች፣ አቃቤ ሕጎችና ጠበቆች አሉ። ይሁንና በሐቅና በቅንነት የሚሠሩ ሰዎችን ብዙ ጊዜ መንግሥት አይፈልጋቸውም። ምክንያቱም መንግሥት የሚሠሩ ሳይሆን የሚፈልጋቸውን ሰዎች መልምሎ ነው የሚያመጣው። የሚሠሩትን ሰዎች እኛ እናውቃቸዋለን። የአቅም ችግር ኖሮባቸው አይደለም። ይልቁንም በመንግሥት ተመልምለው የሚመጡ ሰዎች ከፍተኛ የሆነ የስነ-ምግባር ችግር እንዳለባቸው በተግባር ታይቷል። ለምሳሌ ጠበቆች ከዳኛው በላይ በምንሠራው ሥራ ተከፋይ ሆነን ሳለ ጥቂት የማይባሉት ዳኞች በጣም ቅንጡ በሆነ ቤት ሲኖሩ ነው የሚታየው። ይህንን ያህል ገንዘብ በየወሩ መንግሥት ከሚከፍለው አግኝቶ ነው ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው የሚመስለኝ። ምክንያቱም ዳኛ የመንግሥት ቅጥረኛ እንጂ ነጋዴ ባለመሆኑ ነው።

ስለዚህ መንግሥት የፖለቲካ ሥራውን የሚያበላሽበት ትልቁ ችግር የፍትሕ ተቋማት በሥርዓት እንዲመራ አለማድረጉ ነው። የሚሾሟቸው ሰዎች ለእሱ ፖለቲካ ስለተመቹ ሳይሆን ፍትሕን ማስፈን እስከቻሉ ድረስ የማይፈልጋቸውንም ቢሆን አምጥቶ ማሠራት ይገባዋል። ምክንያቱም ጉዳዩ የአንድ ፖለቲካ ፓርቲ ሳይሆን የሃገር ጉዳይ በመሆኑ ነው። እውነቱንም ለመናገር በፍትሕ ተቋማት ላይ ባለው ስር የሰደደ ብልሹ አሠራር ምክንያት ተስፋ እንድቆርጥ ተደርጌያለሁ። በተለይ ክልሎች ላይ ፍትሕ የሚባል ነገር የለም። ሕዝቡ ከገጠር ቀበሌ ለቀናት በእግርና በፈረስ ተጉዞ ዞን ላይ ፍትሕ ለማግኘት አምኖ ቢመጣም ፍትሕ እያገኘ አይደለም። መዝገብ ጠፋ እየተባለ ሕዝብ መከራ እንዲያይና እንዲያለቅስ እየተደረገ ነው። ስለዚህ መንግሥት የማይፈልጋቸውንም ሰዎች ቢሆን ለሃገር ሕልውና እና ለሕዝብ መብት ሲባል መልሶ ማሠራት ይገባዋል።

**አዲስ ዘመን፡- በተለይም ቀበሌ፤ ወረዳና ክፍለ ከተሞች እንዲሁም የፍትሕ ተቋማት ላይ መዝገብ ጠፋ እየተባለ ተገልጋይ የማንከራተቱ ባህል አሁን ላይ በእጅጉ ተለምዷል። ለመሆኑ ይህንን ችግር የመዝገብ አያያዙ ነው ወይስ ሆን ተብሎ ለሌብነት ሲባል የሚደረግ ተግባር ነው?**

**ዶክተር ዳባ፡-** እውነት ነው፤ ይህ ችግር በጣም ከባድ እየሆነ ነው የመጣው። ሆን ተብሎ መዝገብ ጠፋ ትባያለሽ፤ እኔም ገጥሞኝ ያውቃል። ጠፋ ይሉኝና አልበገር ስላቸውና ብዙ ሳስጨንቃቸው ከሰማይ ይውረድ፤ ከመሬት ይፍለቅ በማላውቀበት ሁኔታ አቆይተው ‹‹አግኝተነዋል›› ይሉኛል። ይሄ ግልፅ የሆነ ሌብነት ነው። ይህ አይነቱን ሌብነት ከወዲሁ በእንጭጩ ካልቀጨነው ወደ ነውጥ ይሄዳል። ሕዝባዊ አመፅ ያመጣል። ሰው መብቱን ከተነፈገ ዝም ብሎ ቁጭ አይልም፤ የትና ማን እንዳጠፋበት ያውቃል፤ ከዚያ በኋላ ሥርዓት አልበኝነት ይመጣል። አንዱ በሌላው ላይ ይነሳል፤ መገዳደል ይከሰታል። ይህም የሚሆነው ደግሞ ከአመራር ችግር ነው። ልክ እንደፍርድ ቤቱ በየክፍለከተማው፣ ወረዳውና ቀበሌ ያሉ አመራሮች በዚያው ልክ ሌቦች ናቸው። መዝገብ ይሰርቃሉ፤ የፍርድ ቤት ውሳኔን ያስገለብጣሉ፤ ምክንያቱም እጃቸው ረጅም ነው። በተለይ አዲስ አበባ ላይ የሚታየው የአመራር ብቃት ማነስ ሳይሆን የስነ-ምግባር ችግር ነው። ይህም ሥርዓቱ እንዳይረጋጋ ያደርጋል። ሥርዓቱ ካልተረጋጋ ደግሞ ብዙ የሚበላሹ ነገሮች አሉ።

**አዲስ ዘመን፡- ከሁለት ዓመታት በላይ የዘለቀው የፀጥታ ችግር በመስፋቱ ላይ ምን አይነት ተግዳሮት ፈጥሯል ብለው ያምናሉ?**

**ዶክተር ዳባ፡-** ይህ ችግር ከሁለት ዓመት በላይም የዘለቀ ይመስለኛል። እኔ የተወለድኩበት ገጠር አካባቢ በዚህ ሃገር መንግሥት ያለ እስከማይመስል ድረስ በፀጥታ ችግር ምክንያት ፍትሕ ሙሉ ለሙሉ ተቋርጧል ማለት ይቻላል። እንደሚታወቀው የሁሉም ስልጣን ባለቤት መንግሥት ነው፤ ስልጣኑን ተጠቅሞ የሕዝብንና የሃገርን ደህንነት የማስጠበቅ፤ ፀረ-ሰላም ኃይሎች ላይ አስፈላጊውን እርምጃ የመውሰድ ኃላፊነት አለበት። ምክንያቱም ሕዝቡ ሃገርን እንዲያስተዳድር ቀጥተኛ ውክልና የሰጠው ለመንግሥት በመሆኑ ነው። በእኔ እምነት በአሸባሪ ቡድኖችና ሃገር አዋኪዎች ላይ የሚወሰደው እርምጃ የላላ ነው። ከዚህ የተነሳ ለምሳሌ በኦሮሚያ በበርካታ ወረዳዎች የፍትሕ ተቋማት አገልግሎት አይሰጡም። ስለዚህ ኅብረተሰቡ ፍትሕ የማግኘት፤ በሰላም የመኖር ህልውና ተጠብቆ የመኖር መብታቸው አደጋ ውስጥ ወድቋል። በርካታ ፍርድ ቤቶች፤ ፖሊስ ጣቢያዎች ተዘግተዋል። አገልግሎት እየሰጡም አይደለም። ይህም ማለት ደግሞ እዛ አካባቢ ያለው ማኅበረሰብ ፍትሕ የማግኘት ሕገ-መንግሥታዊ መብቱ እየተከበረ አይደለም ማለት ነው። ይህ ደግሞ ህዝቡ በመንግስት ላይ ያለው አመኔታ እንዲሸረሸር ያደርገዋል።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በአንባቢዎቼና በዝግጅት ክፍሉ ስም ከልብ አመሰግናለሁ።**

**ዶክተር ዳባ፡- እኔም ሃሳቤን እንድገልፅ እድሉን ስለሰጣችሁኝ አመሰግናሁ።**

# ማህደረ ጤና

## የፕላኔታችንን የጤና ጠንቅ

እፀገነት አክሊሉ

በዓለም ላይ ገዳይ ተብለው በግንባር ቀደምትነት ከተያዙ ሱስ አስያዥ እጾች መካከል ትምባሆ ግንባር ቀደሙ ነው። ትምባሆ በባህርይው የሚገድለው የሚያጨሰውን ሰው ብቻ ሳይሆን አብሮት የሚኖረውን፤ የሚሠራውን በጠቅላላው በአካባቢው ያለውን በሙሉ መሆኑ ነው ግንባር ቀደም ጎጂ ወይም ገዳይ ተብሎ ትልቁን ቦታ እንዲይዝ ያደረገው።

የዓለም ጤና ድርጅት የትምባሆ ኢንዱስትሪ በአካባቢ ላይም ሆነ በሰው ጤና ላይ ምን ያህል ጉዳት እንደሚያደርስ ሰሞኑን አዲስ መረጃ አውጥቷል። እያሳደረ ላለው ውድመት የበለጠ ተጠያቂ ለማድረግ እርምጃ እንዲወሰድ ማስጠንቀቂያ ሰጥቷል።

ድርጅቱ የትምባሆን አሳሳቢነት በተለይም በአሁኑ ወቅት እያደረሰ ያለውን ጉዳት ትኩረት አድርጎ በማየትም ‹‹ፕላኔታችንን የመረዘው ትምባሆ›› በሚል ባወጣው መግለጫው እንደገለጸው፣ በየዓመቱ የትምባሆ ኢንዱስትሪ ከስምንት ሚሊዮን በላይ የሰው ሕይወት፣ 600 ሚሊዮን ዛፎች፣ 2መቶ ሺ ሔክታር መሬት፣ 22 ቢሊዮን ቶን ውኃ እና 84 ሚሊዮን ቶን ካርቦን ዳይኦክሳይድን ያስከፍለናል ብሏል። ትምባሆ በአብዛኛው የሚመረተው ዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ባላቸው አገሮች መሆኑን የጠቀሰው የድርጅቱ መረጃ ለአካባቢው ምግብ ለማምረት በጣም የሚያስፈልጉት ውኃና የእርሻ መሬቶች የትምባሆ ዕፅዋትን ለማልማት እየዋሉ መሆናቸው በዓለም ችግሩ አሳሳቢ እንዲሆን እያደረገው መሆኑንም ያትታል። የደን ምንጣሮውም ከጊዜ ወደ ጊዜ ቁጥሩ እየጨመረ መጥቷል።

በሪፖርቱ እንደተመለከተው ‹‹ትንባሆ ከማምረት፣ ከማቀነባበርና ከማጓጓዝ የሚገኘው የካርበን ዱካ በየዓመቱ በንግድ አየር መንገዶች ኢንዱስትሪ ከሚወጣው ካርቦን ዳይኦክሳይድ አንድ አምስተኛው ጋር እኩል መሆኑ አሁን ላይ ለዓለም ሙቀት መጨመር አስተዋጽኦ ከፍ እያለ እንደመጣም ነው ሪፖርቱ የሚያትተው። ‹‹የትምባሆ ምርቶች በምድራችን ላይ ከ7ሺ በላይ መርዛማ ኬሚካሎችን ይዘዋል የሚለው የዓለም ጤና ድርጅት አሁናዊ ሪፖርት እነዚህም ሲወገዱ ደግሞ ወደ አካባቢያችን ዘልቀው ይገባሉ፣ በየዓመቱ 4 ነጥብ 5 ትሪሊየን የሲጋራ ፊልተሮች (ማጣሪያዎች) ውቅያኖሶችን፣ ወንዞችን፣ የከተሞች የእግረኛ መንገዶችን፣ ፓርኮችን፣ አፈርን እና የባህር ዳርቻዎችን ይበክላሉ፤›› ያለው የድርጅቱ መረጃ እንደ ሲጋራ፣ ጭስ አልባ ትምባሆና ኢ-ሲጋራዎች ያሉ ምርቶች የፕላስቲክ ብክለትን ይጨምራሉም ይላል።

ማይክሮ ፕላስቲኮችን የሚይዙት የሲጋራ ፊልተሮች በዓለም አቀፍ ደረጃ ሁለተኛው ከፍተኛውን የፕላስቲክ ብክለት የያዙ መሆኑንም ያክላል።

የትምባሆ ምርት የሚባለው በከፊልም ሆነ ሙሉ ለሙሉ ከትምባሆ ቅጠል የተዘጋጀ በማጨስ፣ በመሳብ፣ በማኘክ፣ በማሽተት ወይም በሌላ መንገድ የሚወሰድ ማንኛውም ንጥረ ነገር ነው። ይህም ሆኖ ግን ጉዳቱ በሰው ልጆች ጤና፣ ሥነ አዕምሮአዊ ሁኔታና ማኅበራዊ ሕይወት፣ ብሎም በኢኮኖሚያዊ ላይ የሚያስከትለው ችግር በእጅጉ ከፍተኛ ነው።

ትምባሆ የደም ዝውውርን ያስታጉላል። ከዚህ ዓይነቱ ዝውውር ጋር ተያይዞ የሚመጡ የልብና የጭንቅላት ላይ ደም መፍሰስንም ሊያስከትል ይችላል። ከዚህም ሌላ የአጥንት መሳሳት የድድ፣ የጥርስ፣ የመስማትና የማየት እንዲሁም የመውለድ አቅም ላይ ከፍተኛ ችግር ሊያስከትል እንደሚችል፣ ሁለት ሦስተኛው የሚሆነውም አጫሽ የሚደርስበት የሞት አደጋ ከሚያጨሰው ሲጋራ ጋር ተያያዥነት ባለው በሽታ መሆኑን መረጃው ያመለክታል።

**ሲጋራ የሚያጨሱ ሰዎች ሲጋራ ከማያጨሱ ሰዎች መካከል ከ30 እስከ 40 በመቶ ያህሉ ለደረጃ ሁለት የስኳር በሽታ የተጋለጡ ናቸው፣ ሲጋራ ለረዥም ጊዜ የሚያጨሱ ሰዎች አማሟታቸው ከማያጨሱ ሰዎች አሥር ዓመት የቀነሰም ነው**

ሪፖርቱ እንደሚያመለክተው ሲጋራ የሚያጨሱ ሰዎች ሲጋራ ከማያጨሱ ሰዎች መካከል ከ30 እስከ 40 በመቶ ያህሉ ለደረጃ ሁለት የስኳር በሽታ የተጋለጡ ናቸው፣ ሲጋራ ለረዥም ጊዜ የሚያጨሱ ሰዎች አሟሟታቸው ከማያጨሱ ሰዎች አሥር ዓመት የቀነሰም ነው።

ኢትዮጵያም እንደ ሌሎች አገሮች በየዓመቱ ትምባሆን በቀን ደረጃ እያሰበች፤ ቀኑንም ትምባሆ ለእኛና ለምድራችን ሥጋት መሆኑንም እያመለከተች ማክበሯን ቀጥላለች። ከዚህም በላይ የጉዳዩን አሳሳቢነት የገዳይነቱን መጠን እንዲሁም በአረንጓዴ ልማት ላይ የሚያስከትለውን ችግርም በመረዳት ሕገ ወጥ የትምባሆ ንግድ ቁጥጥርና ማስወገድ ፕሮቶኮልን ለማፅደቅ የተለያዩ ሥራዎች እያከናወነች ነው።

በኢትዮጵያ በትምባሆ ሰበብ በዓመት 17 ሺ ሰዎች ሕይወታቸውን እንደሚያጡ በቅርቡ የተጠና አንድ ጥናት ማመላከቱን መረጃዎች ያመለክታሉ፤ አጫሾች በተለይም በካንሰር፣ በልብ፣ በሳንባና በጨጓራ ሕመም የመሞት ዕድላቸው ከፍተኛ መሆኑንም እነዚሁ በዘርፉ ላይ የሚሰራጩ መረጃዎች ያሳያሉ።

በኢትዮጵያ በመፍትሔነትም ግንዛቤ ከመፍጠር ባለፈ በትምባሆ ሥርጭት ላይ ጠንካራ የቁጥጥር ሥርዓትን ለመተግበር የተለያዩ ሥራዎች እየተከናወኑ ነው። ከነዚህም ውስጥ ሕገ ወጥ የትምባሆ ንግድ ቁጥጥር ማስወገድ ፕሮቶኮልን ለማፅደቅ የሚከናወነው ዋነኛው ነው ።

ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ የትምባሆ ምርቶች ላይ ጥብቅ ቁጥጥር ለማድረግ ከፌዴራል የምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ባለሥልጣንና ከጉምሩክ ኮሚሽን ጋር በመሆንም እየተሠራ ነው።

ኢትዮጵያ የዓለም ጤና ድርጅት የትምባሆ ቁጥጥር ማዕቀፍ ኮንቬንሽንን በ 2006 ዓ.ም. ማፅደቋን፣ በ2011 ባወጣችው አዋጅ መሠረትም የትምባሆ ምርትን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ማስተዋወቅ፣ ስፖንሰር ማድረግ መከልከሉ ይታወሳል።

## የዶሮ በሽታ አዲሱ የጤና ዘርፍ ስጋት

እፀገነት አክሊሉ

ከሰሞኑ የዶሮ እርባታ ማዕከል በሆነችው በቢሾፍቱ፣ በአዲስ አበባና በአንዳንድ አጎራባች አካባቢዎች ላይ በተከሰተ ያልታወቀ የዶሮ በሽታ በበርካታ ሺህ የሚቆጠሩ ዶሮዎች ሞተዋል። ይህንን ተከትሎም የግብርና ሚኒስቴር ዶሮና የዶሮ ውጤቶችን ላልተወሰነ ጊዜ ለገበያ እንዳይቀርቡ የሚለውን እገዳውን ሰኔ 3 ቀን 2014 ዓ.ም ማውጣቱም ይታወሳል።

በአንዳንድ የዶሮ እርባታ ጣቢያዎች ውስጥ መቶ በመቶ በሚባል ሁኔታ ዶሮዎች ሞተዋል፤ ይህ ምንነቱ ያልታወቀ የዶሮ በሽታ፣ ምንነቱ፣ መምጫ መንገዱ እንዲሁም መፍትሔ እስኪገኝ ድረስ ዶሮ፣ ጫጩቶችና እንቁላሎች ከተለያዩ ክልሎች ማጓጓዝ ላይም እገዳ ተደርጓል።

በተጨማሪም ዶሮ አርቢዎች ዶሮና የዶሮ ውጤቶችን ለገበያ ማቅረብ እንደማይችሉ የግብርና ሚኒስቴር ተናግሯል። በተለይ በሽታው በዋነኝነት በተከሰተባቸው ቢሾፍቱ፣ አዲስ አበባና አጎራባች አካባቢዎች ላይ ዶሮና የዶሮ ውጤቶችን ማጓጓዝ፣ ከውጭም ማስገባትና ወደ ውጭ መላክ ላይም እግድ ተጥሏል። ይህ የሆነውም ችግሩ እንዳይዛመት በሽታውም በተከሰተባቸው ስፍራዎች ላይ ብቻ ተወስኖ እንዲቀር እንዲሁም በኅብረተሰቡ ውስጥ የጤና መቃወስ ችግርን እንዳያስከትል በማለት ነው።

ግብርና ሚኒስቴር ከሰሞኑ በሰጠው መግለጫም በቢሾፍቱና በአዲስ አበባ እንዲሁም ለመዲናዋ ቅርብ የሆኑ አጎራባቾች ዶሮም ሆነ እንቁላል ወደከተማዋ ይዘው እንዳይገቡ ከማድረግ ባሻገርም የተለያዩ ክልሎች እንደ አላቸው ነባራዊ ሁኔታ በሽታው እንዳያገኛቸው ካገኛቸውም ደግሞ እንዳይዛመትባቸው የየራሳቸውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉም ማሳሰቢያ ሰጥተዋል።

በአሁኑ ጊዜ መጀመሪያ ላይ እንደነበረው የዶሮዎች ሞት እየተከሰተ ባይሆንም ሙሉ በሙሉ ጠፍቷል የሚባልበት ደረጃ ላይ ግን አለመድረሱን በመግለጽ ኅብረተሰቡ ከመዘናጋት ወጥቶ ግብርና ሚኒስቴር እንዲሁም የጤና ሚኒስቴር በጋራ ያቋቋሙት ግብረ ኃይል በበሽታው ላይ ውሳኔን እስኪያሳልፍ ድረስ እገዳው እንደጸና መሆኑንም እየተናገሩ ነው።

የኢትዮጵያ ዶሮ አርቢዎችና አቀናባሪዎች ማኅበር ሥራ አስኪያጅ አቶ ብርሃኑ ሚሊዮን እንደሚናገሩት፣ በሽታው ከቢሾፍቱ እስከ አዳማ ባለው ኮሪደር በስፋት ተከስቶ ቆይቷል። ምንም እንኳን የዶሮ በሽታዎች በተደጋጋሚ ቢከሰቱም በሽታው በፍጥነት የመተላለፍና የመዛመት ባህርይ በማሳየቱ እንዲሁም በገባባቸው የዶሮ እርባታ ማዕከላት በብዛት እንዲሁም ሙሉ በሙሉ ዶሮዎችን መግደሉ ለየት እንደሚያደርገውም ይናገራሉ።

በሽታው በአነስተኛና በመካከለኛ ዶሮ እርባታ ማዕከል ያስከተለውን ከፍተኛ ሞት በማየት ክስተቱ ከበድ ያለ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል። አሁን ላይ ከጤና ሚኒስቴርና ከግብርና ሚኒስቴር የተውጣጡ ኮሚቴዎች ተቋቁመው የበሽታውን ስፋትና መጠን እንዲሁም ያደረሰውን ጉዳት ብሎም ኅብረተሰቡ ጤና ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ችግር የሚዳስስ ጥናትን በማድረግ ላይ ናቸው።

በሽታው ሁሉንም ዓይነት ዶሮዎች፣ ጫጩቶችን ጨምሮ መጠነ ሰፊ ሞት በማድረሱና ሰፊ ቦታ በመሸፈኑ የዶሮ በሽታ ወረርሽኝ ሊባል እንደሚችል እየተገለጸ ነው።

እስካሁን ስለበሽታው የታወቀ ነገር ስለሌለ ምንነቱን ለመለየት የግብርና ሚኒስቴር የምርምር ሥራዎችን በዋነኝነት እያከናወነ ይገኛል። ሆኖም በተደረገው ዳሰሳና ከበሽታው ባህርይ በመነሳት በንክኪ ስለሚተላለፍ በአዲስ አበባ፣ በቢሾፍቱና በኦሮሚያ ክልል የዶሮና የዶሮ ውጤቶች ገቢም ሆነ ወጪ እንቅስቃሴ እንዳይደረግ ውሳኔ ተላልፏል።



ለዚህ ውሳኔ ምክንያቱም አንዳንድ አርቢዎች ዶሮዎች ሲታመሙባቸው ከማስወገድ ይልቅ የመሸጥ ሁኔታ በመታየቱና በሌሎች ስፍራዎች ተዛምቶ እንዲሁም በሰዎች ጤና ላይ ጉዳት አድርሶ በአጠቃላይ በአገሪቱ የዶሮ እርባታ ዘርፍን እንዳይጎዳ በሚል የተወሰደ እርምጃ እንደሆነ ይጠቀሳል። አሁን እንደተባለው በሽታው ስር እንዳይሰድ በሰዎች ጠበቅ ያለና ሙሉ እገዳ ነው የተጣለው፤ በዚህ ምክንያት ደግሞ በኢትዮጵያ ደረጃ ከክልል ወደ ክልል ዶሮና የዶሮ ግብዓቶችን እንቁላልና ጫጩቶችን ማጓጓዝ አይቻልም። ከዶሮና የዶሮ ውጤቶች በተጨማሪ ከዶሮ ጋር ንክኪ የሚኖራቸውን መገልገያዎችን መኖን ጨምሮ ማጓጓዝ እስካሁንም እንደተገደበ ነው ።

ከዚህ ባለፈ ዶሮ፣ ጫጩቶች፣ ቄቦች፣ የዳበረ (የለማ) እንቁላል ከውጭ አገራትም እንዳይገቡ እንዲሁም ወደ ውጭ እንዳይላኩ እገዳው ይከለክላል። ለገበያ ማቅረቡም ሆነ የእንቅስቃሴ ገደቡ በሽታው ተለይቶ በቁጥጥር ስር እስኪውል ድረስም የሚቀጥል እንደሆነም እየተነገረ ነው።

ባለፈው ሳምንት የሞት መጠኑ ከፍተኛ የነበረ ቢሆንም፣ ባለፉት ቀናት ግን ጋብ የማለት ምልክት እንዳሳየም እየተነገረ ነው፤ ይህ ሆነ ማለት ግን አሁንም በትክክል የበሽታው ምንነት ብሎም በሰዎች ላይ የሚያስከትለው የጤና ችግር እስከሚረጋገጥ ድረስ ለምግብነት አይውሉም ማለት መሆኑም ሊታወቅ ይገባል።

ሞት ቆሟል ማለት በሽታው አይዛመትም ማለት ስለማይቻል፣ ምን ዓይነት ተፅእኖ እንደሚያመጣ ስለማይታወቅ፤ የኅብረተሰብ ጤና ጉዳይም ስለሚኖረው ያንን ማጣራት ያስፈልጋል። ሆኖም በአዲስ አበባ ከተማ አንዳንዶች ለችግሩ ተገቢውን ትኩረት ባለመስጠት አሁንም ድረስ ዶሮንም ሆነ እንቁላልን እየተጠቀሙ ነው። ይህ ደግሞ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ሊያመዝን ስለሚችል በመንግሥት የተቋቋመው ገብረ ኃይል የመጨረሻ ውሳኔውን እስከሚያሰማ ድረስ ምርቶቹን ከመመገብ መቆጠቡ ኋላ ከሚመጣው የጤና መዘዝ ሊያድን ይችላል።

# ነፃ ሃሳብ



በ(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# የአገር ጉዶች፤ የንጹሐን ደም ባለ እዳዎች

**ወደ ጸባኦት ያስተጋበው የደም ጩኸት፤**

የአገሬ የኤሎሄ የጣር ጩኸት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየበረታ ሄዶ የጸባኦትን ደጃፍ ወደ ማስከፈት ደረጃ ላይ የደረሰበት ወቅት ይመስላል። ምክንያቱ ደግሞ ግልጽ ነው። በደም የሰከሩ፣ ለግፍ የበረቱ ጨካኝ «ሰብአዊ አውሬዎች» ከጥቂት ዓመታት ወዲህ በተደጋጋሚ ጊዜያት ከጫካ እየወጡ ንጹሐንን በመጨፍጨፍ ምድሪቱን በደም አበላ ማጨቅየትን ሥራዬ ብለው ተያይዘውታል።

በዚህ ምክንያትም አገር «ላማሰበቅታኒ!» እያለች እጆቿን ዘርግታ ወደ ፈጣሪ ስትቃትት ሕዝብም አብሮ ምድሪቱን በማላቀስ እምባችን የጋራ ቀለባችን ከሆነ ሰነባብቷል። በአንጻሩ «አውሬዎቹ ግፈኞች» በደም በጨቀየው እግርና እጃቸው ጮቤ እየረገጡና በእኩይ ተግባራቸው የወገኖቻችንን በድን እንደ ግዳይ በመጣል የደስታ «ርችት» በመተኮስ ያቅራራሉ፤ እያስተኮሱም ያሽካካሉ።

ጋላቢዎቹና ተጋላቢ አጋሰሶቹ «የደም አፍሳሽነት የግፍ ትራዠዲያቸውን ጉግስ» እየፈጸሙ ያሉት እንኳንስ ጥልፍልፉን ውል አልባ የአገራችንን የፖለቲካ እንካሰላንትያ ሊረዱት ቀርቶ «ፖለቲካ» የሚለውን ቃል እንኳን ሰምተው በማያውቁ ንጹሐን ዜጎች ላይ መሆኑ በራሱ ሰዋዊ ባህርያቸው ወደ አውሬነት ስለመለወጡ ጥሩ ማሳያ ነው። የግፉቸው ሰለባ የሆኑ ሕፃናትና እህቶች፣ አባቶችና እናቶች በደደረ መዳፍ የዕለት እንጀራቸውን ለማሸነፍ ደፋ ቀና የሚሉት ሕይወትን ያሸነፉ መስሏቸው እንጂ ሌላ ተልዕኮም ሆነ ዓላማ አልነበራቸውም።

በኢትዮጵያ ምድር የሰኔ ወር በተለየ ሁኔታ እየተጠበቀ፤ በተቀሩት ወራትም እንዲሁ እየተደጋገመ በመፈጸም ላይ ያለው በአሸባሪው ሕወሓትና በሸኔ ጥምር ሰይጣናዊ ተልዕኮ የሚመራው እልቂትና ማፈናቀል ምናልባትም ከጀርመን ናዚና ከኢጣሊያው የፋሽስት ጭፍጨፋዎች በደረጃው ከፍ ባለ የታሪክ ዐይን ተሰንዶ ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍ እንደሚኖር የሚያጠራጥር አይደለም።

ቀደም ባሉት ዓመታት በተለያዩ የአገራችን ክፍሎች፣ በቀደም በጋምቤለ ክልል ውስጥ ትናንት ሰኔ 11 ቀን 2014 ዓ.ም ደግሞ በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ኦሮሚያ በጊምቢ የወረዳ ቀበሌዎች ውስጥ (ጉቱ፣ ጨቆርሳ፣ ስልሳው፣ በገኔ፣ እና ሌሎች መንደሮች ውስጥ) የተፈጸመው አሰቃቂ ፍጅት ከናዚ የሆሎኮስት ጭፍጨፋ በምን ሊለይ እንደሚችል ማሰቡ በራሱ አቅም ይፈትናል። «ሰብዓዊ» ነን ይበሉ እንጂ «ሲፊኒክሳዊ» (ግማሽ ሰው ግማሽ አጋንንት እንዲል የቅዱስ መጽሐፉ ታሪክ) አፍ ባልፈቱ ንጹሐን ሕፃናት ላይ አፈሙዛቸውን አዙረው ሲፈጇቸው ምን ብለው ተማጽነዋቸው ነበር?

እናቶችና እህቶች ተንበርክከው ሲለምኗቸውስ በአውሬያዊ መንፈሳቸው ምን ተሰምቷቸው ይሆን? እነዚያ ምስኪን የመከራ ገፈት ቀማሾች ላባቸው የፈሰሰበት ንብረታቸው በአንድ ቅጽበት የእሳት እራት ሆኖ ሲመለከቱስ ስሜታቸውን እንዴትና በምን ገልጸው ይሆን? እንኳንስ ተጎጂዎቹ ዘንድ ተገኝቶ በአካል ለማጣራት ቀርቶ በርቀት ሆኖ ለመገመት እንኳን ይከብዳል።

የጫካው አውሬ የሸኔ አሸባሪ ቡድን ዳዴ በሚልበት ዕድሜ ላይ ቆሞ ሲውተረተር «ወፌ ቆመች» ባይባል ኖሮ፣ ድክ ድክ እያለ መራመድ ሲጀምርም «የወተት ጥርሱን እንዳይነቅል» በአጭሩ ቢቀጭ ኖሮ ይህ የዛሬው መከራችን ገዝፎ እንደ ወስከንባይ ባልተደፋብን ነበር።

በበደልና በግፍ የወረዛ የሕዝብ ሙሾ በእንባ፣ በግጥምና በዜማ ተለውሶ መፍሰሱ የተለመደ የአገር ወግ መሆኑ በሚገባ ይታወቃል። ይህ ጸሐፊም «ምን ነበረበት ይህ እኩይ ‹ሸኔ ይሉት› ቡድን በእንጭጭ ዕድሜው ላይ በነበረበት ወቅት ቀድሞ ቢቀጭ ኖሮ!?» የሚለውን ቁጭቱን ሊወክሉለት የሚችሉ ጥቂት ስንኞችን ከወዳጁ አንድ ግጥም ተውሶ እንዲህ ጠቅሶታል።

**«ሀ» ሲባል «ሀ» ቢባል፤ ጅምሩ ቀድሞ ቢዳሰስ፣**
**ቀድሞ! ቀድሞ! ቢቀነጠስ፤**
**መፈልፈያው ቢደፈን፣ ሥሩ ማለዳ ቢበጠስ፣**
**የውስጥ ውስጡ የላይ ላዩ፣ ቃርሚያው በወጉ ቢነሣ፣**
**ባልኖረ ባልነበረ - ነበር፣ የዛሬው «ክምር» አበሣ!**
**የችግሩ «ችግር» ይህ ነው፤ ሽምቅታው ነው የበደለን፣**
**«የሣመን» ነው የነከሰን፤ የሣቀ ነው የገደለን።**
**ያለፈው ቀድሞ አለፈ፤ ዛሬ ለነገ እንዲነቀስ፣**
**ድራ-ድሩን ነው መበጠስ፣ «አስኳሉን» ነው መፈርከስ።**
**እንጂማ...ቅርንጫፉማ ጭራሮ ነው፣**
**ግንዱ ሲቆረጥ የሚረግፍ።**
**ግንዱም ቢሆን ግንዲላ ነው፣ ሥሩ ሲነቀል የሚነጥፍ።**
**«አሾክሻኪው» አፉ ሲዘጋ፤ «ወሻቂው» እጁ ሲቆረጥ፣**
**እርቃኑን ይቀራል የጥሻው፤ የጀግናን ክንድ ሲቀምስ።**
**(ምንጭ፡- «አንድ ቀን» -**
**ሻለቃ ክፍሌ አቦቸር፤ 1982)**

በመከራ የሚገረፈው ገላ ሰንበሩ ቶሎ ባይጠግግም፤ የመከራ ቀን ጀንበር አጭር በመሆኑ አገርና ሕዝብ ሊጽናና፤ ከእንግዲህ በኋላም መንግሥት እንደ ካሁን ቀደም ሳይዘናጋ ሕግ የማስከበር ሥራውን አጠንክሮና አምርሮ ሊሠራ ይገባል።

ዛሬ መከራ ወድቆባቸው በመቶዎች በሚቀጠር አሀዝ በጭካኔ የተጨፈጨፉት ኢትዮጵያውያን በምዕራብ ኦሮሚያ እግራቸውን የተከሉት ከ1977 - 1978 ዓ.ም በተከሰተው ድርቅ ምክንያት ከአንዱ የአገራቸው ክፍል ወደ ሌላው የአገራቸው ክፍል በሠፈራ ፕሮግራም የተሰባሰቡ እንጂ ከባእድ ምድር የፈለሱ «መጤዎች» አልነበሩም። ጨፍጫፊዎቹ ህሊና ቢፈጥርባቸው ኖሮ እንኳንስ ሕይወታቸውን ሊቀጥፉ ቀርቶ በክፉ ዐይን ባላዩቸው ነበር። ስለምን? የጅማሮው ታሪክ እንዲህ ይታወሳል።

ያን መሰሉ የሠፈራ ፕሮግራም ሲከናወን በከፍተኛ መንግሥታዊ ኃላፊነት ላይ የነበሩትና እቅዱን በማስፈጸሙም ረገድ ትልቅ ድርሻ የነበራቸው ጎምቱ ባለሥልጣን በቅርቡ ባሳተሙት መጽሐፍ ውስጥ የወለጋ ሕዝብ ወገኔ ብለው የሄዱትን ወንድም እህቶቹን እንዴት ይቀበላቸው እንደነበር የገለጹበት ሁኔታ በእውነቱ እጅግ ልብን የሚነካ ነው።

«በመኖርና ባለመኖር መካከል የሚገኙትን ወገኖቻችንን የመርዳት የዜግነት ግዴታ አለብን በማለት ነበር የወለጋ ገበሬዎች ፕሮግራሙን ከልባቸው የተቀበሉትና የደገፉት። ...የወለጋ ገበሬ ከዳር ዳር ተንቀሳቅሶ ለሰፋሪዎች እነዚያን የመሰሉ ሁላችንም ያደነቅናቸውና የኮራንባቸውን መንደሮች መስርቶ ለሰፋሪዎቹ ቤት ብቻም ሳይሆን ወገባቸውን የሚያሳርፉበት አልጋ፣ ከብርድ ራሳቸውን የሚከላከሉበት ብርድ ልብስ፣ ወደፊት አምርተው እህል የሚያስቀምጡበት ጎተራ፣ ለእዚያ እስኪበቁ ድረስ በጎተራው ውስጥ ለስድስት ወር የሚሆን ቀለብ አልፈው ተርፈው ለስድስት ወራት የሚሆን ቡና ጭምር አከማችተው ነበር ወንድሞቻቸውን የተቀበሉት።» (የሻምላው ትውልድ፤ ፋሲካ ሲደልል፤ ገጽ 315።)

> የግፉቸው ሰለባ የሆኑ ሕፃናትና እህቶች፣ አባቶችና እናቶች በደደረ መዳፍ የዕለት እንጀራቸውን ለማሸነፍ ደፋ ቀና የሚሉት ሕይወትን ያሸነፉ መስሏቸው እንጂ ሌላ ተልዕኮም ሆነ ዓላማ አልነበራቸውም

ታሪካዊው እውነታ ይህ ሆኖ እያለ ዛሬ «ባለጊዜ» የሆነ መስሎት በወገኖቻችን ደም እጁን የሚታጠበው የሸኔ ቡድን የተጎነጨው የግፍ ደም፤ የመጥፊያው ምክንያት እንደሚሆን ወደ አእምሮው ተመልሶ ያሰበ አይመስልም። በተለይም በትውልድ እልቂት ተጠያቂ የሆነውና የፍትሕ ሰይፍ ሊያርፍበት ከጫፍ ላይ ለደረሰው የአሸባሪው ሕወሓት ቡድን መጋለቢያ የሆነው የሸኔ በማን ሳንባ እንደሚተነፍስና በማን አእምሮ እንደሚያስብ በግልጽ የታወቀ ነው።

ጨካኞች በአገር ክብር፤ በወገን መኩራት የሚሉት አስተሳሰብ የሚዞርባቸው አይደለም። እነርሱ ሆዳቸውን አምላካቸው፣ ነውራቸውን እንደ ክብራቸው እየቆጠሩ ስለሚኖሩ «ብሔሬ» የሚሉትን ወገን ስሙን እንጂ በጎ ተግባሩን አይኖሩበትም። አልፎም ተርፎ በአገር ላይ ከተሰለፉ ባእዳን የውጭ ጠላቶቻችን ጋር ተሰልፈው ማበራቸው የከንቱነታቸው ተቀዳሚ መገለጫ ነው።

ለምሳሌ፡- በሰኔ አስራ አንድ ቀን የፈጸሙትን የግፍ ጭካኔ ቀድሞ እንዲያስተጋቡላቸው የተዋዋሉት የግብጹን “Dail News” ጋዜጣ እና ከሌሎች መሰል የሚዲያ ተቋማት ጋር መሆኑ የሚረጋገጠው ድርጊቱ በተፈጸመ በጥቂት ደቂቆች ውስጥ የእልቂቱ ዜና እንዲሰራጭ መደረጉ ነው። በዚህን ዓይነት ቅንብር የደም ቃልኪዳን የተማማሉት «ደማቸውን ደመ ከልብ» ያደረጓቸውን ወገኖቻችንን ለመጨፍጨፍ ብቻማ ሳይሆን አገሪቱን ወደማያባራ የመተረማመስ አዘቅት ውስጥ ከቶ ከጌቶቻቸው ዘንድ ተስፋ የተገባላቸውን ዳረጎታቸውን ተስገብግቦ ለመቀበል በመጓጓት ጭምር አቅደው ነበር።

በመልካም የእርሻ ማሳ ላይ አረም ከየት መጣ ሳይባል እንደሚፈላ ሁሉ፤ በአገርና በሕዝብ መካከልም ያልተጠበቁ ዘግናኝ ክስተቶች እንደሚፈጸሙ ይታመናል። ይህንን መሰሉን የእኩያን እቅድ ቀድሞ በማክሸፉ ረገድ ግን የሕዝብን ሰላምና ጸጥታ ለማስከበር ቀዳሚውን ኃላፊነት መውሰድ የሚገባው መንግሥት ቀድሞ የቤት ሥራውን መሥራት እንደሚገባው ተደጋግሞ ተመክሯል፤ ሲበረታም መገሰጹ አልቀረም።

ዓላማ ቢስ ቡድኖች ሁሌም ኢላማቸው/ ታርጌታቸው ምስኪኑንና ለፍቶ አዳሪውን ዜጋ ማጥቃት ነው። ፈሪ ሰው የሚያደምጠው ጎሊናውን ሳይሆን ቅዠቱን ነው። ስለዚህም ሁሌም እንደባነነ ነው፤ ደግሞም እንደቀባዠረ። ጭንቅላቱ ትራስ ሳይነካ እንደተቅበዘበዘ ውሎ የሚያድረው በከንቱ ያፈሰው የንጹሐን ነፍሶች ወደ ፈጣሪያቸው የሚያደርጉት እሪታና የፍርድ መማጸኛ እንዳባነነው ነው።

ለዚህ አገላለጽ በጥሩ አብነት የሚጠቀሰው የቅዱስ መጽሐፉ ቃየል ነው። ቃየል የወንድሙን ደም በከንቱ ቅንዓት ካፈሰሰ በኋላ ፈጣሪ በመለኮታዊ ነጎድጓድ ድምጹ የጠየቀው እንዲህ በማለት ነበር፤ «ወንድምህ አቤል ወዴት ነው?» እርሱም ለኃያሉ ፈጣሪ የመለሰው የእብሪት መልስ፤ «አላውቅም የወንድሜ ጠባቂው እኔ ነኝ!?» ፈጣሪም በፊናው ውሳኔውን እንዲህ በማለት አሳወቀው፤ «የወንድምህ የደሙ ድምጽ ከምድር ወደ እኔ ይጮኻል።

አሁንም ደሙን ከእጅህ ለመቀበል አፍዋን በከፈተች በምድር ላይ አንተ የተረገምህ ነህ። ኮብላይና ተቅበዝባዥም ትሆናለህ።» ቃየልም በራሱ አንደበት ያረጋገጠው ያንንነው የፈጣሪን እርግማን ነበር። እንዲህ ሲል፡- «በምድርም ላይ ኮብላይና ተቅበዝባዥ እሆናለሁ።የሚያገኘኝም ሁሉ ይገድለኛል።» (ኦሪት ዘፍጥረት ምዕ. 4)

አሸባሪው ሸኔም ሆነ ጋላቢው ሕወሓት ወይንም በውጭ አገራት ተጠልለው አለንላችሁ የሚሏቸው የእኛዎቹ የእንግዴ ልጆችና ባዕዳን ሴረኞች የመጨረሻ ፍጻሜያቸው አንድም እርስ በእርስ መበላላት ወይንም እንደ ጉም ብን ብሎ መጥፋት ነው። እንዴት? ምላሹ ባይዘረዘርም አይጠፋቸውም። መላው ሕዝብም ቢሆን እንደ ሌሎቹ ብሔራዊ ንቅናቄዎች እነዚህን የክፉት ኃይላት ለመፋለምና ለማጋለጥ ሆ! ብሎ ሊነሳ ግድ ነው።

ክፉዎች ፍጻሜያቸው እንደ ትቢያ ብን ብሎ መጥፋት ቢሆንም የሕዝብ የተቃውሞ ድርሻም ቀላል የሚባል አይደለም። ጨካኞች ታሪክም አሻራም አይኖራቸውም። ለሞቱት ኀዘናችንን፣ ልባቸው ለቆሰለ መጽናናትንና ድጋፍ ለሚፈልጉ አለኝታነታችንን ለማረጋገጥ በአንድ ልብ ሆነን መንቀሳቀሱ ግን ጊዜ የሚሰጠው አይደለም። ሰላም ይሁን!

## ተናጋሪው ዶሴ

# የአይበገሬዋ ሞግዚት ክርክር ከፈረንሳይ እስከ ኢትዮጵያ

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

የሰነድ ቁጥር 101675 የሆነው መዝገብ ባለጉዳዮች ጥቅምት 24 ቀን 2008 ዓ.ም ከችሎቱ ፊት ቆመዋል፤ ዳኞችም በችሎቱ ተሰይመዋል። የአመልካች ወይዘሮ መስከረም ሞጋ ጠበቃ መስፍን ጌታቸው በአካል ተገኝተዋል። ተጠሪዋ ወይዘሮ ትዕግስት አረጋ በኩል የቀረበ ባይኖርም ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ፍርድ ከመስጠት አላገደውም።

### የክሱ ይዘት

የሥራ ውል መነሻ ያደረገ የደመወዝ ክፍያ ጥያቄ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ በአሁኗ አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመሠረቱትን ክስ መሠረት በማድረግ ነው። አመልካች በየደረጃው ጉዳዩን የተመለከቱት ፍርድ ቤቶች መሠረታዊ የሕግ ስህተት የፈፀሙ በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ የሚል አቤቱታ በማቅረባቸው አጣርቶ ለመወሰን የቀረበ ጉዳይ ነው።

በተጠሪ የቀረበው ክስ ይዘት በአጭሩ በፈረንሳይ ሀገር በአመልካች መኖሪያ ቤት ውስጥ በየወሩ 1200 /አንድ ሺህ ሁለት መቶ ዩሮ/ ደመወዝ እየተከፈላቸው በሞግዚትነት እንዲሠሩ በ19/02/2001 ዓ.ም በተፃፈ ውል በአዲስ አበባ ከተማ ጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 09 በሚገኘው በአመልካች ወላጆች ቤት ውስጥ ተፈራርመው ከመጋቢት 02 ቀን 2001 ዓ.ም እስከ መጋቢት 08 ቀን 2002 ዓ.ም ድረስ ለአንድ ዓመት ሲሠሩ እንደቆዩ ያስረዳሉ።

የሥራ ውሉም አመልካች ፈረንሳይ አገርን ሲለቁ የሚቋረጥ ስለመሆኑ፣ አመልካች የተጠሪ ደመወዝ ሳይከፈሉ እንዳሰናበቷቸው የዓመት እረፍት ጊዜም አምስት ሳምንት ሊሰጣቸው እንደሚገባ በውሉ የተመለከተ ቢሆንም እንዳልተሰጣቸው፣አመልካች ደመወዛቸውን እንዲከፍሉዋቸው በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል፣ በሽምግልና ጥረት ቢያደርጉም ሊከፈላቸው እንዳልቻለ፣ 1200 ዩሮ በመሆኑ፣ ደመወዝ 299ሺ520.00 የአምስት ሳምንት የእረፍት ጊዜ 29ሺ120 በድምሩ 328ሺ640 ብር (ሦስት መቶ ሃያ ስምንት ሺህ ስድስት መቶ አርባ ብር) እና ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ገንዘብ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ዘጠኝ በመቶ ወለድ ጋር እንዲከፈላቸው፣ የወጪና ኪሳራ ዝርዝር የማቅረብ መብታቸው እንዲጠበቅላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው።

### ስአመልካች በስር ፍርድ ቤት

አመልካች የበኩላቸውን መልስ ያቀረቡ ሲሆን ዋና ፍሬ ነገሩም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና በፍሬ ነገሩ በሰጡት መልስ ክሱ በፌደራል መጀመሪያ ፍርድ ቤት ቀርቦ የተዘጋ ስለመሆኑ፤ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን እንደሌለው፣ የተጠሪ የደመወዝ ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ መሆኑ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ በፍሬ ጉዳዩም ተጠሪ ያልተከፈላቸው ደመወዝ አለመኖሩን፤ ደመወዝ ካልተከፈላቸው ውሉ ለመዘገበው የፈረንሳይ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ያቀርቡ እንደነበር በመግለፅ መከራከራቸውን የሚያመለክት ነው።

የሥር ፍርድ ቤትም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በተመለከተ በ18/06/2006 ዓ.ም ብይን የሰጠ ሲሆን ጉዳዩን ተመልክቶ የመወሰን የሥረ-ነገር ስልጣን እንዳለው በመጥቀስ የአመልካች መቃወሚያ ውድቅ አድርጓል። የሥር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና የቀረቡ ምስክሮች የሰጡት ቃል ከመረመረ በኋላ በግራ ቀኙ የተፈረመው የሥራ ቅጥር ውል መኖሩን ተቀብሎ የተጠሪ የወር ደመወዝ 1200 ዩሮ እንደነበር በአመልካች ከቀረበው ማስረጃ ፍርድ ቤት የተቀበለው የክፍያ መጠን በድምሩ 6ሺ408 ብር ብቻ እንደሆነ፤ ተጠሪ የሚገባቸው ቀሪ ክፍያ ብር 293ሺ112 መሆኑን፤ የአምስት ሳምንት የእረፍት ክፍያ በድምር ብር 29ሺ120 እንደሆነ በአጠቃላይ አመልካች ለተጠሪ ብር 322ሺ232 (ሦስት መቶ ሃያ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሠላሳ ሁለት ብር) እንዲከፈሉ በማለት ወስኗል።

አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቅሬታ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኘም። ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን በመቃወም ለማስለወጥ ነው። ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር በመደረጉ ተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር አድርገዋል።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም የተጠሪ የክፍያ ጥያቄ በፍትሐብሔር ቁጥር 2601 እና



2023/ሀ/ መሠረት በይርጋ የሚታገድ ነው፤ ጉዳዩ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የሚዳኝ አይደለም፤ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች መቅረብ ከነበረበትም በሥራ ክርክር ችሎት መቅረብ ነበረበት የሚል ይዘት ያለው ነው።

ተጠሪ በበኩላቸው ክሱን በወቅቱ ማቅረባቸው እና በይርጋ የሚታገድበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ ዝርዝር ክርክር አቅርበዋል። አመልካች ያቀረቡት የመልስ መልስም የሰበር አቤቱታውን የሚደግፍ ነው። የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ውሳኔ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል። በዚሁ መሠረት የችሎት ምላሽ የሚያስፈልጋቸው መሠረታዊ ነጥቦች ብሎ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ዘርዝሯል።

ግራ ቀኙ በሚከራከሩበት ጉዳይ አግባብነት ያለው የሕግ ማዕቀፍ የትኛው ነው?፣ የደመወዝ ክፍያ ግምት በተመለከተ የተነሳው የይርጋ ክርክር ተፈፃሚነት ያለው የይርጋ ድንጋጌ በአጣሪ ችሎቱ የተጠቀሰው የፍ/ሕ/ቁ.2023/ሀ/ ነው ወይስ አይደለም ፤ አመልካች ለተጠሪ ሊከፍሏቸው የሚገባው በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው የገንዘብ መጠን ምን ያህል ነው? የሚሉት ናቸው።

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው፤ አመልካች እና ተጠሪ የሥራ ውል ግንኙነት እንደነበራቸው፤ ውሉም ኢትዮጵያ ውስጥ ተፈርሞ በፈረንሳይ አገር የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እንደተመዘገበ የተካደ ጉዳይ አይደለም። አመልካች ከተጠሪ ጋር የሥራ ውል ግንኙነት እንደነበራቸው ሳይክዱ ሁሉም ክፍያዎች በወቅቱ እንደተከፈሉ፣ አልተከፈለም የሚባል ገንዘብ ካለም በይርጋ እንደሚታገድ ተከራክሯል።

ተጠሪ በበኩላቸው በአመልካች ቤት በሞግዚትነት ለአንድ ዓመት ማገልገላቸው እና የጠየቁት ክፍያ እንዳልተፈፀመላቸው እንዲሁም ክሱን በወቅቱ ስለማቅረባቸው በስር ፍርድ ቤት ካቀረቡት ክርክር መረዳት ይቻላል። ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ እያከራከረ ያለው መሠረታዊ ጭብጥ እንደሚከተለው መርመሮታል።

የመጀመሪያው ጭብጥ በተመለከተም አመልካች የተጠሪ የሥራ ቅጥር ውል ከፍ/ሕ/ቁ. 2601 አንፃር እንዲታይ በሰበር አቤቱታቸው አመልክቷል። የዚህ ድንጋጌ መሠረታዊ ይዘት በቤተሰብ አስተዳደር ውስጥ ስለሚኖር አሽከር የሥራ ውል፤ ሠራተኛውን የሚኖሩት መብትና ግዴታዎች የሚመለከት ስለመሆኑ መረዳት ይቻላል። ይህ ድንጋጌ ያለው የተፈፃሚነት ወሰን ሲታይ በአገር ውስጥ በሚቀጠሩ ሠራተኞች ስለመሆኑ የሚያከራክር ጉዳይ ነው።

በተያዘው ጉዳይ የአመልካች እና ተጠሪ የሥራ ውል በኢትዮጵያ ውስጥ ተፈፅሞ በፈረንሳይ አገር የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ፀድቆ አመልካች እና ተጠሪም በፈረንሳይ አገር ሲኖሩ እንደነበር ባልተካደበት ሁኔታ ከላይ የተመለከተው ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ለተያዘው ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለው ሁኖ አልተገኘም። በሌላ በኩል ስለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ የወጣው አዋጅ ቁጥር 377/96 እና የዚህ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 494/1998 ዓላማና ግብ በሀገር ውስጥ ስለሚኖረው የሥራ ስምሪት የተዋዋይ ወገኖች መብትና ግዴታ፤ ሊሟሉ የሚገባቸው አነስተኛ መመዘኛዎች ማለትም የሥራ ሰዓት፤ የእረፍት ጊዜ፣ የሕመም ፈቃድ ወዘተ ያካተቱ ሕግ እንጂ በውጭ አገር ተቀጠረው ሥራ ሲሠሩ የነበሩ ሰዎች የሚያነሱት የመብት ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ ሆኖ አልተገኘም። በመሆኑም አመልካች እና ተጠሪ በሚከራከሩበት ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለው ሕግ /Governing Law/ በሀገር ውስጥ ባለው የሥራ ስምሪት የግራ ቀኙ አንፃራዊ መብትና ግዴታ የሚደነግጉ የፍ/ሕ/ቁ.2601 እና የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ የሚመለከት አዋጅ 377/96 አለመሆኑን ተረድተናል ይላል።

ለተያዘው ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለው የሕግ ማዕቀፍ ስለሥራና ሠራተኛ ማገናኘት አገልግሎት የወጣ አዋጅ ቁጥር 632/2001 ነው። የዚህ አዋጅ መግቢያ፤ የተፈፃሚነት ወሰን የሚመለከት አንቀፅ 3/2/ "የግል አገልግሎት ሥራ ላይ ለመቀጠር ወደ ውጭ አገር በሚሄዱ ኢትዮጵያውያን ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል" በማለት ደንግጓል። በተያዘው ጉዳይ የአመልካች እና ተጠሪ የሥራ ውል የግል አገልግሎት ሥራ ላይ የተመሠረተ ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት ከተደረገው ክርክር መረዳት ይቻላል። በመሆኑም ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የሕግ ማዕቀፍ አዋጅ ቁጥር 632/2001 ነው ብለናል ይላል።

ሁለተኛ ይርጋን የተመለከተ ክርክር ነው። አመልካች የተጠሪ የደመወዝ ክፍያ ጥያቄ በስድስት ወር የሚታገድ ነው በማለት ተከራክረዋል። በዚህ ችሎት እንዲመረመር የተያዘው ጭብጥም የይርጋ ጥያቄው ከፍ/ሕ/ቁ.2023/ሀ/ አንፃር እንዲታይ ነው። ይህ ድንጋጌ ከፍ/ሕ/ቁ.2601 በማጣመር ስንመለከተው በሀገር ውስጥ በቤት አገልጋይነት የተቀጠሩ አሽከሮች በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ክፍያ ካልተጠየቁ እንደተከፈለ የሕግ ግምት ይወሰዳል የሚል ይዘት ያለው ስለመሆኑ ተመልክተናል። በተያዘው ጉዳይ የፍ/ሕ/ቁ. 2601 ይሁን የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 በሀገር ውስጥ የሥራ ስምሪት ላይ በሚነሱ ክርክሮች እንደነገሩ ሁኔታ ተፈፃሚ ከሚሆኑ በስተቀር በውጭ አገር ለተሰጠው አገልግሎትና ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሳው የክፍያ ክርክር አግባብነት ያላቸው የሕግ ማዕቀፎች ባለመሆናቸው አመልካች የተጠሪ የመብት ጥያቄ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ የሚታገድ ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር የሕግ መሠረት የለውም።

አዋጅ ቁጥር 632/2001 አንቀፅ 3/1/ የአዋጁን የተፈፃሚነት ወሰን አንቀፅ 20 ስለ ሠራተኛው መብት፣ አንቀፅ 24 ስለ አነስተኛ ደመወዝ መጠን የሚመለከቱ መሠረታዊ ድንጋጌዎች ያካተተ ቢሆንም፤ በአሠሪና ሠራተኛው የሚነሳው የክፍያ ጥያቄ በተለይም የመብት ጥያቄ ለማቅረብ ተፈፃሚነት ያለው የይርጋ ድንጋጌ በግልፅ የተቀመጠ ነገር የለም። እንዲህ ከሆነ ደግሞ አመልካች እና ተጠሪ እያከራከረ ያለው የይርጋ ጉዳይ መታየት ያለበት ከአጠቃላይ የውል ድንጋጌዎች አንፃር ስለመሆኑ ተቀባይነት ያለው የሕግ አተረጓጎም ሥርዓት ነው። የፍ/ሕ/ቁ. 1677/1/ ‹‹ግዴታዎቹ ከውል የተገኙ ባይሆኑም የዚህ አንቀፅ ደንቦች ይፈፀሙባቸዋል" በማለት የደነገገ ሲሆን የዚህ ድንጋጌ ተዛማጅ የሆነው የእንግሊዘኛው ትርጉም›› 1677/1/ the relevant provisions of this title shall apply to obligations not withstanding that they do not arise out of a contract" በማለት የተደነገገ መሆኑን ተረድተናል ይላል የምርመራ ውጤቱ።

በተያዘው ጉዳይ አመልካችና ተጠሪ እያከራከረ ያለው የክፍያ ጥያቄ ክርክር ተፈፃሚነት ያለው የሕግ ማዕቀፍ ከፍ/ሕ/ቁ.1677/1/ እና 1845 አንፃር መታየት ያለበት ነው። የአመልካችና ተጠሪ የሥራ ውል ግንኙት መሠረት በማድረግ የሚነሳው ክርክር በ10 ዓመት ይርጋ ቀሪ የሚሆን ነው። በመሆኑም በአመልካችና ተጠሪ መካከል የነበረው የውል ግንኙነት የተቋረጠው መጋቢት 2002 ዓ.ም በመሆኑ ክሱ እስከቀረበበት መጋቢት 13 ቀን 2003 ዓ.ም ያለው ጊዜ ሲታይ በፍ/ሕ/ቁ.1845 የተቀመጠው የይርጋ ጊዜ ሳይጠናቀቅ ክስ መቅረቡን የሚያሳይ ነው። በመሆኑም አመልካች የማያነሱት የይርጋ ጥያቄ ተፈፃሚነት ካለው የይርጋ ድንጋጌ አንፃር ሲታይ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም። ስለሆነም የተጠሪ የደመወዝ ክፍያ ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ አይደለም።

መጨረሻው ጭብጥ በተመለከተ፤ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ በወር 1200 ዩሮ እየተከፈላቸው ይሠሩ እንደነበር አረጋግጧል። አመልካች ክፍያ መፈፀማቸው ቢከራከሩም የሥር ፍ/ቤት በማስረጃ የተደገፈ ነው በማለት የተቀበለው ክፍያ 6ሺ408 ብር ብቻ መሆኑ ከውሳኔው ግልባጭ መረዳት ተችሏል። ተጠሪ ያልተከፈላቸው አጠቃላይ ደመወዝና የአምስት ሳምንት የእረፍት ጊዜ ክፍያ ወደ ኢትዮጵያ ገንዘብ ሲመነዘር (6ሺ408 ተቀንሶ) 322ሺ232ብርመሆኑን በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተመልክቷል።

የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መዝኖ አመልካች ለተጠሪ ብር 322ሺ232 ይክፈሉ በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍልም የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም።በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የስር ከፍተኛና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔዎች በውጤት ፈርጅ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመባቸው መሆኑ የሚያሳይ ነገር ያልተገኘ በመሆኑ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል።

### ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮድ መለያ ቁጥር 99933 በ12/07/2006 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 99977 ግንቦት 6/2006 የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
2. አመልካች እና ተጠሪ የሚከራከሩበት የይርጋ ጊዜ የሚገዛው በፍ/ሕ/ቁ 1677/1/ እና 1845 ነው፡፡ በዚህ መሠረት የተጠሪ የመብት ጥያቄ በይርጋ ቀሪ አልሆነም በማለት ወስነናል፡፡
3. አመልካች ለተጠሪ ብር 322ሺ232 ሦስት መቶ ሃያ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ ሁለት/ ከ13/07/2003 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ እንዲከፍሉ መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ክርክር ያወጡት ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ በማለት የዘጋ ሲሆን፤ በፍርድ ቤት ሐምሌ 30 ቀን 2006 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ሲል መዝገቡ ዘግቷል፡፡

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## አማኝ የናፈቁ እምነቶች

**ተገኝ ብሩ**

ኢትዮጵያውያን ከሞላ ጎደል እምነት ወይም ሃይማኖት አለን። አማኝ ነን ብለንም በየእምነት ቦታችን እንገኛለን፤ እንመላለሳለንም። በየትኛውም እምነት ውስጥ እንገኝ እምነቶች ሁሉ የሚጋሩት ትዕዛዝ በጎ መሆንን፣ ለሰው ልጆች ምቹ ሁኔታን መፍጠር ብሎም ለሌሎች መኖር ነው። ሃይማኖታዊ እምነታችን ምድር ላይ እስካለን ለሰው ልጆች መልካም እንድንሆን ፍቅርና ኅብረት እንድናስተምር ያዘናል።

የተለያዩ ጥናቶች ላይ በመመርኮዝ መረጃዎች ስናገላብጥ እኛ ኢትዮጵያውያን የእምነትና ሃይማኖት ባለቤቶች መሆናችንን የሚያሳዩ ማስረጃዎች በርከት ብለው ይገኛሉ።ኢትዮጵያ አማኞች በብዛት ከአምላካቸው ጋር ባላቸው ትስስር የሚታወቁባት አገር መሆኗን እኛ ሳንሆን ሌሎችም ሊመሰክሩ ይችላሉ።

ዛሬ እዚህ እውነት ላይ ተመርኩዤ አንድ ጥያቄ ማንሳት ፈለኩ። የእውነት እኛ ኢትዮጵያውያን የእምነትና ሃይማኖት ሰዎች ነን? ሃይማኖትና እምነታችን ባዘዘን፣ እንድንሆን በሚፈቅድልንና እንድናደርግ በሚያዘን መልካም መንገድ ላይ ነኝ? አዎ ይሄን ጥያቄ እያንዳንዳችን እራሳችንን ጠይቀን ምላሽ መስጠት ያለብን ወቅት ላይ እንገኛለን። እኔ እውነት እምነቴን የማውቅ ጠንካራና ለሰው ልጆች የማስብ በሰዎች ዘንድ በመልካምነት የምታወቅ ነኝ ወይ? ማለት ተገቢ ነው።

አገራችን የሃይማኖትና እምነት ሀገር ናት፤ ሕዝቦቿም አማኞች ናቸው የሚለው ጉዳይ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ከተግባርና ከሁኔታችን ጋር እየተፋለሰ መጥቷል። አማኞች ስነምግባር የተላበስን መሆናችንን የሚያጠያይቅ አጠራጣሪ ምልክቶች እዚህም እዚያም መበርከት ጀምረዋል። እምነታችንን አውቀነው የሚያዘንን መተግበር፣ ከሚከለክለን ደግሞ መታቀብ የእኛ መሠረታዊ ጉዳይ ቢሆንም ከዚያ መሠረት ግን ርቀናል። እምነታችን በትክክል በስነምግባር ማሳየት፣ መተግበሩና መኖሩ ላይ እጅጉን ደክመናል። እምነታችን በመልካም ነገሮች መርሕ የቆመ ሆኖ ሳለ እኛና ተግባራችን፣ የዘወትር ልምዳችን ከዚህ ፍፁም ያፈነገጠ ነው።

እዚህ ላይ ቆም ብለን በማሰብ እራሳችንን መፈተሽ ይኖርብናል። አሁን ላይ ከሰሜን እስከ ደቡብ ከምዕራብ እስከ ምስራቅ በተለያዩ የሀገራችን አካባቢዎች የሰላማዊ ሰዎች ላይ የሚፈፀሙ ግድያዎችና መፈናቀሎች አማኞች ካስባሉን እውነታ የሚቃረን ነው።

የብዙዎቻችን እምነትና የምናምነው አምላክ ከመነሻው የሰው አፈጣጠር ላይ ልዩነት የለውም። መነሻው ተመሳሳይ ሆኖ ሳለ ለምን በብሔርና በጎሳ እየለየን ሌላውን እናጠቃለን? ነገር ግን ዛሬ የሰው ልጆች መነሻው አዳም/አደም መሆኑ እኛም የእሱ ልጅ ልጆች መሆናችን ከደን በየጎሳና በየጎጥ ተለያይተን እንጋደላለን። አምላክ በምክንያት የፈጠረው ለራሱ ጥበብ ያሰኘውን የሰው ልጅ ስለምን እዚህ ተገኘህ ብለን ለመጉዳት ተነሳን? እኛ አቅም እና ብዛት አለን ብለን ባሰብንበት ቦታ ላይ አነስ ብሎ የሚገኘውን ለመጉዳት በምንስ ድፍረት ተሞላን?

በዚህች የምዕመናት አገር በተባለችው ኢትዮጵያ፤ እንግዳ ተቀባይ ኩሩ ሕዝቦች አገር የራስዋ ልጆች መስማማት እንደምን ተሳናቸው? አዎ የሰላምና የፍቅር አገር በተባለችዋ ምድር መስማት ሳንፈልግ የምንሰማቸው፣ ማየት ሳንፈልግ የምንመለከታቸው መዓቶች ተከታትለው ያለ እረፍት እየቀረቡን ነው። በዚህ ዘመን ሰው ሊፈጽማቸው የሚከብዱ ዘግናኝ ግድያዎች እየተፈፀሙ ነው። ሕግና ሥርዓት ባለበት ሀገር ውስጥ ሥርዓት አልበኝነት ተንሰራፍቶ በየቦታው ሰቆቃ በርክቷል።

እኛ አማኝ ከሆንና በስነምግባር ከታነፅን፤ እንዴት አምላካዊ ፍጡርን ያለአግባብ ለመቅሰፍ በረታን። እንዴትስ የሰዎች ሞት ስንሰማ በተመሳሳይ አግባብ ያን ግድያና ሰቆቃ መቃወምና ማውገዝ ያቅተናል። ወገን እምነቶች ለሰው ልጆች መልካም አሳቢዎች ለምድርም ሰላም ምንጭ ከሆኑ ከእኛ ተግባርና ሥራ ጋር እንዴት ተለያዩ።

አዎን ታመናል፤ ወይ እምነታችንን አናውቀውም አሊያም ደግሞ እምነት አለን እንጂ አማኝ አይደለንም። እምነትና መርሆችን ጥሰን እምነት አልባዎች የሚደርጉትን ከአንድ አማኝ የማይጠበቅ ተግባር ላይ ተጥደናል። በክፉው ተግባር ባንሳተፍ፣ ክፉውን ተግባር ባንደግፍ እንኳን ይህ ተገቢ ያልሆነ ክፉ ተግባር እንዲቆም ያደረግነው አስተዋፅዖ እንደ አማኝ ኢምንት ነው። ሰዎች መልካም እንዲያስቡ ግጭትና የእርስ በርስ መጠፋፋት እንዲገታ መጣር ተስኖን በጥቂት ክፉዎች ተውጠናል።

ወገን፤ የክፉ ሥራ ክፉትነት ላይ እንኳን አልተግባባንም እኮ፤ ክፉው ተግባር እኛ ጋር ሲሆን መቅለል ሌላው ጋር ሲሆን መግዘፍ እንዴት ይችላል? ክፉ ተግባርን ሁሌም ክፉ መሆኑ እንዴት ዘነጋን? አማኝ እኮ ከፍትሕ ጎን ነው የሚቆመው፤የእምነት ሰው እኮ በእውነት ላይ ነው የሚፀናው። በደሉ የተፈፀመው ከወገኑ በኩል እንኳን ቢሆን ከማያውቀውና የእውነትና የፍትህ ባለቤት ከሆነው ጋር ነው የሚቆመው። ደሞ በምንስ ስሌት ነው ይህ ሁሉ መከራና ስቃይ እያየን በአካባቢና በቦታ በክልልና በእምነት እየለየን ማልቀስና እየለየን ማውገዝ የተላመድነው።

የምንገድለውም የምንገደለውም እኛው ነን። የምንወቅሰውም የምንወቀሰውም እራሳችን። ይህ አያያዛችን ተያይዘን ማለቅ እንጂ አንዳችን በሌላችን ማለቅ ወይም መጎዳት የምናተርፍ ሊሆን አይችልም። ሀገራችን ሰላም እንድትሆን ሕዝባችን ሰላማዊ ኑሮውን እንዲቀጥል ሁላችንም የእውነት አማኝ እምነታችንም የሚይዘን በጎ ተግባር ላይ የምንገኝ በስሜት ሳይሆን በትክክለኛ እውቀት ላይ የቆምን የመርህ ሰዎች እንሁን።

የእምነት አባቶች የሌላውን መጥፎነት ከመግለፅ ምዕመናንን በበጎነት ስበኩ፤ የእምነት ተከታዩ ማኅበረሰብ የእምነታችሁ ስነምግባር ይላበስ ዘንድ መልካምን ነገር ስበኩ። አምላክ ምድር ላይ ያስገኘው ሁሉ በራሱ ፍቃድና መሻት ነውና እናንተ ሌሎችን በማጥፋት የእናንተ እምነትና ጎሳ ምቾት በፍፁም ሊያገኝ አይችልም። የሁላችንም እምነት በጎ መሥራት የሚደግፍ፣ ግፍ መሥራትና የሰው ልጆች መበደል የሚፀየፍ ነውና አማኞች በጎነት ላይ እንዲያዘወትሩ በርትታችሁ ሥሩ።

እምነት የሌለው ማኅበረሰብ እዚህ አገር ላይ የለምና የፖለቲካ ተሳትፎውም ላይ ያለው ከእያንዳንዱ እምነት የሚፈልቅ የሕዝብ አገልጋዩም መነሻው ማኅበረሰቡ ነውና፤ ተግባርና ሥራው የተበላሸ አሁን ላይ እንደምንሰማው ጭካኔ የተሞላበት ፈፅሞ ሊሆን አይችልም። የእምነት ስነ ምግባሩ የተሟላ ሰው የሌሎችን ሙሉ መብት ያከብራል።

ብዙዎች እምነት እንጂ አማኝነት ከእኛ የራቀ መሆኑን በብዙ ማስረጃዎች ያመላክታሉ። አሁን ላይ ያለንበት ዘርፈ ብዙ ችግር ደግሞ ዋንኛ የዚህ ማስረጃና ማሳያቸው ነው። አንድነትና ኅብረታችን መላላት፣ መደጋገፍና መረዳዳታችን መለዘብ፣ የእርስ በርስ ግጭትና ፍጅት መበራከቱ፣ መተሳሰብና መተጋገዛችን መላላቱ ለዚህ አስረጂ ምክንያት መሆኑን ይነግሩናል።

ትልቅ የቤት ሥራ አለብን ትውልዱን በስነምግባር መቅረፅ፣ እምነት ሳይሆን አማኝ በስነምግባር የታነፀ የሰዎችን መብት እንደራሱ የሚያከብርና የሚያስከብር ዜጋ መቅረፅ፣ የሰላማችን መደፍረስ ዋንኛ ምክንያት የሆኑና የሚያጣርሱን ከእርስ በርስ መግባባት የሚያርቁን ጉዳዮችን መመርመርና እዚያ ላይ መግባባት ላይ መድረስ።

ሀገራችንን ከወደድን ይህቺ ልዩና ካወቅንበት ገነት ማድረግና ለእያንዳንዳችን በበቂ ሁኔታ ሁሉም ማሟላት የምንችልባት ውዷ ሀገራችን እንድትበለፅግና ሰላምዋ እንዲረጋገጥ ከፈለግን ቀድመን ለሰላሟ ዘብ መቆም፣ አጥፊን በአንድነት ተው ማለት፣ የተሳሳተ ተግባር በጋራ መኮነንና ፍትሕ እንዲረጋገጥ መሥራት ይገባናል። ይህን ማድረግ ደግሞ ለሌላው የምንተወው ሳይሆን እኛው ተሳታፊ የምንሆንበትና የእያንዳንዳችን ተግባርና ኃላፊነት ሊሆን ግድ ይላል። እናም ወገን እምነት ያለን ብቻ ሳይሆን አማኞችም እንሁን፤ ትክክለኛ አማኝ ደግሞ ለሰዎች ሰላም ዘብ የሚሆን በእሱ መኖር ሌሎቹ የሚጠቀሙ እንጂ የሚጎዱ ፈፅሞ ሊሆን አይችልምና። ቸር ይግጠመን።

# ዓለም አቀፍ

## የአሜሪካ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት የጦር መሣሪያ ቁጥጥር ረቂቅ ሕግን አጸደቀ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የአሜሪካ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ከ30 ዓመታት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ በጦር መሣሪያ ቁጥጥር ላይ አዲስ ረቂቅ ሕግ አጸደቀ።

የዲሞክራቶችና የሪፐብሊካንን ጎራ የሚለየው የጦር መሣሪያ ቁጥጥር ጉዳይ ከረዥም ዘመን ትግል በኋላ ነው ለዚህ የበቃው። ይህ የሆነው ባለፉት ጥቂት ሳምንታት በተለያዩ የአሜሪካ ግዛቶች የተኩስ እሩምታን የከፈቱ ግለሰቦችን ተከትሎ በርካቶች ሕይወታቸውን ካጡ በኋላ ነው።

በኒውዮርክ፣ ቡፋሎ ባለፈው ወር በአንድ ሱፐርማርኬት ውስጥ ጥቁሮችን እየነጠለ ተኩስ የከፈተው ወጣት እንዲሁም በቴክሳስ፣ ዩቫልዲ ከተማ፣ በአንድ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በርካታ ሕጻናትን ጨምሮ በድምሩ 31 ሰዎች መገደላቸው የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው።

ረቂቁ በሚቀጥለው ሳምንት የታችኛው ምክር ቤት ከመከረበት በኋላ ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ፈርመውበት ሕግ ይሆናል። ይህም በሚቀጥሉት ጥቂት ቀናት ውስጥ የሚፈጸም ተግባር ነው። እዚህ ለመድረሱ ብዙ ውጣ ውረድ ቢያይም የታሰበውን ያህል አንጀት አርስ እንዳልሆነ በጉዳዩ ላይ ብዙ ሕዝባዊ ንቅናቄን ሲመሩ የነበሩ ተሟጋቾች እየተናገሩ ነው።

ረቂቁ አያሌ ውስንነቶች አሉበት የሚሉ የሕግ አዋቂዎችም ጥቂት አይደሉም። በቅርቡ ሲጸድቅ የጦር መሣሪያ ገዝቼ ማንገት እፈልጋለሁ የሚል ሰው በተለይ ዕድሜው ከ21 በታች ከሆነ የጀርባ ታሪኩ በብርቱ እንዲጠና ይደረጋል። ከዚህ ሌላ 15 ቢሊዮን ዶላር ከፌዴራል መንግሥት ለግዛቶች ይመደባል።

ይህም ከጦር መሣሪያ ቁጥጥር ጋር በተያያዘ ለሚከናወኑ ሥራዎች በሚል ፈሰስ የሚደረግ ነው። በተለይም በትምህርት ቤቶች አካባቢ የጥበቃ ቁጥጥርን ለማጠናከርና ለአእምሮ ጤና ማኅልበቻ መርሐ ግብር ማስፈጸሚያ የሚውል ይሆናል።

ከዚህ ሌላ ግዛቶች የደኅንነት ስጋት ናቸው ብለው ለሚያምኗቸው ግለሰቦች አስቀድመው ትጥቅ ማስፈታትን ያበረታታል።

ይህ "ሬድ ፍላግ" ተብሎ የሚጠራው የሕግ ሐሳብ ፖሊስ፥ ቤተሰብ ወይም የሥራ ባልደረቦችም ሊሆኑ ይችላሉ አንድ ግለሰብ ለደኅንነት ስጋት ነው ብለው በጽኑ ካሰቡ፣ የታጠቀውን መሣሪያ እንዲፈታ ጥያቄ የሚያቀርቡበት ዘዴ ነው።

ሌላው በዚህ ረቂቅ የተካተተው ፍቅረኛሞች፣ በመጠናናት ዘመናቸው ምናልባትም ከሁለቱ አንዱ ቀደም ብሎ የጾታ ጥቃት ታሪክ ያለው ሰው ከሆነ ከዚያ ወዲህ መሣሪያ እንዳይታጠቅ የሚከለክል ነው።

ከዚህ በፊት የፌዴራል ሕግ ያገቡ፣ ወይም ልጅ ያላቸው ወይም በእጮኛነት ደረጃ ያሉና በጾታ ጥቃት ታሪክ ያላቸው ሰዎችን ብቻ መሣሪያ እንዳይታጠቁ ክልከላ ያደርግ ነበር። አሁን በአዲሱ ረቂቅ ግን ይህ ሕግ አዲስ እየተጠናኑ ያሉ አፍላ ፍቅረኛሞች ጭምር እንዲያካትቱ ተደርጓል።

አሁን በሕግ መወሰኛ ምክር ቤት የመሣሪያ ቁጥጥር ረቂቁ በሰፊ ድጋፍ ማለፉ ልዩ ያደረገው። በርካታ ሪፐብሊካን እንደራሴዎች ለመሣሪያ ቁጥጥር ረቂቅ ይህን ያህል ድጋፍ ሲሰጡ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው።

በታሪክ ለዘመናት በዲሞክራቶች ይቀርቡ የነበሩ የመሣሪያ ቁጥጥር ረቂቅ የሕግ ሐሳቦች ወዲያውኑ በሪፐብሊካን ተወካዮች ውድቅ ሲደረጉ ኖረዋል።

የዲሞክራት እንደራሴዎች ተጠሪ ቸክ ሹመር "ይህ ረቂቅ ሕግ ማለፉ ሁሉን ችግር ይቀርፋል ባንልም ሐቀኛውን መንገድ መያዛችንን አመላካች ነው" ብለዋል። የብሔራዊ ጠመንጃ ማኅበር (NRA) ረቂቅ ሕጉን በጽኑ ተቃውሞታል።

ጆ ባይደን ውሳኔው የሚበረታታ ነው ቢሉም እሩምታ ተኩስ መክፈት የሚያስችሉ ዘመናዊ ጠመንጃዎች ላይ ዕቀባ እንዲደረግ የነበራቸውን ፍላጎት አለማሟላቱ ግን ቅር አሰኝቷቸዋል።

በቡፋሎም ሆነ በቴክሳሱ ጥቃት 31 ሰዎች የተገደሉት አከታትለው ጥይት በሚተፉ አውቶማቲክና ከፊል አውቶማቲክ መሣሪያዎችን ገዝተው በታጠቁ ወጣቶች ነበር።

በአሜሪካ አሁን በአማካይ በግለሰቦች እጅ 390 ሚሊዮን ጠመንጃና ሽጉጦች ይገኛሉ። በ2020 ብቻ 45 ሺህ አሜሪካውያን በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ በጦር መሣሪያ ተገድለዋል።




## በደቡብ አፍሪካ በዝንጀሮ ፈንጣጣ የተያዘ የመጀመሪያው ሰው ተመዘገበ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በደቡብ አፍሪካ የመጀመሪያው በዝንጀሮ ፈንጣጣ የተያዘ ሰው የተገኘ ሲሆን፣ አገሪቱ ከሞሮኮ በመቀጠል በአፍሪካ ወረርሽኙ የተገኘባት አገር ሆናለች።

በደቡብ አፍሪካ ውስጥ ከዚህ በፊት በሽታው መከሰቱን በተመለከተ ሪፖርት አልተደረገም። የአገሪቱ የተላላፊ በሽታዎች መቆጣጠሪያ ተቋም በጉተንግ አውራጃ የሚኖር የሰላሳ ዓመት ሰው ላይ በሽታው መገኘቱን ገልጿል።

ሰውዬው ከሌሎች ሰዎች ጋር የነበረው ንክኪ እየተጠና ሲሆን፣ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ወደ ሌሎች አገራት አለመጓዙም ተረጋግጧል። በሽታው ወደ ተከሰተባቸው አገራት ሳይጓዙ ወይም በአገር ውስጥ የዝንጀሮ ፈንጣጣ ወረርሽኝ ሳይኖር በአፍሪካ በበሽታው ሰዎች የሚያዙበትን ምክንያት ለማወቅ ተመራማሪዎች ጥረት እያደረጉ ነው።

የዝንጀሮ ፈንጣጣ ዝቅተኛ የመሰራጨት አቅም ያለው በሽታ ሲሆን፣ አብዝቶ የሚከሰተው በጥቅጥቅ ደን በተሸፈኑ እና ዝናብ በሚበዛባቸው ገጠራማ የምዕራብና ማዕከላዊ አፍሪካ ነው። በእነዚህ አካባቢዎች የሚገኙ እንደ አይጥ ያሉ እንስሳት ደግሞ በሽታውን ወደ ሰዎች ሊያስተላልፉ ይችላሉ ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው።

የዝንጀሮ ፈንጣጣ በበሽታው ከተያዘ ሰው ጋር በሚኖር የቅርብ ንክኪ ሊተላለፍ የሚችል ነው። ቫይረሱ በቆሰለ ቆዳ፣ በመራቢያ አካል ወይም በዐይን፣ በአፍንጫ እና በአፍ አማካኝነት ወደ ሰውነት ሊገባ ይችላል።

በዩናይትድ ኪንግደም የበሽታው ምልክት የሚታይባቸው ሰዎች ቫይረሱን ወደ ሌሎች እንዳያስተላልፉ ከወሲብ እንዲታቀቡ ተመክረዋል። የዝንጀሮ ፈንጣጣ ስርጭት በአፍሪካ በከፍተኛ መጠን እየጨመረ መሆኑን የአፍሪካ የበሽታ መቆጣጠሪያ ማዕከል ወይም ሲዲሲ አሳውቋል።

የማዕከሉ ዳይሬክተር ተወካይ ዶክተር አህመድ ኦግዌል ባለፈው ሳምንት በአህጉሪቱ በበሽታው እንደተያዙ የሚጠረጠሩ ሰዎች ቁጥር በ38 በመቶ፣ በበሽታው መያዛቸው የተረጋገጡ ሰዎች ደግሞ በ12 በመቶ መጨመሩን በሰጡት መግለጫ አስታውቀዋል።

በማዕከሉ የዚህ ዓመት መረጃ መሠረት እስካሁን አንድ ሺህ 571 ሰዎች በዝንጀሮ ፈንጣጣ እንደተያዙ ተጠርጥረው ነጻ ሲሆኑ 71 ሰዎች ደግሞ በሽታው ተገኝቶባቸዋል። 73 ሰዎች ከበሽታው ጋር በተገናኘ ለህልፈት ተዳርገዋል።

የዓለም ጤና ድርጅት የዝንጀሮ ፈንጣጣን የዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ የጤና ስጋት ስለመሆኑ ወይም ስላለመሆኑ የሚሰጠው ማብራሪያ እየተጠበቀ ነው። በተጨማሪም የቫይረሱ ስያሜን በመቀየር በሽታው ከአፍሪካ ጋር ተያይዞ እንዳይነሳ እየሠራ ነው።

ማህበራዊ

# መጋቢ አዕምሮ

# ለውጥ፤ በመውጣት

**በአገልጋይ ዮናታን አክሊሉ**

በወጣትነት እድሜ ላይ የምትገኝ ሴት ነች። በአካባቢዋ ለየት ባለው የለውጥ ሃሳብ አራማጅነቷ ትታወቃለች። ሕይወት የምትጣፍጠው በለውጥ ውስጥ ነው ብላ የምታምን ወጣት ነች። አንድ ሰው ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ለውጥን መከተል እንዳለበት የምትገልጽ፤ በአለባበስ፣ በአበላል፣ በመዋያ ቦታ፣ በቤት ውስጥ ያለውን ቁሳቁስ በማስተካከል፣ ወዘተ ለውጥ መኖር እንዳለበት ታምናለች። የቤቷን ዕቃ አቀማመጥ በየጊዜው በማድረግ የለውጥ ስሜት እንዲሰማት ታደርጋለች።

ወጣቷ አንድ ሰሞን የሆነን ቲቪ የምትከታተል ከሆነ በሌላ ጊዜ ሌላውን ታደርጋለች። የእንቅልፍ ሰዓቷን ከረጅም ወደ አጭር፤ ከአጭር ወደ ረጅም በማድረግ ለውጥን እንቅልፍ በማጣትም ሆነ እንቅልፍ በማብዛት ውስጥ ለማየት የምትሞክር። ለውጥ ስሜት አለው፤ ለውጥ ድምጽ አለው፤ ለውጥ ቅርብም እርቁም ነው ብላ የምትፈላሰፍ። የሕይወትን ትርጉም በለውጥ ውስጥ የምትፈልግ ዓይነት ሰው ነች።

አንድ ቀን በሰፈሩ ውስጥ ባለ ሱቅ ውስጥ ሄዳ ዕቃ ትገዛለች። የገዛችው ዕቃ ደግሞ ክብሪት ነበር። ክብሪቱን ተጠቅማ የመጀመሪያውን ሻማ ለኩሳ ማንበብ ጀመረች። ይህን የምታደርገው ከመብራት አምፖል ለየት ያለ ነገር ለማድረግ፤ እንዲሁም ሻማው ትኩረትን ሰብስቦ ለማሰብ ይጠቅማል የንባብንም ፍላጎት ይጨምራል ብላም ስለምታምን ነው።

ሻማውን እያየች በሀሳብ ፈረስ ተሳፈረች። የሀሳቡ ፈረስ አንድ ቦታ አደረሳት፤ በፖለቲካ ለውጥ ምክንያት ሕይወታቸውን ስላጡት አባቷ። አባቷ የደርግ ባለሥልጣን ነበሩ፤ ትውልዱ እርስበእርሱ ሲገዳደል እርሳቸውም ሕይወታቸውን አጡ። አባቷ «ትንንሽ ለውጦች ትልልቅ ለውጥ ያመጣሉ ሁሌም ለለውጥ ጥሩ ስሜት ይኑርሽ» እያሉ ይመክሯት ነበር።

ትንንሽ ለውጦችን መኖር የጀመረችው ከእዚያ ጊዜ በኋላ ነው። በመሠረታዊነት ጥቅምና ጉዳቱን የመዘነ ባይሆንም ለውጥን በበጎ የምትወስድ ለለውጥ ትልቅ ቦታ የምትሰጥ ሴት ነች። ትንንሽ ለውጦችን በየቀኑ ለማድረግ የምትሠራ።

ከአገራችን እልፍ ብለን ሌላውን ዓለም በምናይበት ጊዜ ለለውጥ የሚሰጡትን ከፍተኛ ትኩረት እናያለን። እንዴት ቢሠሩ ነው እንዲህ የተለወጡት የሚልም ጥያቄ ያጭራል። ለለውጥ ዝግ በሆነ ማህበረሰብ ውስጥ እድገት እንደሚታሰበው አለመሆኑንም እንረዳለን። ለውጥ ሁልጊዜ ተፈጥሮዊ ሆኖ የሚሳል ቢሆንም የሰዎች ፍቃድ ውጤት የመሆን ዕድሉ ግን ሰፊ ሆኖ እናገኘዋለን።

አንድ አካል ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ ባያደርግ እንኳን የለውጥ ስሜት ውስጥ የሚገባ መሆኑ ግድ ነው። ለውጥ ትልቅ አቅም ነው፤ ወደፊት መስፈንጠሪያ ተስፋ። ለውጥን የሚለማመድ የሕይወት ሥርዓት ይኖረን ዘንድ የተወሰኑትን እናንሳ። ጥንካሬና ድክመታችን ውስጥ የለውጥ አምጪነት ወይንም የለውጥ አደናቃፊነት ትርጉም አለ።

### ወደ ውስጥ ስንመለከት

ሁሉም ነገር ዛሬ ባለበት ሁኔታ ውስጥ ሆኖ አመታትን ሊቆይ አይችልም። ለውጥ ተፈጥሯዊ ወይንስ ሰው ሰራሽ የሚለውን የተለመደ ክርክር ወደ ጎን አድርገን የለውጥ መኖርን ግን የማንክድ ከሆነ ስለ ለውጥ ስናስብ ስለ ውስጣችን እናስባለን። የውስጥ እድገትም ሆነ ውድቀት ከለውጥ ጋር ቀጥተኛ ትርጉም ያለው መሆኑን በመረዳት።

አዲስ ነገርን ህልም ስናደርግ፤ አዲሱን ነገር በለውጥ ውስጥ እየፈለግን በጥንካሬና ድክመታችን ውስጥ ከመዳረሻው እንደርሳለን። በለውጥ ጉዞ እየተሻሻሉ መሄድን እናስባለን። እየተሻሻልን መሄድን የምናስብ ከሆነ መለወጥን እና ነገሮችን እያሻሻሉ መሄድ ይገባል። አዳዲስ ነገሮች ከጥንካሬ ጋር የተገናኙ ሊሆኑም ይገባቸዋል። በጥንካሬያችን ላይ አዳዲስ ነገሮችን እየጨመሩ መሄድ። ጥንካሬያችን ይበልጥ ጠንካራ እንዲሆን ማድረግ። ልዩነት መፍጠር የሚያስችል ጥንካሬ ላይ መድረስ።

በዘርፉ ላይ ጥናት የሚያደርጉ ባለሙያዎች 25% የሚሆነውን ጊዜህን፣ ኃይልህን፣ እና ሀብትን በጥንካሬህ ላይ አዳዲስ ነገሮችን በማድረግ ማዋል አዎንታዊ ለውጥን ለማምጣት እንደሚያስችል ይመክራሉ። ይህ ሲሆን የሚመጣው ለውጥ በእድገት ውስጥ ትርጉም ያለው ይሆናል።

የውጭ አቅማቸውን አውቀው በጥንካሬያቸው ላይ ትኩረት የማድረግ ችግር ያለባቸው ሰዎች ሁሉም ነገር ላይ ሲባትሉ ይገኛሉ። በባተሉበት ሁሉ ፍሬ ሊያገኙ አይችሉም። በጥንካሬያቸው ላይ የተመሠረተ መባተል ቢሆን በቀላሉ የፈለጉትን ነገር በቀላሉ ማሳካት ይችላሉ። የአንድ ነጋዴ ጥንካሬው ደንበኛ አያያዙ፤ ደንበኛ ተኮር ሆኖ አገልግሎትን ማቅረቡ ነው። አዲስ ነገር እዚያ ላይ እየጨመረ በሄደ ቁጥር እጅግ ጠንካራ መሆን ቻለ ማለት ነው። ምናልባትም በሳምንት ውስጥ አንድ እቁብ ሳይሆን ሁለት እቁብ መግባት የሚያስችል ጥንካሬ።

### ወደ ውስጥም ወደ ውጭም ስንመለከት

ወደ ውስጥ ስንመለከት ጥንካሬንና ድክመትን ከለውጥ አንጻር መመልከቱ ዋና ነገር ሲሆን ወደ ውጭም መመልከት ደግሞ ሌላው ቁልፍ ነጥብ ነው። ራስን መቀበል ወደ ውስጥም ወደ ውጭም የመቀበል ውጤት ነው። ሰዎች ሌሎች ሰዎች እነርሱን የሚያዩበትን መንገድ ተመልክተው ጉዟቸውን ሊገቱ ይችላሉ። ሰዎች ራሳቸውን የሚያዩበትን መንገድም ካላስተካከሉም በተመሳሳይ ሁኔታ እክል ይገጥማቸዋል።

ራስን መቀበል መቻል የሚበረታታ እያንዳንዱ ሰው ሊያደርገው የሚገባ ነው። ለራስ ቦታ መስጠት ተገቢነቱ እንዲሁ አያጠያይቅም። ፈጣሪም ባልንጀራችንን እንደ ራሳችን እንድንወድ ሲጋብዘን ለራሳችን ከምንሰጠው ቦታ ተነስተን መሆኑን መረዳት ይገባል። ለለውጥ የሚነሳ ሰው ለራሱ የሚሰጠው አመለካከት በራሱም ሆነ በሌሎች ሰዎች አመለካከት ያልተበላሸ ሰው ነው።

ሰዎች በመሠረታዊ ነገራቸው እኩል ናቸው። ነገርግን ባደጉበት ባህል፣ በሚናገሩት ቋንቋ፣ በእድሜያቸው፣ በጾታቸው፣ በትምህርት ዝግጅታቸው፣ በሚሠሩት ሥራ፣ ባላቸው ተሰጥዖ ወዘተ ሊለያዩ ይችላሉ። ሰዎች ከቆዳ ቀለማቸው ባሻገር በሰውነታቸው የሚጋሩት የጋራ ማንነት ከፍ ያለነው። በምድር ላይ ባሉ የሰውልጆች መካከል ያለው ልዩነት ካለን አንድነት አንጻር ፈጽሞውኑ ለውድድር የሚቀርብም አይደለም።

ሆኖም በታሪክ ውስጥ ለራስ ከሚሰጥ የተሳሳተ ትርጉም የተነሳ ብዙ ጥፋት ሲሆን አይተናል። የለውጥ መንገድን የሚያዛባ ጥፋት። ለራስ የሚሰጠው የተሳሳተ ትርጉም ራስን ከሌሎች የተለየ አድርጎ ማሰብ፣ ሌሎችን ከራስ በታች አሳንሶ ማየት፣ ሌሎች ከእኛ ተለይተው በሚታዩበት ልዩነት ምክንያት ከሰውነት አውርዶ መመልከት ወዘተ ነው። ለራስ የሚሰጥ የተለየ ትርጉም ያለንበትን ትክክለኛ ነባራዊ ሁኔታ እንዳንረዳና የተሳሳተ መንገድ ውስጥ እንድንገባ ያደርገናል። የተሳሳተው መንገድም ወደ አዎንታዊ ለውጥ ሳይሆን ወደ አሉታዊ ለውጥ ሊሆን የሚችል።

ለውጥን አስቦ ነገርግን ለውጥን ሌሎችን በማጥፋት ውስጥ በማለም ከሆነ ጉዳቱ ከፍ ያለ ነው። ይህን መሰል የለውጥ አስተሳሰብም ታሪክንም ዓለማችን መዝግባለች። ለራስ የተለየ ትርጉም ከመስጠት ውስጥ የወጣ። አይሁድን ከምድረገጽ ለማጥፋት የተዘረጋው ፕሮጀክት መነሻና መድረሻው ለራስ የተለየ ትርጉም መስጠት ነበር። ጣሊያን ኢትዮጵያን ዳግም ለመውረርና ለከፍተኛ ጥፋት ድግስ ውስጥ እንድትገባ ያደረጋት ለራስ የተለየ ትርጉም በመስጠት ነበር። የባሪያአሳዳሪ ሥርዓትን ከአሜሪካ ለማስቀረት የተደረገው ትግል ሚሊዮኖችን እንዲጨርስ የአሜሪካውን ፕሬዚዳንት አብርሃም ሊንከንንም በበቀል ለመግደል የተደረገው ለራስ በሚሰጠው የተለየ ትርጉም ነበር።

በቅርብ ጊዜ ታሪክ ውስጥ የፍሎይድ አሟሟት የቀሰቀሰው «የጥቁርም ሕይወት ይገዳል» የተሰኘው እንቅስቃሴ መነሻው ለራስ ከሚሰጥ የተለየ ትርጉም የተነሳ የተፈጠረን ኀዘን ለመግለጽ ነው። በአገር እንዲሁም በዓለምአቀፍ ደረጃ ካሉት ማሳያዎች ወደ አካባቢያችን እንዲሁም ቤተሰባችን ጉዳዩን ይዘን ብንመጣ የበረከቱ ማሳያዎችን ልናነሳ እንችላለን።

ራስን በመቀበልና ለራስ የተለየ ትርጉም በመስጠት መካከል ያለውን ልዩነት በመረዳት አዎንታዊ ለውጥን በመኖር ጤናማ ሕይወትን እርሱም ከሌሎች ጋር በሰላም የመኖርን ጥበብ ማግኘትን ይገባል። ብቻችንን ልንኖረው የምንችለው ሕይወት ምድር ላይ እንደሌለ በመረዳት በዙሪያችን ላሉት ሰዎች ከየትኛውም ልዩነት ባሻገር ትርጉም በመስጠት መኖርን መልመድ አለብን።

ሁላችንንም ያለብንን ውስንነት በመረዳት በውስንነት ውስጥ የምንኖር በመሆናችን መደጋገፋችን የግድ መሆኑን በመገንዘብ መኖር ብልህነት ነው። ራስን ውስንነት የሌለበት፤ ሌላውን ግን በውስንነት የሚኖር አድርጎ የመሳል ውስንነትን በማስወገድ ትርጉም ያለው ሕይወት ልንኖር ይገባል። የለውጥ ሕይወት ሌሎችን በምናይበት መንገድ ራሳችንንም መመልከት ነውና። ወደ ውስጥም ወደ ውጭም በመመልከት ለራስ ትክክለኛውን ትርጉም መያዝ ይገባናል።

ለውጥን በማምጣት ሂደት ውስጥ ሌላው ነጥብ ከልካዩን መረዳት ነው። በውስጣችን ለለውጥ ጥሩ ቦታ ሰጥተን ነገርግን ለውጥ ሆኖልን አናይ ይሆናል። ይህ የሚሆነው አንዳች ከልካይ በሕይወታችን ውስጥ ሲኖር ነው።

### ከልካዩን መከልከል

ለውጥን ስናስብ የምንኖርበትን ነባራዊ ሁኔታን ተረድተን ሕይወትን በአግባቡ መምራትን ይጠይቃል። ነባራዊ ሁኔታን ማወቅን ተከትሎ ሁኔታውን መቀበል ወይንም መቀየር ያለበትን ለመቀየር መነሳሳትን ያመጣል። ከነባራዊ ሁኔታ ግምገማ ውስጥ ከምናወጣቸው ነጥቦች መካከል አንዱ ለለውጥ በምናደርገው ጉዞ ውስጥ የሚገጥመንን ውስንነትን መረዳት ነው።

ውስንነት በምድር ላይ ባለ በየትኛውም አካል ላይ በተፈጥሮ ውስጥ የሚሰጥ የጋራ መገለጫ ነው። የሰው ልጅ ያለፈው ታሪኩ የሚያሳየን ውስንነቱን ለማሸነፍ የሚያደርገው ጥረት መኖሩን ነው። በሂደቱም ለውጥ እየተወለደ ይሄዳል።

ውስንነትን ሳይረዱ ለውጥን ማሰብ አንዳንዴ ውስን ሀብትን እንዲሁ ለማባከን የሚዳርግ ሊሆን ይችላል። አንዳንዱ ውስንነት ቀን በቀን የምናውቀው ሲሆን ሌላው ግን ድንገተኛ ክስተትም ሊሆን ይችላል። ሞክሮ ሞክሮ አልሳካ ሲል የምንቀበለው ውስንነት እርሱ የትህትናን መንገድ የሚያሳይ፤ በውስንነት ውስጥ የመኖርን ጥበብ መረዳትን የሚያመጣምነው።

አካላዊ ውስንነት፣ ከቤተሰብ የሚመጣ ውስንነት፣ በትዳር ሕይወት ውስጥ የሚገኝ፣ የጊዜ፣ የገንዘብ ወዘተ ብለን ለለውጥ መምጣት ውስን የሚሆንብንን ለይተን እንዴት መፍትሔ እንደምናገኝለት ማሰብ ያስፈልጋል። ከልካዩን ውስንነትን መከልከል ከቻልን የለውጥ እርምጃ ለመተለም አቅጣጫን መንደፍ ያስፈልጋል። ምን ዓይነት አቅጣጫን ተከትለን እንደምንራመድ የሚያሳይ።

### መስመሩን ማግኘት

ጉዞ ለማድረግ ተነስተን ከእዚህ በፊት ወደማናውቀው አካባቢ ለመሄድ ስንነሳ አቅጣጫውን ለማግኘት ጥረት እናደርጋለን። ለለውጥ አቅጣጫን ማግኘት ወሳኝ የሆነውን ያህል፤ አቅጣጫን መሳት ልብን ያደክማል። አቅጣጫ መሳት የሚያስከፍለውም ዋጋም ብዙ ነው።

በሕይወት ጉዟችን ውስጥ አቅጣጫ ከፍተኛ ቦታ የምንሰጠው ነገር ነው። አቅጣጫን ማስተካከል ጤናማ የለውጥ እቅድን ለመምራት ያግዛል። አቅጣጫን ማስተካከል ግን ለሁሉም ቀላል አይደለም። ስህተት እንደሆነ ከምናስበው ነገር ለመውጣት ከራሳችን ጋር መማማሉ የተለመደ ነው። ሆኖም ያሰብነውን ማድረግ ሳንችል ቀርተን ራሳችንን እናገኘውና እንገረማለን። አመት መጥቶ በሄደ ቁጥር በተሳሳተ መንገድ ውስጥ ያለው አቅጣጫችን እንዲስተካከል ተስፋ እናደርግም ይሆናል።

አቅጣጫ ፍለጋ በብዙ የሕይወት ክፍል ውስጥ ሊገጥመን ይችላል። በትዳር ሕይወት ጉዳይ፣ በሥራ ጉዳይ፣ በማህበራዊ ሕይወት፣ ከሱስ በመውጣት፣ ገንዘብ በመያዝ ወዘተ አቅጣጫ ፍለጋ ውስጥ እንሆን ይሆናል። ከትናንት ትምህርት ውስጥ የሚቀዳ ነገን ስናስብ መሆን ወደ ምንፈልገው እንድንደርስ የሚያደርግን እይታም የያዘ ነው። የአዲስ አመት ዋዜማ ውስጥ ያሉት ሳምንታትን በስፋት አእምሮችን በአቅጣጫ ፍለጋ ተሞልቶ እናየውም ይሆናል። አቅጣጫ ፍለጋ አስፈላጊ ነገር ነው፤ የለውጥ ጉዞ መስመር ነውና ።

ዛሬ ወደ ውስጣችን ስናዳምጥ በተሳሳተ መንገድ እንደሆንን የሚሰማን ምን ጉዳይ አለ? ውስጣችንን ባዳመጥን ቁጥር የሚያስቃስተንም ይሆን? እንዲህ ዓይነት



ስሜትን ተሸክመን ወደ አዲስ አመት ከመግባት ስሜቱን አዳምጦ መስተካከል የሚገባው ጉዳይ ላይ ውሳኔ ማሳለፍ ተገቢነት ይኖረዋል። በተደጋጋሚ ሞክረን ባልተሳካልን ነገር ተስፋ ወደመቁረጥ ከመሄድ የቀደመው ግምገማችን ውስጥ የነበረውን ጉድለት በመገምገም አሁንም ለሌላ ሙከራ በእችላለሁ መንፈስ በመነሳት የለውጥ አቅጣጫ ማስቀመጥ ያስፈልጋል።

አዲስ አመትን አዲስ የሚያደርገው፤ አዲስን ወር አዲስ የሚያደርገው፤ አዲስን ሳምንት አዲስ የሚያደርገው እንዲሁም አዲስን ቀን አዲስ የሚያደርገው በራሱ በቀኑ ሳይሆን በውስጣችን በሚፈጠረው አዲስ መነሳሳት ነው። አዲሱ መነሳሳት በጥንካሬ ሲሆን አቅጣጫ ፍለጋውን ያቀለዋል። አቅጣጫ ፍለጋው ወደ ውጤት ከመምጣት ባሻገር ነገ ላይ ለሚገጥመን ፈተና የሚረዳ ትምህርትን ከትናንት ማግኘት የምንችለው በአዲስ ልብ በመነሳሳት ነው።

አቅጣጫ ፍለጋ ውስጥ ብዙ ጊዜ የሚሠራ ስህተት ትናንትን ሙሉ ለሙሉ አፍርሶ እንደ አዲስ ነገሮችን ለመሥራት መሞከር ነው። በሕይወታችን እጅግ ውስን ጉዳዮች ብቻ ሙሉ ለሙሉ አፍርሶ መስራትን የሚጠይቁ ሊሆኑ ይችላሉ። በተጨባጭ ግን ሁሉንም ነገር አፍርሶ ለመሥራት መዘጋጀት አደጋ አለው። ትናንት ውስጥ ያገኘነው በጎነገር ላይ ተጨማሪውን እየጨምርን ወደፊት መራመድ ውስጥ የተሻለው ውጤት አለ። የተሻለው የሕይወት አቅጣጫ።

የተለምነው አቅጣጫ፣ ለራሳችን የምንሰጠው ቦታ፣ በጥንካሬና ድክመታችን ውስጥ ያለው ቁምነገር ወዘተ በልባችን ውስጥ ይብላላል፤ ለተግባር እርምጃም የሚያነሳሳን ይሆናል። ልባችን የለውጥ ማቀነባበሪያ ስፍራ ስለሆነ።

### የለውጥ ማቀነባበሪያ ስፍራ

ልብ የሕይወት መውጫ ተብሎ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ትርጉም ተሰጥቶት እናገኛለን። በልብ በኩል የሚወጣውና የሚገባው ረጅሙን አቅጣጫ የመወሰን ጉልበቱን በሚገባ የሚያሳይ ስለሆነ። ልባችን ውስጥ የሚሆነውን ስሜት ቃላት ሊገልጹ የማይችሉበት የሕይወት ጉዞ ውስጥ አልፈን ይሆናል፤ ምናልባትም በእዚህ ወቅት እያለፍን ያለን።

አንባቢው አሁን ባለበት ቦታ ሆኖ በዙሪያው ያሉትን ሰዎች ይቃኝ። በልባቸው ውስጥ ምን ይዘው እየኖሩ እንደሆነ ለማወቅ ይመርምር። ለውጥን ወይንስ ባሉበት ነገር ተመቻችቶ እዚያው አመታትን እየረገጡ መኖርን። በእርግጥ ከባድ ጥያቄ ነው። ልብ የሕይወት መውጫናት ሲባል የሕይወት መላ አቅጣጫ የሚብላላባት መባሉ ነው። የለውጥ ጉዞም የውስጥ መነካትን፤ ስለ ለውጥ ሊከፈል የሚገባውን የትኛውንም ዋጋ ለመክፈል መቁረጥን ወዘተ ይጠይቃል። በልባችን ውስጥ ተራራ የመውጣት ውሳኔ ሲኖር ለውጥ ዳር ይደርሳል። ስለሆነም ዛሬ ራሳችንን በመመልከት ስለ ለውጥ እናስብ፤ መሰናክሉን በሙሉ በመውጣት ወደ ሚደረስበት ከፍታ። ለውጥ በመውጣት!!!!

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# የጊዜን ጥቅም የተረዳው የጊዜሽወርቅ የስኬት መንገድ

ፍሬሕይወት አወቀ



ነገሮችን የምታስተውልበት አንዳች ልዩ ተሰጥኦ አይሉት ችሎታን ታድላለች። በቅርብ የሚያውቋት ወዳጆቿ እንዲያውም «ምትሀተኛ ነች» ይሏታል። እርሷ ባለችበት ሥራ፤ ሥራ ባለበት ሁሉ እርሷ አለች። ሌት ተቀን ለለውጥ ትተጋለች። ሥራ ነብሷ ነው። አዳዲስ የተባሉ ሥራዎች ሁሉ እርሷን ይሻሉ። እርሷም ለዚሁ ታደላለች። አንዱን ይዛ ሌላውን፤ እርሱን ሳትለቅ ደግሞ ሌላ ተግባር ላይ ታማትራለች። ከቴክኖሎጂ ጋር ባላት ጥብቅ ቁርኝት የተነሳ በሰከንዶች ሽርፍራፊ ለቁጥር የበዙ ተግባራትን ታከናውናለች።

መልከመልካምና ዘለግ ያለ ቁመና አላት። ከጸጉሯ ቀለም ጀምሮ የፊቷ ቅላት የውጭ ዜጋ አስመስሏታል። ሰው አክባሪ፣ ተጫዋችና ተግባቢ ናት። ትህትናን ገንዘብ ያደረገ ማንነትም አላት። ቀጠሮ አክባሪና ለጊዜ ትልቅ ዋጋ በመስጠቷ ምክንያት ከልባችን ምት እኩል ከሚነጉደው ጊዜ ጋር አብራ ትጓዛለች። ትወጣለች ትወርዳለች። «ስምን መልአክ ያወጣዋል» እንዲሉ ምግባሯ ከመጠሪያ ስሟ ፍጹም የተስማማ ነው። ጊዜሽወርቅ ተሰማ ትባላለች። የዝግጅት ክፍላችንም የዕለቱ የስኬት እንግዳ አድርጎ መርጧታል።

ጊዜሽወርቅ፤ አዲስ አበባ ከተማ ልዩ ስሙ ተክለሃይማኖት አካባቢ ነው ተወልዳ ያደገችው። ከትምህርት ሁሉ የጎበዝ ተማሪ መለያ የሆነውን የሒሳብ ትምህርት አብልጣ ትወዳለች። ልዩ ተሰጥኦም አላት። ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ጀምራ አብሯት ያደገው የሒሳብ ትምህርት ችሎታ ዛሬ ለደረሰችበት የስኬት ማማ ዓይነተኛ ሚና ተጫውቷል። የሒሳብ ትምህርት ጥልቅ ዕውቀቷና ፍላጎቷ ባለምጡቅ አዕምሮ ትንታግ ሳያደርጋት አልቀረም።

እስከ ስምንተኛ ክፍል በነበራት የላቀ ውጤት የ9ኛ እና 10ኛ ክፍል ትምህርትን እንደእርሷ ጎበዝ ተማሪ ሆነው ከተመረጡ መሰሎቿ ጋር የፋይናንስ ትምህርትን ተምራለች። 10ኛ ክፍል ስትደርስም ከመላው አገሪቱ ከተመረጡ ጎበዝ ተማሪዎች መካከል አንዷ ሆና ወንዶችን ብቻ ይቀበል ከነበረው ጀነራል ዊንጌት ትምህርት ቤት ከጥቂት ሴቶች መካከል አንዷ ሴት ተማሪ በመሆን ተቀላቅላለች።

በሂሳብ ጉብዝናዋ ምክንያት አካውንቲንግ መማር የምትፈልግ ቢሆንም በወቅቱ የወጣላት ዕጣ ግን ሴክሬቴሪያት ሆኖ ተገኘ። ለሒሳብ ትምህርት ያላትን ፍቅር፣ ፍላጎትና ችሎታ ለርዕሰ መምህሩ በማስረዳት ወደ አካውንቲንግ ትምህርት ክፍል ለመመለስ ጥያቄ አቀረባለች። ጥያቄዋን ተከትሎም ከፍላጎቱ ውጭ የተመደበ ተማሪ እንደየ ዕምነቱ የዕምነት መጽሐፍትን በመምታት እንዲመለስ ሆነ።

በዚህ ወቅት ታድያ መጽሐፍ ቅዱስን በምስክርነት በመምታት ወደ አካውንቲንግ ትምህርት ክፍል ለመመለስ ቀዳሚ ያልነበራት ጊዜሽወርቅ፤ የነብስ ጥሪዋ የሆነውን የአካውንቲንግ ትምህርት ክፍል ተከታትላ በዲፕሎማ ተመርቃለች። ትምህርቱን ባጠናቀቀች ማግስትም እርሷን ጨምሮ ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ስድስት ተማሪዎች ጅማ የእርሻ ምርምር የሒሳብ ሠራተኛ ሆነው ተቀጥረዋል።

ገና በጠዋቱ ወደ ሥራ ዓለም የገባችው ጊዜሽወርቅ፤ በመጀመሪያ ደመወዟ ወላጅ እናቷ የሚወዱትን ዓይነት ቀሚስ መግዛቷን ታስታውሳለች። በወቅቱ የነበራትን ደስታ ስታስታውስም አሁን የሆነ ይመስል ስሜቷ ከገጿ ይነበባል። ወላጅ እናቷ ሦስት ወንዶች ልጆቻቸውን ሞት ከወሰደባቸው በኋላ የተገኘች ብርቅዬና ፈጣኗ ልጅ ተወልዳ በተመለከቷት ቅጽበት «ይቺማ ጊዜሽወርቅ ናት» ያሏትም ወላጅ አባቷ አቶ ተሰማ ናቸው።

ከትምህርቷ ባለፈ በቤት ውስጥ ሥራም ጎበዝና ባለሙያ እንደሆነች የምታስታውሰው ጊዜሽወርቅ በዚህ ምክንያትም ገና ተማሪ እያለች በተደጋጋሚ ባል ይመጣላት እንደነበርም አጫውታናለች። እርሷም ሆነች ወላጅ አባቷ ግን በትምህርቷ መግፋት እንዳለባት ነው የሚያምኑት። ስለሆነም አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ገብታ ትምህርቷን በቀጠለች ጊዜ ለትዳር የሚጠይቋትና የሚዝቱባት ሰዎች በዙ። በዚህ ጊዜ ታዲያ ወላጅ አባቷ አማራጭ ነው ያሉትን የውጭ አገር ጉዞ አመቻቹላት። አጋጣሚው ለሒሳብ ያላትን እምቅ ችሎታና ልዩ ተሰጥኦ በግልጽ ማወቅና አውጥታ መጠቀም እንድትችልም ምቹ ሁኔታን ፈጥሮላታል።

ለመጀመሪያ ጊዜ በሄደችበት አልአይን የእንግሊዝ ጋዜጦችን ስታገላብጥ በአካውንቲንግ ጎበዝ የሆነንና በራሱ የሚተማመን ሰው የሚጋብዝ የሥራ ማስታወቂያ ተመለከተች። በሒሳብ ችሎታዋ የምትተማመነው ጊዜሽወርቅ አላመነታችም አመለከተች። ብዙዎች «እረ ተ...ይ... የእንግሊዞች ካምፓኒ ነው አንቺኮ ኢትዮጵያዊ ነሽ» ቢሏትም እርሷ ግን እነሱን ሳይሆን ልቧን አድምጣ የመጀመሪያዋ ኢትጵዮጵያዊ በመሆን ከእንግሊዞች ካምፓኒ ሰተት ብላ በመግባት የነብሷ ጥሪ የሆነውን የሒሳብ ሥራዋን መሥራት ጀመረች።

በካምፓኒው በነባራት የ15 ቀን ቆይታ ታድያ በሥራዋ ብቃት ስሟን በከፍተኛ ደረጃ አስጠራች። የማያባራው ፍጥነቷም ወደ ቀጣይ ድል አድራጊነት ሊመራት ያንደረድራት ጀመር በዚህ ወቅት ከምታገኘው ገቢ ለትምህርት ቤት እየከፈለች ከሥራዋ ጎን ለጎን የማኔጅመንት ትምህርቷን አስቀጥላለች። በአጭር ጊዜ ትምህርት ማኔጅመንትን ጨምሮ ማንኛውንም ዓይነት ስልጠና መሰልጠን ቻለች። ይሄኔ ይበልጥ እራሷን ማብቃት የቻለችው ጊዜሽወርቅ፤ በፈለገችው ጊዜ በማንኛውም ቦታ መሰለፍ የምትችል መሆንኑ አረጋገጠች።

እሷን የመሰለ ፈጣን ሰው አገሩ ቢገባ ብዙ ሥራ መሥራትና ለውጥ ማምጣት የሚችል እንደሆነ ከአንድ ኢትዮጵያዊ ያደመጠችውም በዚህ ወቅት ነበር። ወጣትነት በራሱ ከሚሰጠው ኃይል በተጨማሪ እጅጉን ለምትታትረው ፈጣኗ ጊዜሽወርቅ፤ መልዕክቱ ቀላል ግምት የሚሰጠው አልነበረምና በዚያው ቅጽበት ወደ ኢትዮጵያ አቀናች። እንደተባለው ኢትዮጵያ ውስጥ መሥራት የምትችለው ሥራ ምን እንደሆነ በውል ባታውቀውም አዲስ አበባን ከእግር እስከ ራሷ በእግሯ እየዞረች ቃኘቻት።

ለመጀመሪያ ጊዜ ከኦሮሚያ ፋይናንስ ቢሮ እግር ጥሏት ስትገባ ወረቀት ይዘው ከወዲህ ወዲያ የሚሉ ሴቶች ትመለከታለች። ምክንያቱ ደግሞ ታይፕራይተር ፍለጋ ነው። ፈጣኗ ጊዜሽወርቅ፤ ሥራ አስኪጁ ጋር ቀርባ ቀልድ የሚመስል ጥያቄ «ታይፕራይተር ከጀርመን አገር ላስገባላችሁ» ስትል ጠየቀች። ምላሹን ሳትጠብቅ ፕሮፎርማ ሰብስባ ከሁሉም ባነሰ ዋጋ ለማስመጣት ቃል ገባች። ሥራ መሥራት እንደምትችል ማሳየት የፈለገችው ጊዜሽወርቅ፤ ትርፍ የማግኘት ሂሳብ ውስጥ አልገባችምና ከጀርመን ካምፓኒዎች ጋር ተጻጽፋ ቃሏን በተግባር አስመስክራ በዚህም እራሷን አስተዋወቀች።

ከዚህ በኋላ መሰል ሥራዎች እሷን ብለው እየተግተለተሉ ይጎርፉ ጀመር። እችላለሁ የሚል ወኔዋን ሰንቃ ለማንኛውም ጥያቄ ፈጣን ምላሽ ያላት ጊዜሽወርቅ፤ ከጃፓን መኪናን ጨምሮ የተለያዩ ጨረታዎችን በመወዳደር መንግሥትን ከወጪ የሚያድን ሥራዋን በልበ ሙሉነት ታሳልጠው ጀመር። ሥራ ባለበት ሁሉ የምትገኘው ጊዜሽወርቅ፤ አንደኛው ሥራ ሌላ ሥራ እየወለደላት በበርካታ ዘርፎች ተሰማርታ ውጤታማ መሆን ችላለች።

ወቅቱ በሁሉም የሥራ ዘርፎች ከፍተኛ መነቃቃት መታየት የጀመረበት እንደመሆኑ በርካታ ሥራዎችን በቀዳሚነት ማከናወን ችላለች። ለአብነትም ከግለሰብ በተበደረችው 15 ሺ ብር በ500 ብር ወረቀት እና በ14500 ብር ደግሞ ፎቶ ኮፒ ማሽን በመግዛት ወቅቱ የሚጠይቀውን የፎቶ ኮፒ ሥራን ተቆጣጠረችው። በዚሁ ሥራ ላይ ሆና የተዋወቀቻቸው የውጭ ዜጎች ፍጥነቷንና ቅልጥፍናዋን አስተውለው አብራቸው እንድትሠራ ያሳዩትን ፍላጎት ተቀበለች። በወቅቱ ጊዜ የፈጀባቸውን የህትመት ጥራዝ በተለያዩ ማተሚያ ቤቶች ወስዳ ባጠረ ጊዜ ከእጃቸው አስገባች። በዚህ ጊዜ ታድያ ማንኛውንም ነገር መሥራት እንደምትችል በተግባር ከማረጋገጥ ባለፈ ጠቀም ያለ ገንዘብም ከነጮቹ ማግኘት ችላለች።

በሥራዋ አጋጣሚ ሁሉ ከምታገኛቸው ሰዎች በተለይም ከውጭ ዜጎች ጋር በቀላሉ መግባባት በመቻሏና ባላት ቅልጥፍና አጠቃላይ ሥራዋ ከተለያዩ የውጭ ዜጎች ጋር ሆነ። ኢትዮጵያ ውስጥ የተለያዩ የግንባታ ሥራዎችን ሊሠሩ ከመጡ የውጭ ዜጎች ጋር አብራ ለመሥራት ቀዳሚ አልነበራትም። ከውጭ ዜጎች ጋር ጥብቅ ትስስር የነበራት ጊዜሽወርቅ፤ በተለይም ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ አየር መንገድ በሚገነባበት ወቅት በሎጅስቲክስ ሥራ ትልቅ ድርሻ ነበራት ቢባል ማጋነን አይሆንም።

ሌሎች ትላልቅ ሥራዎችንም እንዲሁ በኃላፊነት እየወሰደችና ለሌሎች እያከፋፈለች ሥራዋን ማስፋፋት ቀጠለች። እንቅልፍ የሌላት ጊዜሽርቅ፤ ለመንገድ ሥራም ይሁን ለሌሎች የግንባታ ሥራዎች ወደ አገሪቱ ከመጡ የውጭ ዜጎች ጋር በመሆን የተለያዩ ግብአቶችን ከአገር ውስጥና ከውጭ አገር በማስመጣት ሰፊ አበርክቶ ነበራት። በርካታ የአውሮፓ አገራትና አሜሪካ የመመላለስ ዕድል አግኝታለች። በተለይም አልላይንና አሜሪካ በርካታ ጊዜያትን አስቆጥራለች።

አጋጣሚው የፈጠረላትን ሁሉ ወደ ሥራ በመቀየር በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ተሰማርታ ፍሬ ማፍራት የቻለችው ጊዜሽወርቅ፤ ጊዜ ስቴሽነሪ ከሚለው አነስተኛ ድርጅት ጀምራ ጊዜ ትራቭል ኤንድ ቱሪዝምንም ከፍታለች። በዚህ ጊዜ ታድያ ከ2000 በላይ ለሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል ከመፍጠር ባለፈ በርካታ የውጭ አገር አምባሳደሮችን የመተዋወቅ ዕድልም አግኝታለች። ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ በርካታ የውጭ ዜጎች በሎጅስቲክስ ዘርፍ የሚያገኙት አገልግሎት በቂ አለመሆኑን ባነሱበት ወቅት አገልግሎቱን ተደራሽ ለማድረግ ወስና አስፈላጊውን ስልጠና በመውሰድ ሎጅስቲክስና ሺፒንግ ድርጅት አቋቋመች። መማርና መሥራት የነብሷ ጥሪ በመሆኑ ስለ ጉምሩክ ተምራ አገልግሎቱን ተደራሽ ማድረግ ችላለች።

ከትምህርቱ ባሻገር በተፈጥሮ የተሰጣትን ፍጥነት፣ ቅልጥፍናና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታዋን ተጠቅማ የውጭ ዜጋ የሆኑ ደንበኞቿ የሚፈልጉትን ማንኛውም ግብዓት ከዓለም ዙሪያ በማሰባሰብ ታቀርብ ጀመር። በዚሁ ድርጅቷም ኢትዮጵያን ወክላ በበርካታ የዓለም መድረኮች ተቀምጣለች። «ይሄኔ ሎጅስቲክስና ሺፒንግ ለእኔ የተፈጠረ ሥራ እንደሆነ አመንኩ» የምትለው ጊዜሽወርቅ፤ የዩናይትድ ኔሽን እና የዓለም ባንክ የኢትዮጵያ ተወካይ በመሆን ወደብ የሌላቸው አገራት ያላቸውን ችግርና መፍትሔዎቹ በሚለው የውይይት መድረክ ኢትዮጵያን ወክላ ተሳትፋለች።

ከዚህ በኋላ ከፍተኛ ተቀባይነትን ያገኘችው ጊዜሽወርቅ፤ በዓለም መድረክ አግዋን ጨምሮ በብዙ መድረኮች ላይ የተለያዩ ጉዳዮች ላይ ስለ ኢትዮጵያ ሞግታለች። በዚህም በርካታ ሰርተፍኬቶችን አግኝታለች። በደረሰችበት ሁሉ ሥራ ሥራን እየወለደ በአገሪቱ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ላይ የመሰማራት ዕድል ያጋጠማትና ከፍተኛ ፍላጎትም ያላት ጊዜሽወርቅ፤ በኢነርጂ ኢንቨስትመንትም ተሰማርታለች። ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር አስፈላጊውን ሁሉ በማሟላት የውጭ ባለሀብቶቹ ወደ አገር ውስጥ ገብቶ ሥራውን ለመጀመር በዝግጅት ላይ ይገኛሉ።

አማርኛ፣ እንግሊዝኛና አረብኛን አቀላጥፋ የምትናገረው ጊዜሽወርቅ፤ ወርቅ የሆነውን ጊዜ በአግባቡና ተጠቅማ ሁሉም ቦታ አለች። አሁን ደግሞ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በከተማው የሚስተዋለውንና ፍጹም አልታረቅ ያለውን የመኖሪያ ቤት አቅርቦትና ፍላጎት ለማስታረቅ ከባለሀብቱ ጋር በጋራ ተቀናጅቶ መሥራትን አንደኛው አማራጭ አድርጓል። ለዚህም ታድያ ትጉና ታታሪዋ ጊዜሽወርቅን ጨምሮ ሌሎችም ተመርጠው ከአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ጋር ሥራ ጀምረዋል።

ዕውቀታቸውን፣ ጊዜያቸውንና ገንዘባቸውን ተጠቅመው አገራቸውን ማገልገል ከሚፈልጉ ሰዎች መካከል አንዷ ነኝ ከማለት ባለፈ በተግባርም አገሯን ዘርፈ ብዙ በሆኑ ተግባራት እያገለገለች ያለችው ጊዜሽወርቅ፤ በተለይም በፋይናንስ ዘርፍ ያላትን እውቀትና የሰው ሀብት ተጠቅማ የጋራ መኖሪያ ቤቶችን መገንባት የሚያስችል ከውጭ ባለሀብቶች ለማምጣት ኃላፊነት ወስዳ ደፋ ቀና ትላለች።

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ አንደኛው ልጇ የሆነ ያህል የሚሰማት ጊዜሽወርቅ፤ ለግድቡ ግንባታ ከባለሀብቶች ገንዘብ በማሰባሰብ በኩል ከፍተኛ ድርሻ ያላትና አሁንም በግድቡ ዙሪያ በመጻፍ ከፍተኛ ንቅናቄ እያደረገች ትገኛለች።

«አገር ካለኛ ማንም የላትም» የምትለው ጊዜሽወርቅ፤ በአገር ውስጥ ሠርቶ መለወጥንና አገርን መለወጥ ማሳደግ እንደሚቻል ሙሉ ዕምነት አላት። ለብዙዎች መትረፍም ያስደስታታል። ለዚህም ሲባል አገርና ሕዝብን ይጠቅማል በተባለ ማንኛውም ዘርፍ ላይ ትሰማራለች። በቀጣይም የጀመረቻቸውን ሥራዎች አጠናክራ በውጤት የመፈጸምና ኢትዮጵያን በሁሉም ዘርፈ ከፍ የማድረግ ዕቅድ አላት።

ለሴቶችም ልዩ ምልከታ አላት። በዚህ ምክንያት አገርን ማቆም የቻሉ ሴቶች እንደሆኑ ተናግራ ዕምቅ ችሎታና ብቃት አላቸው ትላለች። በተለይም ወጣቱ በአገር ውስጥ ሰርቶ መለወጥ እንደሚችልና እያንዳንዱ ዕድል አጠገቡ እንደሆነ በመምከር በውጭው ዓለም በግልጽ የማይታይ ቅኝ ግዛት ስለመኖሩ በበርካታ አገራት የነበራትን ቆይታ ምስክር በማድረግ ወጣቱ ከስደት ይልቅ በአገሩ ሰርቶ መለወጥ የሚያስችሉ በርካታ ዕድሎችን እንዲያማትር መክራለች።

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## የመሠረተ ልማት ግንባታ በቅንጅት ማከናወን፤ ወጪና ጊዜ ለመቆጠብ

መላኩ ኤሮሴ



ባለፉት ጥቂት አስርተ ዓመታት በሀገራችን በመንገድ፣ በቴሌ፣ በባቡር እንዲሁም በኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት ዘርፎች ሰፋፊ የመሠረተ ልማት ዝርጋታ ተከናውኗል። በተሠሩ ሥራዎችም የሀገሪቱ የመሠረተ ልማቶቹ ሽፋን ከፍ ብሏል። እነዚህ መሠረተ ልማቶች የሀገሪቱ ስም በመልካም እንዲነሳ ያደረጉ ናቸው። ይሁን እንጂ በሀገራችን የመሠረተ ልማት ዝርጋታን የሚያካሄዱ ተቋማት መካከል በቅንጅት የመሥራት ከፍተኛ ችግር ያለባቸው በመሆናቸው በተለያዩ ወቅቶች የተለያዩ ችግሮች ተስተውለዋል።

በተለይም በከተሞች አካባቢ የመንገዶች፣ የኤሌክትሪክ፣ የቴሌ እና የውሃ መሠረተ ልማቶች በሚዘረጉበት ወቅት ችግሩ በግልጽ ይታያል። አንዱ የራሱን መሠረተ ልማት ከዘረጋ በኋላ ሌላኛው ተቋም ደግሞ የተዘረጋውን መሠረተ ልማት በማፍረስ የራሱን መሠረተ ልማት ሲዘረጋ ማየት የተለመደ ነው። ጉዳዩን እጅግ አሳሳቢ የሚያደርገው ደግሞ ሀገሪቱ ያላትን አንጡራ ሀብት በማፍሰስ የምትገነባቸው መሠረተ ልማቶች ወራት እንኳ ሳይቆዩ ለሌላ መሠረተ ልማት ዝርጋታ መፍረሳቸው ነው።

በዚህ ሁኔታ ከአንዴም ሁለቴ ወይም ሶስት አራቴ ፈርሰው የሚገነቡ መሠረተ ልማቶች አሉ። የዚህ ችግር ዋነኛ ሰለባ እየሆነ ያለው የመንገድ መሠረተ ልማት ነው። አንድ የመንገድ ፕሮጀክት ተገንብቶ በተመረቀ በወራት ውስጥ ለኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ ወይም ለውሃ መስመር ዝርጋታ ወዘተ ሲፈርስና ሲጠገን ማየት የተለመደ ነው። መንገዶቹ ፈርሰው ዳግም ሲጠገኑ እንደ መጀመሪያው ሊሆን ስለማይችል በአጭር ጊዜ ለብልሽት የመዳረግ እድሉ ላቅ ያለ ነው።

ለተለያዩ መሠረተ ልማቶች ዝርጋታ ተብሎ በተለያዩ አካባቢዎች የሚቆፈረው መንገድ ተመልሶ በአግባቡ ስለማይጠገን እና ጉድጓዶች በአግባቡ አለመደፈን እና ድንጋዮች በአግባቡ ቦታቸውን እንዲይዙ ስለማይደረግ ለትራፊክ አደጋዎች መንስኤ ሲሆንም ይታያል።

የቅንጅታዊ አሠራር አለመኖር መሠረተ ልማቶቹ ለማኅበረሰቡ ኑሮ መሻሻልና ለሀገሪቱ ልማት መፋጠን የሚጠበቀውን ያህል እንዳያበረክት እንቅፋት መሆኑም አልቀረም። ከዚያ አለፍ ሲልም ለጊዜና ለገንዘብ ብክነት መንስኤ ከመሆን አልፎ ለሌሎች ችግሮች መንስኤ ሲሆንም ታይቷል።

በቅንጅታዊ አሠራር እጦት ሳቢያ የፕሮጀክቶች ግንባታ መጓተት ሀገሪቱ በብድር፣ በእርዳታና በውስጥ ገቢ የምታገኘውን ውስን ሀብት ለታለመለት ዓላማ እንዳታውል ስለሚያደርግ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ የራሱን አሉታዊ ጫና ያሳድራል።

ችግሩ የሰነበተ ሲሆን፤ አዲስ አበባን ጨምሮ በተለያዩ የክልል ከተሞች ዛሬ በስፋት የሚታይ ክስተት ነው። አንዳንድ ጊዜ በተቋማቱ መካከል አለመናበብ በመኖሩ ምክንያት የሚከሰቱ ችግሮች ሲታይ ተቋማቱ በአንድ መንግሥት ይመራሉ? እና ለአንድ ሀገርስ ነው የሚሠሩት የሚል ጥያቄ እንዲነሳ የሚጋብዝ ነው።

በቅርቡ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤታቸውን የ10 ወራት አፈጻጸም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀረቡት የከተማ እና መሠረተ ልማት ሚኒስትሯ ወይዘሮ ጫልቱ ሳኒ እንደተናገሩት፤ ችግሩ ዛሬም ቀጥሏል። በዚህም ምክንያት የጊዜ እና የገንዘብ ብክነት እየተከሰተ ነው።

ይህም ከፍተኛ የጊዜ ብክነት እና ከፍተኛ የገንዘብ ወጪ ከማስከተሉም ባሻገር የመልካም አስተዳደር ችግር እያስከተለም ይገኛል። የሕዝቡ ምሬት ምንጭ ሲሆን ይታያል።

የዘርፉ ባለሙያዎች እንደሚናገሩት የችግሩ ዋነኛ መንስኤዎች ሀገራዊ የቅንጅት ማስተር ፕላን ያለመኖር፣ ሀገራዊ የቅንጅት ስታንደርዶች ያለመኖር፣ መሠረተ ልማት ፈጻሚ ተቋማት የተሟላና የተደራጀ መረጃ ያለመኖርና መረጃዎች ቢኖሩም እንኳ ያለመናበብ ችግር ከዋና ዋና መንስኤዎች መካከል ተጠቃሽ ናቸው።

በዚህም ምክንያት የመሠረተ ልማቶች ዝርጋታ በማስተር ፕላን የማይመሩ መሆናቸውን የዘርፉ ባለሙያዎች ይናገራሉ። የሚገነቡ መሠረተ ልማቶች በማስተር ፕላን የሚመራ ቢሆን አንዱ ተቋም የራሱን መሠረተ ልማት በሚዘረጋበት ወቅት ለሌላኛው መሠረተ ልማት ዝርጋታ የሚሆን ቦታ ሊያስቀር ይችላል።

መሠረተ ልማቶችን መገንባት፣ ማደስ እና መጠገን ብቻ ሳይሆን መሠረተ ልማትን በሚዘረጉ ተቋማት መካከል ቅንጅታዊ አሠራርን መዘርጋት ላይ ማተኮር ለነገ የማይባል አንገብጋቢ ጉዳይ ነው። በተለይም ከመንገድ ሥራ ፣ ከኤሌክትሪክ ግንባታና ከቴሌኮሙዩኒኬሽን መሠረተ ልማት ግንባታ ጋር ተያይዞ የሚሠሩ ሥራዎች አቀናጅቶ መምራት መቻል በመሠረተ ልማት ዘርፍ ከዋጋ፣ ከጥራትና ከጊዜ አኳያ የተሻለ ጥቅም እንደሚያስገኝ እሙን ነው።

በርካታ መሠረተ ልማቶች በቅንጅት በጋራ በሚዘረጋበት ወቅት ለተለያዩ መሠረተ ልማቶች ዝርጋታ ለየብቻ የሚወጣውን ወጪ በማስቀረት በአንድ ላይ ወጪ እንዲደረግ ስለሚያስችል ከፍ ያለ ፋይዳ አለው።

በቅንጅታዊ አሠራር እጦት ምክንያት እየደረሰ ያለውን የወጪና የጊዜ ብክነት ለመከላከል የተለያዩ ጥረቶች እየተደረጉ መሆኑን በቅርቡ በፓርላማ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤታቸውን የ2014 በጀት ዓመት የ10 ወራት አፈጻጸም ሪፖርት ያቀረቡት የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትሯ ወይዘሮ ጫልቱ እንደተናገሩት፤ ችግሩን ለመቅረፍ ጥናት እየተካሄደ ሲሆን፤ በቅንጅታዊ አሠራር እጦት ምክንያት እየተከሰተ ያለውን የጊዜና የወጪ ብክነት የሚያሳይ ጥናት እየተካሄደ ሲሆን ጥናቱ በአሁኑ ወቅት 85 በመቶ ተጠናቋል።

ይህ ጥናት የችግሩን መሠረታዊ መንስኤዎችን ከመለየት ባሻገር የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ያመላክታል ተብሎ ተስፋ የተጣለበት ነው። በቅንጅት አሠራር እጦት ምክንያት የሚከሰተውን የጊዜና የገንዘብ ብክነት በማስቀረት የመሠረተ ልማት ዘርፉን በከፍተኛ ሁኔታ የሚያግዝ ይሆናል።

ጥናቱ በአስቸኳይ እንዲጠናቀቅ አስፈላጊው ርብርብ ሊደረግ ይገባል። ጥናቱ ብቻውን በራሱ ችግሩን ለመቅረፍ ስለማያስችል ጥናቱን ተጨባጭ ለውጥ እንዲያመጣ በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋል ያስፈልጋል። ጥናቱ ሲጠናቀቅም የጥናቱን ግኝቶችን ሳይሸራረፍ በመተግበር ችግሩን በዘላቂነት ለመቅረፍ የሚመለከታቸው አካላት ዝግጁ መሆን አለባቸው።

ሚኒስትሯ አክለውም ባለፉት 10 ወራት 71 ፕሮጀክቶች በቅንጅትታዊ አሠራር፣ በካሳ ክፍያ፣ በዲዛይንና በወሰን ማስከበር ዙሪያ የነበሩባቸውን ችግሮች የሚያቃልል ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ተችሏል። ይህም እንደ ትልቅ ስኬት የሚታይ ነው። ችግሩን ለመቅረፍ የሚደረጉ ጥረቶችም ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው።

በቅንጅታዊ አሠራር እጦት የሚስተዋሉ ችግሮችን በዘላቂነት መፍታት እስኪቻል ድረስ ጊዜያዊ የመፍትሔ እርምጃዎች ሊወሰዱ ይገባል። ከተቻለ ከቅንጅታዊ አሠራርን ያልተከተሉ መሠረተ ልማቶች ዝርጋታ ሙሉ በሙሉ ማስቆም እና ቅንጅታዊ አሠራር ውስጥ እንዲገቡ ሊደረግ ይገባል። የመሠረተ ልማቱ ግንባታ ማስቆም ከጥቅሙ ጉዳቱ የሚያመዝን ከሆነና ግንባታው የግድ መካሄድ አለበት ተብሎ ከታመነበት ደግሞ ጥንቃቄ በተሞላበት አኳኋን መቀጠል አለበት።

በተለይም ለተለያዩ መሠረተ ልማቶች ዝርጋታ የሚቆፈረው መንገድ ለትራፊክ አደጋና ለሌች ችግሮች መንስኤ እንዳይሆን በአግባቡ መጠገን አለበት። ያፈረሰውን መሠረተ ልማት በአግባቡ የማይጠግን አካል በሕግ ተጠያቂ የሚደረግበት አሠራር ሊዘረጋ ይገባል ለሚፈጠሩ ችግሮች ካሳ የመክፈል ግዴታ ሊጣልበት ይገባል።

የመሠረተ ልማቶች ዝርጋታ በማስተር ፕላን ሊመራ ይገባል። የነባር ከተሞችን አሮጌ አካባቢዎችን መልሶ የማልማት ሥራ በሚሠራበት ወቅት ይህ ጉዳይ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። አጋጣሚውን በመጠቀም ከተሞቹ ሲመሠረቱ የተፈጠሩ ስህተቶችን በመጠኑም ቢሆን መቅረፍ ይቻላል። በነባር ከተሞች መሠረተ ልማቶች በማስተር ፕላን ብቻ መዘርጋት አዳጋች ሊሆን እንደሚችል ይታመናል።

አዲስ በሚለሙ ከተሞች መሠረተ ልማቶችን በማስተር ፕላን የመዘርጋት ጉዳይ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። አዳዲስ ከተሞች ከነባር ከተሞች ትምህርት በመቅሰም የነባሮችን ስህተት ላለመድገም መጠንቀቅ አለባቸው።

ለመሠረተ ልማት ሥራዎች ውጤታማነት የተቋማት ቅንጅታዊ አሠራርን ማጠናከር እንዲቻል ሀገራዊ የቅንጅት ማስተር ፕላን የማዘጋጀት ጉዳይ ለነገ የማይባል ነው። በዚህ ረገድ ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት በጋራ ሊረባረቡ ይገባል። መሠረተ ልማት የሚዘረጉ ተቋማት በጋራ እቅድ በማውጣት፣ ሥራቸውንም በጋራ የሚሠሩበት እንዲሁም አፈጻጸማቸውንም በጋራ የሚገመግሙበት አሠራር ሊዘረጋ ይገባል።

ያለስታንዳርድ የሚሠሩ ሥራዎች የሚፈለገውን ውጤት ለማስመዝገብ የማያስችሉ እንደመሆናቸው የሀገሪቱ የመሠረተ ልማት ዝርጋታ የቅንጅት ስታንዳርድ ከሌለ በአስቸኳይ ማዘጋጀት፤ ካለ ደግሞ ተግባር ላይ ማዋል እንደሚገባ አንስተዋል። በተጨማሪም የመሠረተ ልማት ፈጻሚ ተቋማት መረጃ ሀብት መሆኑን በመገንዘብ የተሟላና የተደራጀ መረጃዎችን መያዝ አለባቸው። የተሟላና የተደራጀ መረጃ ሲኖር የዝርጋታ ሥራው የተቀናጀ እንዲሆን ለማድረግ ከፍ ያለ እገዛ ይኖረዋል።

መረጃ በራሱ ችግሮችን ስለማይፈታ ተቋማት መረጃ ከመያዝ ባሻገር መረጃዎቻቸውን ማናበብ አለባቸው። አንዱ ጋር ያለውን መረጃ ሌላው ማወቅ አለበት ይህ ሲሆን በመረጃ ተመርኩዞ የሚወሰኑ ውሳኔዎች ችግሮችን ለመቅረፍ ያስችላሉ።

ግንዛቤ ማሳደግ ወሳኝ በመሆኑ፤ በክልሎች አካባቢ ስለመሠረተ ልማቶች ቅንጅት አስፈላጊነት የሚስተዋለው የአቅም ግንባታና የግንዛቤ እጥረት ለመቅረፍ በትኩረት ሊሠራ ይገባል።

ሁሉም አካላት የሚሠሩትን ሥራ በቅንጅት ለመሥራት ተገቢውን ትኩረት መስጠት አለባቸው። ችግሮች በሚፈጠሩበት ወቅት ደግሞ ጣት ከመቀሳሰር ይልቅ ችግሩን በጋራ ለመፍታት መረባረብ ያስፈልጋል።

የአንድ ሀገር እድገት ደረጃ ጠቋሚ ከሆኑት መካከል አንዱ መሠረተ ልማት መሆኑን ከግንዛቤ በማስገባት ለመሠረተ ልማት ዘርፍ እንቅፋት የሆነውን የቅንጅት እጦት ችግር በዘላቂነት ለመቅረፍ የችግሩን መንስኤ ለማወቅ ከሚደረጉ ጥናቶች ባሻገር የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር፣ የመንገዶች አስተዳደር፣ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት፣ የኢትዮ ቴሌኮም፣ የውሃና ፍሳሽ ተቋማት የሥራ ኃላፊዎች በቅርበት ሊሠሩ ይገባል። በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ መረጃ መለዋወጥ መቻልም ይኖርባቸዋል።

እያንዳንዱ መሠረተ ልማት ከመዘርጋቱ አስቀድሞ የሌሎች መሠረተ ልማቶች ዲዛይን መካተቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ለዚህም ተቋማት በየግላቸው መሠረተ ልማቶችን ከመዘርጋት ይልቅ ከሌሎች መሠረተ ልማቶች የሚዘረጉ ተቋማት ጋር አብሮ መሥራት ያስፈልጋል። ይህን በማድረግም የአገር ሀብት የሚፈስባቸውን የተለያዩ የመሠረተ ልማት ግንባታዎችን በጊዜ፣ በገንዘብና በሀብት መታደግ ይቻላል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የአውሮፓ ኅብረት በዓባይ ወንዝ ውሃ አጠቃቀም ላይ ያሳየው አቋም ኢ-ፍትሐዊና መቼም ቢሆን ተቀባይነት የሌለው ነው!

ሰኔ በገባ ቁጥር ሀገርን እንደ ሀገር የሚንጡ ችግሮች ማስተዋል ከጀመርን እነሆ በጥቂቱ አራት ዓመታት እያሳለፍን ነው። የለውጡ ኃይል ወደ ስልጣን መምጣቱን ተከትሎ የታላቁን የህዳሴ ግድብ ሥራ መፋጠንና የግድቡ የውሀ ሙሌት መጀመር ከችግሮች በስተጀርባ ያለ ዋነኛ ምክንያት እንደሆነም ብዙዎች ይስማማሉ ።

በርግጥ የዓባይ ወንዝ ውሀ ጉዳይ ለኢትዮጵያውያን ዘመን ያስቆጠረ የችግር ምንጭ ነው። ከወንዙ ውሀ ጋር በተያያዘ በስውርም ሆነ በግልጽ በብዙ ፈተናዎች ውስጥ አልፈናል።ፈተናዎቹን በጽናት ለመሻገርም ከፍ ያለ መስዋዕትነት ከፍለናል፤ ዛሬም ድረስ እየከፈልንም ነው።

የችግሩ ስፋትና ጥልቀት አሁን ላለንበት ድህነትና ኋላቀርነት ፤ ከዚያም አልፎ በየዘመኑ ለተፈጠሩ ማኅበራዊ ምስቅልቅሎች ምክንያት በመሆን ይገለጻል። በየዘመኑ ችግሮቻችን አሻግረን በተስፋ የምናያቸውን ነገሮች በእጃችን እንዳናስገባ አድርጎናል። ለተስፋ መቁረጥና ከዚህ ለሚመነጭ ማኅበራዊ ቁዘማም ዳርጎናል።

ዛሬ ግን ከነዚህ ችግሮቻችን ለዘለቄታው አሸንፎ በመውጣት የራሳችን ዕድል በራሳችን ለመወሰን እያደረግነው ያለው ጥረት ፣ ጥረቱ እያስገኘ ያለው ስኬት ተስፋ ሰጭ ቢሆንም ለብዙዎች ሕመም እየሆነም መጥቷል።

በተለይም የወንዙን ውሀ በተመለከተ በተሳሳተ ዕሳቤ የጠላትነት መንገድን መርጠው ለሚንቀሳቀሱ ሀገራት እና ቡድኖች ጉዳዩን አፍራሽ በሆነ መንገድ የሀገር ውስጥ ፖለቲካ ማስታመሚያ ከማድረግ አንስቶ ዓለም አቀፍ አጀንዳ ለማድረግ እየሠሩ ነው።

በአንድ በኩል በተለያዩ ጉዳዮች ያኮረፉ ቡድኖችን በማሰልጠን በማስታጠቅና የሎጂስቲክ አቅርቦት በመስጠት በባንዳነት መጠቀሚያ በማድረግ ፤ ሀገርን እስከ ማፍረስ የሚዘልቅ ሴራዎችን በመሸረብ ለሀገር ፈተና እየሆኑ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ ዓለም አቀፉን ኅብረተሰብ በተሳሳቱ መረጃዎች ከጎናቸው በማሰለፍ ያልተገባ ድምጻቸው አካል እያደረጉ ነው።

አንድ ሀገር የተፈጥሮ ሀብቷን አልምታ ለሕዝቦቿ የተሻሉ ዛሬዎችን የመፍጠር ተፈጥሯዊ መብት አላት ፤ይህ መብት በየትኛውም መንገድ ለድርድር የሚቀርብ አይደለም። እንደ ሀገርም የዚህች ሀገር የሕልውና መሠረት የሚዋቀረው ከዚህ ተፈጥሯዊ መብት ነው።በዚህ መብት ላይ መደራደር መፍረስን በሂደት የመምረጥና የመቀበል ያህል ነው።

ይህ ማለት ግን ኢትዮጵያ ለፍትሐዊ የሀብት አጠቃቀም ስፍራ የላትም ማለት አይደለም።በተለይም በድንበር ተሻጋሪ የውሀ ሀብት/ወንዞች ዙሪያ ኢትዮጵያ ያላት የማይናወጥ አቋም የጋራ ተጠቃሚነትን መሠረት ያደረገ ፤ከፍትሐዊ አስተሳሰብና ከዚህ የሚመነጭ ፍትሐዊ የውሀ ክፍፍልን መሠረት ያደረገ ነው።

ለዚህም ሲባል በድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ፍትሐዊ ተጠቃሚነት ዙሪያ ዓለም አቀፍ ሕጎችና ለሕጎቹ ተገዥ የሆኑ መርሆችን ተቀምጠዋል። የትኛውም ሀገር ፣ ቡድንና ተቋም ለነዚህ የፍትሐዊነት ሕጎች መገዛት ይኖርበታል፤ ለሕጎቹ ላለመገዛት ምንም ዓይነት ምክንያት ሊኖረው አይችልም።



ኢትዮጵያውያን እንደ ሕዝብ ከያዙት ከጎረቤት ሀገራት ጋር በሰላም አብሮ ከመኖር ባለፈ ፤ አብሮ የማደግ መርሕ አንፃር ፤ የዓባይን ውሀ ለዚሁ መርሕ ማስፈጸሚያ አንድ አቅም አድርገው ማየት ከጀመሩ ውለው አድረዋል ፤ይህንን በግልጽ በአደባባይ ለተፋሰሱ ሃገራትም ሆነ ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ አስታውቀዋል ።ከማስታወቅም ባለፈ በተጨባጭ የሚታዩ ተግባራትን ፈጽመዋል ፤እየፈጸሙም ነው።

በተለይም የታላቁ ህዳሴ ግድብ በተፋሰስ ሀገራት ላይ ስጋት የሚሆን ተጽዕኖ እንደማይኖረው የቴክኒክ ኮሚቴ እንዲዋቀር በማድረግ እውነታውን ለዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ ለማሳወቅ ረጅም ርቀት ተጉዘዋል።ባልተገባ ትርክት የተፈጠረ የጠላትነት መንፈስን ለማስወገድም የሕዝብ ለሕዝብ ግንንኙነቱን የሚያሻሽሉ ፣መተማመንን ሊፈጥሩ የሚችሉ ሥራዎችን ሠርተዋል።

ዓለም ስለ ፍትሐዊነት ከፍ ባለ ድምጽ በሚያዜምበት በዚህ ወቅት፤ ፍትሐዊነትን መሠረት ባደረገ መልኩ የተፈጥሮ ሀብታችንን ለመጠቀም እያደረግነው ያለው ጥረት ፤ከዛም በላይ በሕዝቦች መካከል ባልተገባ ትርክት የተፈጠሩ የጠላትነት ስሜቶችን ለማስወገድ ብዙ እርምጃ መጓዛችንም ከፍ ያለ ዓለም አቀፍ ዕውቅና እንዳስገኘልን ይታወቃል።

ይህ ሁሉ በሆነበት የግብጽ መንግሥት ለቅኝ ገዥዎች የቅኝ አገዛዝ አስተሳሰብ እና ጥቅም የተገዛውንና ኢትዮጵያ እንደ ሃገርና ባለመብት ያልተሳተፈችበትን ፤ ከተፋሰሱ ሀገራት ፈቃድና እውቅና ውጪ የሆነውን ግብጽና ሱዳንን ታሪካዊ የውሀ ባለድርሻ ያደረጋቸውን ኢ-ፍትሐዊ ስምምነት ላይ የሙጥኝ ብሏል፤ ከትብብርና አብሮ ከመልማት ውጪ ለኔ ብቻ በሚል መርሕ መንቀሳቀስን መርጧል ።በተለይ ደግሞ ሰኔ በገባ ማግስት ጉዳዩን የሀገር ውስጥ ሆነ ዓለም አቀፍ አጀንዳ ለማድረግ ሲጥርም ተደጋግሞ ይስተዋላል።

ይህ ከዓለም አቀፍ ሕግ ያፈነገጠ ፤ ፍጹም ከሆነ እራስ ወዳድነት የሚመነጨው የግብጽ ያልተገባ አቋም ለሀገር ውስጥ ፖለቲካ ትኩሳት ለማብረድ ከመጥቀም ካለፈ ኢትዮጵያውያን ፍትሐዊ በሆነ መንገድ የተፈጥሮ ሀብታቸውን በማልማት ነገዎቻቸውን ብሩህ ለማድረግ የጀመሩት የልማትና የብልጽግና መንገድ ሊያደናቅፍ አይችልም።

ይህ እውነታ ዓለም አቀፍ እውቅና እያገኘ በመጣበትና የፍትሐዊነት መሳያ እየሆነ ባለበት ወቅት ሰሞኑን የአውሮፓ ኅብረት በጉዳዩ ዙሪያ ያወጣው መግለጫ የኅብረቱ አባል ሀገራት ሕዝቦች ለፍትሐዊነት ያላቸውን የፀና እምነት የማያንጸባርቅና ፍጹም ኢ-ፍትሐዊ የሆነ ጣልቃ ገብነት ነው።

ቅኝ ግዛትና የቅኝ ግዛት አስተሳሰብ በአፍሪካውያን ላይ ጥሎት ያለፈውን ጠባሳ የሚያስታውስም ነው። ከሁሉም በላይ ደግሞ ኅብረቱ ለእኔ ብቻ የሚሉ የስስት አቀንቃኞች አካል በመሆን ጫና ለመፍጠር የመጣበት መንገድ ችግሩን ለመሸምገል ኃላፊነት ከተሰጠው አካል በፍጹም የማይጠበቅ ሲሆን ኢትዮጵያ መቼም ቢሆን ይህን ዓይነቱን ኢ-ፍትሐዊ አስተሳሰብና አቋም የማትቀበለው መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል!

ኢፕድ

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**
ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ነፃ ሃሳብ

**ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።**

# የትግራይ ሕዝብ አሸባሪውን ሕወሓት በቃ ለማለት የደረሰበት መከራ በቂና ከበቂ በላይ ነው!

**በእምነት**

በጣም ግርም ስላለኝ አንድ መረጃ ሳነብ ካየሁት ልነሳ ፤ አሸባሪው ሕወሓት ከዛሬ 40 ዓመት በፊት የትግራይን ሕዝብ ብሎም ኢትዮጵያን ነጻ አወጣለሁ፤ በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካ እንዲሁም በማኅበራዊ መስክ ታይቶ የማይታወቅ እመርታን አስመዘግባለሁ ብሎ ጫካ ሲገባ እነ ሳውዲ ነዳጃቸውን አላገኙም ነበር ፤ ይህ ማለት ደግሞ አሁን እኛ ያለንበትን አይነት ኑሮ ወይንም ደግሞ ከዚህም የባሰ ዝቅተኛ ኑሮ ውስጥ ነበሩ ማለት ነው።

ቻይናም የዛሬ ገናናነቷን ብሎም የዓለም ኢኮኖሚ ሞተር የሆነውን ብልጽግናዋን አልተቆናጠጠችም ነበር። ግን ሆዳቸውን ወይም ስልጣናቸውን ከዛች የሚያገኟትን ትርፍራፊ ብቻ እየለቀሙ ሀገራቸውን በመበዝበዝ ለመኖር ያልፈቀዱት የሳውዲም የቻይናም መንግሥታት ሕዝባቸውን ይዘው ወደፊት በመጓዛቸው ዛሬ ያሉበት ደረጃ ደርሰዋል። እኛስ?

እኛማ! አሸባሪው ሕወሓት ነጻ አወጣችኋለሁ ብሎ በጀመረው የ 17 ዓመት መራራ ጦርነት የሀገር ሃብት መተኪያ በሌለው ሁኔታ ከመውደሙም በላይ ሀገርን በጠንካራ መሠረት ላይ ሊገነቡ የሚችሉ ውድ የአገር ወጣቶች ሕይወት በከንቱ ተቀጥፏል። ከዛም በኋላ በነበረው የአገዛዝ ዘመን ሀገርን ከማሳደግ ይልቅ የስልጣን ሽሚያ ፣ ኋላም በስልጣን መባለግና ሙስናን በማስፋፋት አገር እንኳን እንደነ ሳውዲና ቻይና ቀርቶ በነበረችበት ሁኔታ እንኳን እንዳትቀጥል በሚያደርግ መልኩ እንድትንኮታኮት ሆናለች።

ወጣቶች በሀገራቸው ተስፋ ከመቁረጣቸው የተነሳ ሀገራቸው ላይ ለመኖር፣ ለመሥራት፣ ለመለወጥ ከማሰብ ይልቅ የባዕዳን ደጅ ናፋቂና ተሰዳጅ ሆነው እንዲቀሩ በዚህም የኢትዮጵያ ስም ደሃ ተሰዳጅ እንዲሆን አድርጓል። እንደ ሕዝብ በቡድኑ የስልጣን ዘመንም የከፈልነው ዋጋ ዘርዝሮ ለመጨረስ የሚመች አይደለም ።

የቡድኑ ግፍና መከራ የታከታቸው የሕዝብ ልጆች ባደረጉት መራራ ትግል ከስልጣን ቢወገድም ፤ በሕዝብ ትግል የመጣውን ለውጥ በመቀልበስ ከተቻለው ተመልሶ ወደ ስልጣን ለመምጣት ካልተቻለው ሀገርን ለማተራመስ ያልፈነቀለው ድንጋይ የለም ። የትግራይን ሕዝብ እንደ ማስያዣ በማድረግ በመላው ሀገሪቱ ችግር መፍጠርን እንደ ትልቅ ሥራ ይዞ መቆየቱ የሁላችንም የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። ዛሩም ከዚህ የተለየ ነገር የለም ።

ከፍጥረቱ ጀምሮ በተጠናወተው ጀብደኝነት ፤ሀገርና መንግሥትን ወደ ጦርነት ገፋፍቶ አስገብቶት እነሆ ሀገርን ችግር ውስጥ ከከተተ ወራት አልፈው ዓመታት አንድ ሁለት ማለት ይዘዋል ። በዚህም የትግራይን ሕዝብ ጨምሮ መላው ሕዝባችን አላስፈላጊ ዋጋ እየከፈለ ነው ።

በኋላ ከስልጣን ዘመኑ ጀምሮ በራሱ አምሳያ ቀርጾ የሠራቸው የሱ ተላላኪ ቡድኖች በሚፈጥሩት ሁከትና ግርግር ሕዝብ የሰላም አየር እንዳይተነፍስ ሆኗል።ግድያና መፈናቀል በሀገር አቀፍ ደረጃ ተስፋፍቷል ።

የትግራይን ሕዝብ መያዣ አድርጎ እየሄደበት ባለው የፖለቲካ ቁማር የትግራይ ሕዝብ ከፍ ላለ ችግር ተዳርጓል ። ልጆቹን ከንቱ ለሆነ ጦርነት ከመገበር አንስቶ፣ የሚበላውና የሚጠጣው እስኪያጣ ድረስ በስቃይ ውስጥ ለመኖር ተገድዷል ።

ብዙ መስዋዕትነት የከፈለለት ትግል የሚመኘውን እኩልነት፣ ሰላም፣ ፍትህና ዲሞክራሲ ከማምጣት ይልቅ ፤የከፋ መከራና ስቃይ ካመጣለት ውሎ አድሯል። መስዋዕትነቱ ለብድኑ ጥቂት አመራርና ቤተሰቦች የቅንጦት ሕይወት ከመፍጠር ባለፈ የፈየደው አንዳች ነገር የለም።

የትግራይ ሕዝብ የቀደመ የትግል መስዋዕትነቱ ተስፋ ያደረገውን እውነት ከማስጨበጥ ይልቅ ፤ ላልጠበቀውና ላልገመተው ችግርና መከራ አሳልፎ ሰጥቶታል ፤ ይህ ደግሞ ለሕዝቡ ተጨባጭ አስተምሮ ሊሆን እንደሚችል ይታመናል ።

ይህ ሕዝብ ከትናንት ተሞክሮው በመነሳት በቀደመው መስዋዕትነቱ የባርነት አገዛዝ ቀንበር የጫኑበትን የአሸባሪው ሕወሓት አመራሮች በቃችሁ ሊላቸው ይገባል ። ተስፋው ተነጥቆ ፤ ፍትሕ ተነፍጎ ብሎም በማያባራ የጦርነት እሳት ሊለበለብ ፣ ልጆቹንም ሊገብር አይገባም። ግድም የለበትም።

የትግራይ ሕዝብ የወያኔ አምባገነን አገዛዝ በፈጠረው እኩልነት የጎደለው የፖለቲካ ሥርዓት ሰለባ ከመሆኑ አንጻር ፤ አገዛዙ ያበቃ ዘንድ ፤ ከሌሎች ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ጋር በመሆን ሊንቀሳቀስ ይገባል። በፍትሕ የመዳኘት ፣ሠርቶ የመብላት ፣ራሱንና ሀገሩን የመለወጥ መብቱን ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅበታል ።

ይህንን መብቱን ከማንም ሊያገኘው እንደማይችል ተገንዝቦ የችግሩ ዋነኛ ባለቤት የሆነውን አሸባሪውን ሕወሓት በማስወገዱ ከፊት ሊሰለፍ ይገባል። ሞት፣ መፈናቀል፣ ረሃብ እና ስቃይ እንዲያበቃ ፤ ትናንቶቹ በተስፋ የተሞሉ እንዲሆኑ ሌላ አማራጭ የለውም ።

እስካሁን ባለው ታሪኩ የስልጣን ጥማቱን ለማርካት ሕዝብን ከሕዝብ ፤ ሃይማኖትን ከሃይማኖት ከማጋጨት፤ በዚህም ሀገርን ከማተራመስ ያለፈ አጀንዳ ኖሮት አያውቅም። ይህ እኩይ ተግባሩ ደግሞ የትናንት ብቻ ሳይሆን የዛሬም መገለጫው ነው ።ከዚህ ቡድን ጋር ሕብረት መፍጠር የትግራይን ሕዝብ አይመጥነውም ።

ቡድኑ በስልጣን በቆየባቸው ዓመታት እንደ መንግሥት ከሀገርና ከሕዝብ ጥቅም ይልቅ ለራሱ ህልውና ሲሠራ የቆየ ፤ለምንም አይነት አማራጭ አስተሳሰብ ሆነ ሰጥቶ የመቀበል ባህሪ እራሱን ያላስገዛ ነው ። ይህ ባህሪው ደግሞ ከሁሉም በላይ የትግራይን ሕዝብ ዋጋ አስከፍሏል ፤እያስከፈለም ነው ።

አሸባሪውን ሕውሓት በሀገር ሆነ በሱ ላይ ለፈጸማቸው መጠነ ሰፊ ጥፋቶች ለፍርድ ለማቅረብ በሚደረገው የሕግ ማስከበር ሂደት ውስጥ የትግራይ ሕዝብ የቡድኑን እኩይ ተግባርና ተግባሩ ያደረሰበትን ስቃይና መከራ ተገንዝቦ በቃህ የሚልበት ጊዜ አሁን ነው ።

የትግራይ ሕዝብ በቡድኑ ራስ ወዳድነትና ጀብደኝነት ምክንያት ከዚህ በላይ ዋጋ መክፈል የሚያስችል አቅም አይኖረውም ፤ላለፉት 50 ዓመታት ገደማ የከፈለው ዋጋ ያስገኘለት ጥቅም አለመኖሩ ፤ቡድኑን በቃ ለማለት በቂና ከበቂ በላይ ነው ።

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፣ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ስመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤^አስተውሳችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

## እንደወርቅ በእሳት...

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

### ትናንትና...

ዝነኛ ነበረች። ድንቅ ውበት፣ ማራኪ አለባበስ መለያዋ የሆነ ። ስለእሷ የሚያደንቁ፣ ስለማንነቷ የሚያወጉ በርካቶች ስሟን አንስተው አይጠግቡም። በየጊዜው እየቀያየረች የምትይዛቸው መኪኖች ዘመናዊነቷን ሲመሰክሩ ቆይተዋል። ቀበጥ ነች። መዝናናት፣ መጫወት ያስደስታታል።

በከተማው በተሰማራችባቸው ሥራዎች የሚለይዋት ሁሉ ሲያደንቋት፣ ኖረዋል። የትናንት አስተዳደጓን የሚያውቁ ብርታት ጥንካሬዋን እያወጉ በምሳሌ ያነሷታል። ቁንጅናዋ ውሎ አድሮ ባመጣላት ሲሳይ ከራሷ አልፋ አካባቢዋን አስጠርታለች። ይህ የትናንትናው ውብ ታሪኳ ነው።

ወደኋላ ያለፉ ጣፋጭና መራራ ዓመታትን ዛሬ ላይ ቆማ በትዝታ ታስባቸዋለች። በእነዚህ ጊዜያት በሻካራና ምቹ መንገዶች ተራምዳለች። በሳቅና ፈገግታ፣ በለቅሶና ችግር አልፋለች። በእሷ ሕይወት ጨለማና ብርሀን፣ ኀዘንና ደስታ ብርቅ ሆነው አያውቁም። በሌላው ትናንቷ በደመቁ ፈገግታዎችና በማያባሩ ለቅሶዎች መሀል ተመላልሳለች። አብነት ሀይሉ።

### ዓመታትን ወደኋላ...

የልጅነት ሕይወቷን ስታነሳ ያሳለፈችው ፈተና ትውስ ይላታል። እሷ ችግር ይሉት ጉዳይ በሁሉም ዘንድ መኖሩን ታምናለች። ወደራሷ ስትመለስ ግን የእሷ ከሌሎች ሁሉ እንደሚለይ ይሰማታል። ገና በጠዋቱ አባቷ በሞት ሲለዩ እሷና ሁለት ወንድሞቿ ለምግብ ብቻ የደረሱ ሕፃናት ነበሩ። እንዲህ መሆኑ ፈተና የሆነው ለቤት እመቤቲቱ እናት ብቻ አልሆነም። ለቤቱ የመጀመሪያ ልጅ ለሆነችው ለዛኔዋ እምቦቃቅላ ለአብነት ጭምር እንጂ።

አብነት ሃዋሳ ወልዳ ያሳደገቻት የደቡብ ፍሬ ነች። የአባቷን መሞት ተከትሎ የኑሮ ጫናን የተሸከመችው ገና በልጅነት ዕድሜዋ ነበር። እኩዮቿ ደብተር ይዘው ትምህርት ቤት ሲሄዱ ዕጣ ፈንታዋ የቤተሰቡን ኑሮን ለማቅናት ሸክሙን መቀበል ሆነ። ለቤቱ የመጀመሪያ ልጅ መሆኗ ኃላፊነትን ለመቀበል ከፊት አስቀደማት። የልጅነት ጫንቃዋ ሁሉን ሊሸከም ‹‹በቃኝ›› አላለም። በሰባት ዓመት ዕድሜዋ ለሥራ ከመንገድ ወጣች። ሸንኮራ እየሸጠች፣ እየተላከች፡ ሳንቲም ማግኘት ጀመረች። የምታገኘው ጥቂት ገቢ ለእናቷና ለወንድሞቿ በቂ አልነበረም። ይህኔ ትንሽዬዋ አብነት ከሀዋሳ ትልቁ ገበያ እየዞረች ለገበያተኞች ዕቃ መሸከም፣ ያዘች።

ዛሬ ስታስበው በዓይኖቿ ውሀ እስኪሞላ የምትቸገርባቸው ክፉ ትውስታዎች የዚያን ዘመን ጥቁር አሻራዎች ሆነው አልፈዋል። ትንሽዋ አብነት እንደአባት የምታየው፣ እንደታላቅ የምታማክረው የልብ ሰው ከጎኗ አልነበረም። በብቸኝነት እየተብሰለሰለች የቤተሰቦቿን ብርሀን ልታደምቅ ዕድሜ ጉልበቷን ገበረች።

የዛኔ ልጅነቷ ከሴትነቷ ተዳምሮ ብዙ ፈትኗታል። ከማንም በላይ ክብር የምትሰጠው የእንጀራ አባቷ ግን ለእሷ ክፉ አልነበረም። መልካም መንገዶችን እያመላከተ እንዳትውድቅ ደግፏታል። ዛሬን ቆማ እንድትራመድ ከጎኗ ሆኖ « አይዞሽ» ብሏታል ። ስለሱ ያላት ምስጋና ዛሬም ድረስ ሙሉ ነው።

ጠዋት ማታ በሥራ የምትባትለው ሕፃን በዕድሜዋ ስለሚገባት የመማር ዕድል አስባ አታውቅም። በሊጋነት ዕድሜዋ ቤተሰቦቿን ለማኖር በድካም ባዘነች። አጋጣሚ ሆነና ከሰባት ዓመቷ በኋላ እንደእኩዮቿ «ሀሁ... » ልትል ፣ ቀለም ልትቆጥር መንገዱን አገኘች። ይህ ዕድል ግን በቀላሉ የተገኘ አልነበረም።

አብነት በአካባቢው ከሚገኝ የካቶሊኮች ትምህርትቤት የገባችው ጉልበቷን ጭምር በመገበር ነበር። ውሎዋን የትምህርት ቤቱን ክፍሎች እያጸዳች የማታ ለመማር ከአንደኛ ክፍል ጀመረች። የዛኔ እንደእኩዮቿ የሆነች ቢመስላት ልቧ በደስታ ዘለለ። ሁኔታው ግን እንዳሰበችው ቀላል አልሆነም። የቀን ድካሟ በዕንቅልፍ እየረታት ተቸገረች። አብነት ከምትማረው የምታንቀላፋበት ጊዜ እየበዛ ተቸገረች።

ቀን በጽዳትና በመላላክ የምትውለው ታዳጊ ምሽቱን ከነድካሟ ደብተር ይዛ ፊደል ቆጠረች። እስከ አምስተኛ ክፍል በጥንካሬ ተጉዛም ቀለም ለየች፣ ዕውቀት ጨበጠች። እነዚህ ጊዜያት ለብርቱዋ ታዳጊ ምቹ አልነበሩም። እርምጃዎቿ ሁሉ የችግር መሰላሎች ሆነው በእጅጉ ፈተኗት። ስድስተኛን ተሻግራ እስከ ስምንተኛ ተማረች። በኋላም እስከ ሁለተኛ ደረጃ በታቦር ትምህርት ቤት ዘለቀች።

በኮምቦኒ ትምህርትቤት ያሉ ተማሪዎች የኑሮ ደረጃ አንድ አልነበረም። የድህና የሀብታም ቤተሰብ ልጆች በአንድ ይውላሉ። ያለክፍያ ከሚማሩት ተማሪዎች አንዷ የሆነችው አብነት ከማታ ትምህርት ወደቀን ተመልሳ ባልንጀሮቿን መሰለች። ይህኔ ረጅሟና ቀጫጫዋ ተማሪ ከሌሎች ተለይታ ከዓይን ገባች። ቁመቷን ያዩ፣ አረማመዷን የገመገሙ ብዙዎች አሻግረው በጎ ተመኙላት።

በተለይ የትምህርት ቤቱ ፈረንጆች በመለሎዋ አብነት ጀርባ መልካም ነገር አሰቡ። ሞዴል እንድትሆን፣ የፋሽን ኢንዱስትሪውን እንድትቀላቀል መካከሯት። አብነት በየቀኑ በምትሰማው በጎ ሀሳብ ልቧ ተነሳሳ፣ ብዙዎች እሷን እያሰቡ የሚነግሯት የሞዴልነት ዓለም ውስጧን ገዛው። ደግማ ደጋግማ አሰበችበት። ፍላጎቷ ከሌሎች ተዳምሮ አዲስ አበባ አደረሳት።

### አብነት በሸገር ...

ለአገሩ ባዳ፣ ለከተማው እንግዳ ለሆነችው ወጣት የአዲስ አበባ ሕይወት ቀላል አልነበረም። በውስጧ ጽኑ ፍላጎት ብቻ ለሰነቀችው የፋሽን አፍቃሪ በዋዛ ኢንዱስትሪውን መቀላቀል አልጋ በአልጋ አልሆነም። ለትራንስፖርት ተቸገረች፣ በአልባሳትና በጫማዎች እጥረት ተፈተነች። ከሌሎች እኩል ለመወዳደር ብትቸገርም እጅ አልሰጠችም። ጎዶሎውን በዘዴ እየሞላች ከሞዴሎች ተርታ ተሰለፈች።

የአብነት መንገድ ከባድና ትግል የበዛበት ነበር። ያም ሆኖ ሙከራዋ በጥረት ተሳካ። በቆይታዋ የሚያስፈልገውን ሙያ ዘግና ወደ ሀዋሳ ተመለሰች። እጇን ዘርግታ በተቀበለቻት የትውልድ አገሯ የያዘችውን ዕውቀት በወጉ ልትመነዝር ዕድል ተቸራት ።

በከተማዋ በተካሄደው የቁንጅና ውድድር መድረኩን ናኘችበት። በርካቶች በተወዳደሩበት የሚስ ሀዋሳ ቁንጅና ውድድር ዓይን አዋጅ የሆነባቸው ተመልካቾች አንዷን ቆንጆ ከሌላዋ ሊለዩ ተቸገሩ። የተወዳዳሪዎቹን ውበትና የአንደበታቸውን ቃላትም ሊያመዛዝኑት ጨነቃቸው። ከሁሉም ግን ቁመተ ሎጋዋ፣ መልከ ቀናዋ አብነት የበርካቶችን ቀልብ ገዛች። ዓይኖች ሁሉ በእሷ ላይ አተኮሩ፣ እርምጃዋና፣ ንግግሯ ከሌሎች ተለይቶ ጎላ።

ጥቂት ቆይቶ ዳኞች የተወዳዳሪዎቹን ውጤት አሳወቁ። ወጣቷ ሞዴል አብነት ሀይሉ የውድድሩን የአሸናፊነት አክሊል ከራሷ ላይ ደፋች። ዕልፎች በ‹‹ይገባታል›› አድምቀው አጨበጨቡ። በርካቶች በአድናቆት እጃቸውን ከአፋቸው ጫኑ።

የዘመኑ ‹‹ሚስ ሀዋሳ›› ከውበቷ ጀርባ ማንነቷ አነጋገረ። ምስኪን ድሀ፣ ለእግሯ ጫማ ያልነበራት፣ በሳር ፍራሽ የተኛች፣ በበርካታ ችግሮች የተመላለሰች መሆኗ አስደነቀ። ታሪኳን የሰሙ ሁሉ በከፍታ አከበሯት፣ ቆመው በድምቀት አጨበጨቡላት። እንዲህ በሆነ ማግስት የቆንጆዋ ስምና ዝና ናኘ። ይህን ተከትሎ አድናቂዎቿ ለውጧን ተመኙ። ዳግም በዓለም አቀፍ መድረኮች ሊመለከቷት ናፈቁ። አብነት አስተያየቶችን ሰማች፣ አድናቆቶችን ተቀበለች። ፈላጊዎቿ በረከቱ፣ ውሎና ሥራዋ ከታዋቂ አርቲስቶች ሆነ።

### አዲስ ሕይወት...

የቁንጅና ውድድር አሸናፊዋ አብነት ሕይወቷ ሊቀየር ፣ ታሪኳ ሊለወጥ ጊዜው ደረሰ። ዝነኝነቷን ተከትሎ የመጣው አዲስ የሕይወት መንገድ ኑሮዋን በእጅጉ ቀየረው። ከመኪና መኪና ለዋወጠች፣ በበርካታ ሥራዎች ታወቀች። በቂ ገንዘብና ጥሩ የሚባል ሀብት ከእጇ ደረሰ።

የትናንት ማንነቷን የሚያውቁ በጎዎች ከልብ ተደሰቱ። አብነት ድህነትን ለማምለጥ በበረከቱ አማራጮች ስትሻገር ቆይታለች። ራሷን አሸንፋ ቤተሰቦቿን ለማገዝ ያላለፈችበት መንገድ የለም። በሻካራማው ጉዞ ተራምዳ ኑሮን ድል መንሳቷ ብዙ አስተምሯታል።

ከቀናት በአንዱቀን አብነት ከአንድ ነጭ ጓደኛዋ



ጋር ስትዝናና ከሌላ ጉብል ዓይን ወደቀች። እሷም ብትሆን ያየትን ሰው ቀድማ አይታው ኖሯል። የዚያች ቀን መተያየት ሰበብ ሆኖ ከትዳር አጋሯ ተጣመረች። አምስት ልጆችንም ወለደች። የውበት ሳሎን፣ የመኪና ማከራያና የባህል ምሽት ቤትን ከፈተች። ከታወቁ ሰዎች እየተጣመረች ታላላቅ የሙዚቃ ኮንሰርቶች ማዘጋጀት ልምዷ ሆነ። የሀብት መምጣትን ተከትሎ ዝነኝነቷ ጨመረ። ሥራዋን የሚያደንቁ፣ ቤቷን የሚያዘወትሩ ደንበኞች በየዕለቱ ከበሯ ተመላለሱ።

አብነት ብዙዎች እሷ ባለፈችበት አስቸጋሪ የሕይወት መንገድ እንዳያልፉ እገዛዋ የበዛ ሆነ። ‹‹መልካሙ ሳምራዊ›› የሚል አገር በቀል ድርጅት አቋቁማ ወጣቶች በራሳቸው ገቢ እንዲተዳደሩ ዕድሉን ከፈተች። የእናቶችን ችግር ለመፍታትም ከጎናቸው ቆመች። ብርታቷ ብዙዎች ያልሞከሩትን የሕፃናት ተጨማሪ ምግብ ማምረቻን እስከመክፈት አደረሳት።

በመሬት ሽያጭና መሰል ሥራዎች ውጤታማ መሆን ቻለች። ከአገር ውጭ ተመላልሳ የጎደሉትን እየደፈነች ፣ የብዙዎችን ፍላጎት አሟላች። ጥረቷን ተከትሎ የመጣው ስኬት ከዝነኝነት ተዳምሮ የአብነትን ስም ከማማው ሰቀለው። በሀዋሳ ምድር ማንነቷ በበጎ ተወሳ። ቆንጆዋና ሞዴሏ ወጣት በሥራዎቿ ታወቀች፣ ደመቀች።

### ከዓመታት በኋላ ...

ዛሬ በአብነት ሕይወት የትናንቱ ታሪክ የለም። የጀመረችው የስኬት መንገድ ከዳር ባያደርሳት በ ‹‹ነበር›› የምታነሳቸው ድንቅ ታሪኮች ብቻ ከእሷ ቀርተዋል። አሁን የቀድሞው መልካም ዝና፣ አብሯት የኖረው ሀብት ንብረት ከጎኗ የለም። ይህ ብቻ አይደለም። ትናንት በአድናቆት የሚያወሷት ብዙዎች ዛሬ ስሟን ደግመው አይጠሩትም። ስኬቷን ተከትሎ የደረሰባት ድንገቴ ኪሳራ ከብዙ እውነታዎች ነጥሏታል።

አብነት የትናንትናዎቹ የቅርብ ባልንጀሮቿ፣ የደመቀው ኑሮና ትዳሯ ከተለዩዋት ጊዜያት ተቆጥረዋል። ገንዘብ በነበራት ጊዜ ለበርካቶች ደርሳለች፣ ጠቅማለች። በአንጻሩም ብኩን መሆኗ ብዙ አስከፍሏታል። በእጇ ያለውን ገንዘብና ጥሪት በወጉ አለመያዟ ለዛሬው ችግሯ ምክንያት መሆኑን ታውቃለች። እሷ መጠን ባለፈ ኑሮ ማለፏ የእጇን በረከት እንደበተነው ይገባታል። የዛኔ ለሌሎች የምታደርገው መጠን የለሽ ውለታ ለዛሬው ማንነቷ ጥቁር አሻራ ትቷል። አብነት ትናንት የደፋችው ምግብ እስኪናፍቃት በማይታመኑ ችግሮች ታፍናለች፣ አጥታ ያገኘች ቢሆንም አግኝታ ድንገት ማጣቷ ይበልጥ ያስከፋታል።

### አብነት ዛሬ...

የትናንቷ ውብ ቆንጆ ዛሬም የመኖር ትግሏ ቀጥሏል። ሕይወቷን በብርታት መርታ ፣ ልጆቿን በወጉ ለማኖር ግን እንደቀድሞው አልሆነችም። እንደትናንቱ በድምቀት አልታየችም። ዛሬ ያቿን ጠንካራ ሴት የሚያውቁ ሁሉ ከቁንጅናው መድረክ፣ ከኢንቨስትመንቱ ጎራ አይፈልጓትም። አሁን የእሷን በረከት ሲሹ የኖሩ እጆች እንደቀድሞው አይመኩባትም። አብነት እንኳን ለእነሱ ለራሷም መሆን ተስኗታል።

ለእሷ ችግርና ፈተና፣ መከራና ትግል ብርቋ አይደሉም። አሁን ያለችበት አጋጣሚ ግን ሆድ አስብሶ ከዕንባ ያተናንቃታል። በትካዜ አንገት አሰደፍቶ በሀሳብ ያናውዛታል። ‹‹አሸነፍኩት›› ያለችው ፈተና ዳግም ሊገጥማት ቢገዳደራት፣ እጅ መስጠት ሞቷ ሆኖ ትታገለው፣ ትተናነቀው ይዛለች።

### ስመኖር...

አብነት ዛሬ ቤት ንብረት ይሉትን አጥታለች። ውሎ አዳሯ ከከሰል፣ ጋር ሆኗል። ከሰል ለአብነት ትርጉሙ ይለያል። እንደሌሎች ጥቁር ብቻ አይደለም። ሕይወቷን ለመምራት፣ ልጆቿን ለማሳደግ የእንጀራዋ ብርሃን ነው። ዛሬ እነዛ ለስላሳ እጆች ከከሰሉ ሲታገሉ ይውላሉ። ትናንት ባማሩ ጌጦች የተዋቡት ጣቶች አሁን መገኛቸው ከአመድ ብናኝ ሆኗል።

አንዳንዴ አብነት እህል ባላየ አንጀቷ ማዳበሪያ በትከሻዋ አዝላ በየመንደሩ ትዞራለች። ዓይኖቿ ውዳቂ ቁሶችን አያልፉም። ይበጃሉ የምትላቸውን ሁሉ ትለቅማለች። እጆቿ ያገኙትን ለማንሳት አይጠየፉም። እርግጥ ነው፤ ትናንት የሚያውቋት ሲያተኩሩባት ትሳቀቃለች። ለመኖር፣ ልጆቿን ለማሳደግ ግን እንዲህ ሊሆን ግድ ብሏል።

እሷ የሚቀመሰውን፣ የሚጎረሰውን ይዛ፣ የምታበስልበት እንጨት ያጣችባቸው ጊዜያት አሉ። እንዲህ በሆነ ጊዜ ከሱቅ ዱቤ እስከመከልከል ደርሳለች። ይህ ዓይነቱ እውነታ ብዙ ታደርግ ለነበረው አብነት የኀዘን፣ የአንገት መድፋት ዘመን ነበር። ግን ደግሞ በርሀብ መሞት የለባትም። የትናንት የስኬት መንገዷ ታሪክ ከሆነ በኋላ ብዙ አስባለች። ሕይወቷን ለመቀጠል፣ ልጆቿን ለማሳደግ ቢያንስ ቀምሶ ማደር አለባት። እንደቀድሞው መልካም ነገሮች ከእሷ ቢርቁም ዝምታ ምርጫዋ አልሆነም።

ሰዎች ስለከሰል ሽያጭ መንገዱን በጠቆሟት ጊዜ ዓይኗን አላሸችም። ከጭስ፣ገብታ፣ ከአመድ ተለውሳ፣ በእሳት ተለብልባ እንደ ከሰል ጠቁራ ለመኖር አማራጭ ወሰደች። እናም ከሰሉን እያመረተች መሸጥ እንጀራዋ፣ ሕይወቷ ሆነ። ዛሬ አብነት የጥንካሬዋ መሠረት ፈጣሪዋ መሆኑን ታምናለች። ቢከፋት፣ ብታዝንም ተስፋ አልቆረጠችም። ነገ ሌላ ተስፋዋ ነው። በሀብት አትመካም፣ ዳግም የወደፊቱን በጎነት አጥብቃ ታስባለች።

አብነት ትናንት ስለሆኑባት መጥፎ አጋጣሚዎች በሌሎች ላይ እጅ አትጠቁምም። አዎ! የከንዷ በረከት ተበትኗል። የቅርብ ባልንጀሮቿ እንዳለየ አልፈዋታል። ቤት ትዳሯ ፈርሷል። እሷ ግን ካለፈው ሕይወቷ ለመማር ከራሷ በላይ አጋዥና ብርቱ እንደሌለ ታውቃለች። ከትንሽ እንደተነሳች ሁሉ ወድቃ እንደማትቀር ዕምነቷ ነው። ከውድቀቷ ብዙዎች መማራቸው ደግሞ ከልብ ያስደስታታል።

አብነት ስለፈረሰው ትዳሯ ብዙ ማውራት አትሻም። ልጆቿ ግን ዛሬ ቀና ብላ ለመሄዷ ምክንያት ናቸውና ከአፏ አትነጥላቸውም። ሁሌም በእነሱ ውስጥ ጥንካሬና ብርታትን ታያለች። የታሪኳ አብይ ክፍል በመሆናቸው ለእነሱ ያላት ፍቅርና አክብሮት ለየት ይላል።

የትናንቷ ባለዝና ፣ የቀድሞዋ ቆንጆ ባለሀብት፣ ዛሬን በነበረችበት ቦታ አልቆመችም። አሁን የኖረችበትን ታሪክ ፣ያሳለፈችውን ድንቅ ሕይወት በነበር ታወሳዋለች። ለእሷ በሻካራማ መንገዶች አልፎ ከምቾት ዓለም መድረስ ብርቅ አይደለም። በደልዳላው ሜዳ ተራምዳ ከአስቸጋሪው ገደል መግባትን አልፋበታለች።

እርግጥ ነው። ትናንት እንዳለፈ ሁሉ ዛሬም እንዲያልፍ ታውቃለች። የእሷ ዓለም ግን አሁን ነው። ዛሬን የምትኖረው ፈታኝ ሕይወት። አብነት ሀይሉ ኑሮን ታግላ ሕይወትን ለማሸነፍ እንዲህ መኖር ይዛለች። በተስፋ፣ በጥንካሬ፣ በአይበገሬ ጽናት።

# ስፖርት



# ዋልያዎቹ በፊፋ ያላቸውን ወርሐዊ ደረጃ አሻሻሉ

ቦጋለ አበበ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን(ዋልያዎቹ) የዓለምን እግር ኳስ በበላይነት የሚመራው ፊፋ በየወሩ በሚያወጣው የሀገራት የእግር ኳስ ደረጃ መሻሻል አሳይተዋል። ዋልያዎቹ ካለፈው ወር የፊፋ የሀገራት የእግር ኳስ ደረጃ ሰንጠረዥ በሁለት እርከን መሻሻል አሳይተው ከነበራቸው 140ኛ ደረጃ ወደ 138ኛ ደረጃ ከፍ ብለዋል። በአፍሪካ የነበራቸው ደረጃም ወደ አርባ አንደኛ ከፍ ሊል ችሏል።

ዋልያዎቹ ከሶስት ሳምንት በፊት በ2023 የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ከመጀመሪያዎቹ ሁለት ጨዋታዎች አንዱን ማሸነፋቸው ይታወሳል። ዋልያዎቹ የመጀመሪያውን የማጣሪያ ጨዋታ ከሜዳቸው ውጪ ከማላዊ አቻቸው ጋር አድርገው ሁለት ለአንድ መሸነፋቸው የሚታወስ ሲሆን ሁለተኛውን ጨዋታ እዚያው ማላዊ ላይ በማድረግ የግብጽ አቻቸውን ሁለት ለ ዜሮ ማሸነፋቸው አይዘነጋም። የነዚህ ሁለት ጨዋታዎች ውጤት ለዋልያዎቹ የደረጃ መሻሻል ትልቅ ድርሻ አላቸው። ፊፋ ለየሀገራቱ የሚሰጠው ወርሐዊ የእግር ኳስ ደረጃ ሀገራቱ በወር ውስጥ በሚያደርጉት ጨዋታ እንዲሁም በተጋጣሚያቸው ጥንካሬ ላይ የተመረኮዘ መሆኑ ይታወቃል። በዚህም መሠረት ዋልያዎቹ በአፍሪካ ጠንካራና የተሻለ ደረጃ ያላት ግብጽን ማሸነፋቸው አሁን ከተሰጣቸው ደረጃ የተሻለ የሚያስቀምጣቸው ቢሆንም በአንጻራዊነት ደካማ በሆነችው ማላዊ መሸነፋቸው በወርሐዊ ደረጃቸው ላይ ከዚህ የተሻለ ቦታ እንዳይቀመጡ አድርጓቸዋል።

በተያያዘ በሴቶች ወርሐዊ የፊፋ የደረጃ ሰንጠረዥ የኢትዮጵያ የሴቶች ብሔራዊ ቡድን(ሉሲዎቹ) ከባለፈው ወር ከነበራቸው ደረጃ ቀንሰው ከዓለም 126ኛ ደረጃ ላይ ሲቀመጡ በአፍሪካ አስራ ስምንተኛ ሆነዋል። ሉሲዎቹ ከሶስት ሳምንት በፊት በመካከለኛና ምስራቅ አፍሪካ ዋንጫ(ሴካፋ) ወደ ዩጋንዳ ተጉዘው በሶስተኛነት ማጠናቀቃቸው ይታወሳል።



**የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን(ዋልያዎቹ) በፊፋ ወርሐዊ የደረጃ ሰንጠረዥ ከዓለም 138ኛ ሆነዋል፣**

ያለፉት ሁለት የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ጨዋታዎች በአህጉሪቱ የእግር ኳስ ደረጃ ላይ የተለያዩ ለውጦችን ፈጥረዋል። ጊኒን በሜዳዋ አንድ ለዜሮ የረታችው የሰባት ጊዜ የአፍሪካ ዋንጫ አሸናፊዋ ግብጽ በዋልያዎቹ መሸነፏ በአፍሪካ የነበራትን ደረጃ ከቀዳሚዎቹ እንዲንሸራተት አድርጓል። በዚህም ከአፍሪካ ወደ ስድስተኛ ደረጃ ስትወርድ በዓለም አርባኛ ደረጃ ላይ አስቀምጧታል።

የአፍሪካ ዋንጫ ሻምፒዮኗ ሴኔጋል በበኩሏ የአህጉሪቱን የእግር ኳስ ደረጃ በመሪነት ልትቆናጠጥ ችላለች። በዓለም ያላት ደረጃም ወደ አስራ ስምንተኛ ከፍ ብሏል። ሴኔጋልን ጨምሮ በኳታሩ የዓለም ዋንጫ አፍሪካን ከሚወክሉ አምስት ሀገራት አንዷ መሆኗን ያረጋገጠችው ሞሮኮ በዓለም ሃያ ሁለተኛ በአፍሪካ ደግሞ ሁለተኛ የሆነችበትን ደረጃ ማግኘት ችላለች።

ሌላኛዋ የዓለም ዋንጫ ተሳታፊና ያለፈው የአፍሪካ ዋንጫ አዘጋጅ አገር ካሜሩን በወሩ የፊፋ ደረጃ ከተንሸራተቱ የአፍሪካ አገራት አንዷ ብትሆንም ከዓለም ሰላሳ ስምንተኛ ከአፍሪካ አምስተኛ ደረጃ ላይ መቀመጥ ችላለች። የፊፋ አረብ ካፕ ንጉሷ አልጄሪያ በበኩሏ ደረጃዋን አሻሽላ ከአፍሪካ ሰባተኛ ከዓለም አርባ አንደኛ መሆን ችላለች። ናይጄሪያ፣ጋናና ደቡብ አፍሪካም ካለፈው ወር ደረጃቸውን ማሻሻል የቻሉ ቁንጮ የአፍሪካ ሀገራት ሆነዋል።

እንደ አጠቃላይ በዓለም ቀዳሚውን የደረጃ ሰንጠረዥ በመያዝ ደቡብ አሜሪካዊቷ የእግር ኳስ ሀገር ብራዚል ባለፈው የነበራትን ደረጃ ሳትለቅ መሪነቱን ይዛለች። ቤልጂየምም በተመሳሳይ የነበረችበትን የሁለተኛነት ደረጃ አስጠብቃ ቀጥላለች። ሌላኛዋ ደቡብ አሜሪካዊት አገር አርጀንቲናም ደረጃዋን አሻሽላ በሶስተኝነት ተቀምጣለች። በአውሮፓ ኔሽንስ ሊግ ደካማ አቋም በማሳየት ያልተጠበቁ ሽንፈቶችን ያስተናገደችው የዓለም ዋንጫ አሸናፊዋ ፈረንሳይ ከዓለም የነበራት ቀዳሚ ደረጃ ባለፉት ወራት እየተንሸራተተ ቢመጣም የአራተኛነት ደረጃን በመያዝ ከመሪዎቹ ብዙ አልራቀችም።

የሴቶቹን እግር ኳስ የአፍሪካ ደረጃ ናይጄሪያ በቀዳሚነት ከመቀመጥ ያገዳት የለም። ናይጄሪያን በመከተልም ካሜሩን፣ደቡብ አፍሪካ፣ጋና፣ኮትዲቯርና ቱኒዚያ ተከታዮቹን ደረጃዎች ይዘው ይገኛሉ። የዓለምን ደረጃ ደግሞ አሜሪካ በቀዳሚነት ትመራዋለች። ስዊድን፣ፈረንሳይ፣ኔዘርላንድስና ጀርመን ደግሞ በቅደም ተከተል እስከ አምስተኛ ያለውን ደረጃ ይዘው ይከተላሉ።


## Bid Announcement

**Adami tullu Jido Kombolcha woreda Finance office in 2014 budget year wants' to upgrade Dambi Naga small scale irrigation by "GCF' project by open bid.**

1) Oromia/East shoa Zone / Adami Tulluu worada has secured budget from **"GCF'** to cover eligible payment under the contract of the **construction of civil works, pipes and Fittings, Electromechanical (Pump and transformer) supply and Installation for upgrading of dambi Naga small scale irrigation project** Sources located in East Showa zone **AATJK Woreda Dodicha Kebele.** Bidding is open to all eligible bidders having a construction **license of GC-6 and above OR WWC 4 have renewed in 2014 E.C/2022 G.0 trading license.**

2) Registered at **Ministry Of Water, Irrigation and Energy or Ministry of Urban and Construction or Oromia Construction Authority, Oromia Water and energy Resources Development Bureau** and also.

3) Registered for **VAT** & Tax Identification number **(TIN)** and submit **valid tax Clearance certificate** from revenues authority.

4) More over, to be eligible for this bid, a bidder should be **non black listed and non track record of termination** of projects with the public body at regional or zonal offices.

5. East Showa Zone **ATJK** Werada Irrigation Development Office **(ESHAATKWIDO)**, acting as contracting authority for the project ,invites eligible bidders for the **construction of Civil Works, supply and installation of pipes and fittings as well as pump and transformer)** to the project site which general description for each Project is provided in the table below.

| No. | Description of the work | Dambi Nagay small scale irrigation project | |
|---|---|---|---|
| | | Un it | Quantity |
| 1 | **Supply, Transportation** and **laying** of pipes with fittings/Delivery pipe length | m | 1128 |
| 2 | **Supply, Transportation** and **installation** of EM (**Pump &transformer** with all accessories) | Is | 1 |
| | Main canal lined(90m) | No | 1 |
| 3 | Secondary canal lined (982m) | No | 1 |
| 4 | offtake | No | 8 |
| 5 | Turn out | No | 40 |
| 6 | Drop structure | No | 11 |
| 7 | Division box | No | 1 |
| 8 | Delivery pool | No | 1 |
| 9 | Pump house | No | 1 |
| 10 | Total lift head=28m | m | 28 |
| 11 | Discharge-103 Vs, suction pipe length-7m, and Required NPSH is 4.086m | | |

Bidding documents can be purchased from **Adami Tullu woreda Finance office, Batu town, (ETB) 500.00)**,E2tch Bidder can purchase one Bid document only.

6) Bid shall be valid for a period of ninety (90) days

7) **CPO (Certified payment order) 120,000.00 only from Bank .**

8) The bid should be submitted in four wax sealed documents properly marking the inner envelopes as **Technical "ORIGINAL"** and **One "COPY", Financial "ORIGINAL"** and One **"COPY"** each of them sealed 'separately and then the **ORIGINAL and COPY** of technical document sealed in **One Envelope** while the **ORIGINAL** and **COPY** of Financial document similarly sealed in another **One Envelope**: These **two wax sealed** envelopes are then sealed in o**ne wax sealed Main Envelope. The Bid Security (CPO) in its own envelope should be submitted in the Technical Original document.**

9) The bid shall be on air for **21 Working days calendar.**

10) From the date of this bid announcement , willing bidders can buy bidding document.

11) The bid should be submitted to Adami tullu Finance office, On 12/11/2014 before 8:00 PM Closed at local time E.C just on the 12/11/2014nd day, at 8:30 PM, if the 22/11/2014nd day will not be on the working day, it shall be on the next working days from bid announcement date and will be opened on the same day at 8:30 PM in the presence of bidders or legal representatives who choose to attend the bid.

12) Completion time for supply and installation of pipes and Fittings, pump and Transformer and construction of civil works of each project shall be four Months or 120 days calendar for all activities in the contract fr**om the date of signing the agreement**.

13) **A bidder who fails** to comply with conditions indicated under criteria number 1-11 above will not be regi**stered** for the Bid.

**14) The Office Reserves the right to reject all bids or partially.**

**(ATJKWIDO)**

**TELEPHONE NUMBER-0464412731/0464412447**

**Adami Tulu Jido Kombolcha Woreda Development Office**

# ከኢትዮጵያ የጤና መድህን አገልግሎት
## ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# በጤና ተቋማት ተጠያቂነትን በማስፈን ጥራት ወዳለው አገልግሎት የመሻገር ትልም

ዳንኤል ዘነበ

በሀገራችን የጤና መድህን ሥርዓት ባለፉት አስርት ዓመታት ተግባራዊ እየተደረገ እንደሆነ ይታወቃል። የጤና መድህን አገልግሎቱን በማስፋት በ887 ወረዳዎች መድረስ ችሏል። የጤና መድህን ሥርዓት ሀገራችን ሁሉን አቀፍ የጤና ሽፋን ለማረጋገጥ ለምታደርገው ጥረት ዓይነተኛ ማሳለጫ መንገድ ነው። የክፍያ አስተዳደር ደግሞ በጤና ተቋማት ተጠያቂነትን በማስፈን በዘርፍ ላይ ጥራት ያለው አገልግሎትን እንዲሰፍን በማድረግ የራሱን ሚና እየተጫወተ ይገኛል። እኛም በዛሬ እትማችን በአገልግሎቱ የጤና አገልግሎት ክፍያ አስተዳደር የተቋቋመበት ዓላማ፣ ከጤና ተቋማት ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሠራር እና ሌሎች ወቅታዊ ጉዳዮችን በተመለከተ በኢትዮጵያ ጤና መድህን አገልግሎት የጤና አገልግሎት ክፍያ አስተዳደር ዳይሬክተር ዶክተር ሀሊማ አባተን አነጋግረናቸዋል። እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡

የጤና አገልግሎት ክፍያ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ከተፈጠረ ሁለት ዓመት ያስቆጠረ ነው። የክፍያ አስተዳደሩ ዋነኛ ሥራው የጤና መድህን አባላት ውል በታሰረባቸው የጤና ተቋማት ያገኙት አገልግሎት ሂደት ተከታትሎ ለተቋማቱ ክፍያውን ይፈጽማል። ቀደም ሲል ጤና ተቋማቱ የሚከፍላቸው አካል የለም ነበር። በተለያዩ ምክንያቶች ገቢያቸውን በአግባቡ እየሰበሰቡ አልነበረም። አሁን ግን ኃላፊነቱን ወስዶ የሚሠራ እና የሚከፍል አካል አለ። ስለዚህ ጤና ተቋማቱ በአግባቡ ገቢያቸውን እንዲሰበስቡ ማድረግ የተቻለ



ዶክተር ሀሊማ አባተ

ሲሆን፤ ይህም ተቋማቱ ለሚያደርጉት የጥራት ማሻሻያ ፕሮግራሞች እንዳይቸገሩ ያደርጋቸዋል።

በተጨማሪም አንዳንድ የህክምና እክሎች ወረዳው ውል ባሰረባቸው የጤና ተቋማት ላይፈቱ ይችላሉ። ስለዚህ ቀጣይነት ላለው አገልግሎት አልያም ከፍ ወዳለ የጤና ተቋም መሄድ ሊያስፈልግ ይችላል። በዚህ ወቅት ወረዳዎቹ አገልግሎቱን ተደራሽ የሚያደርጉበትና ክፍያ የሚፈጽሙት አባላቱ የህክምና አገልግሎት ያገኙባቸው ጤና ተቋማት በመሄድ ነበር ። ለምሳሌ አንድ የጤና መድህን አገልግሎት አባል ከባሌ ጊንር በመምጣት አዲስ አበባ ህክምናውን ቢከታተል፤ በዚያ ወረዳ የሚገኘው የጤና መድህን እዚህ ድረስ መጥቶ ወጪውን የሚከፍልበት መንገድ ነበር።

በዚህ መንገድ መጓዙ በወረዳዎቹ ላይ አስተዳደራዊ ጫና እና ወጪ ይፈጥራል። የጤና አገልግሎት ክፍያ አስተዳደሩ ይህ ዓይነቱን አሠራር ለማስቀረት ከወረዳ ጤና ቢሮዎች ጋር በመነጋገር የመግባቢያ ሰነድ በመፈራረም ኃላፊነት ወሰደ። በዚህም ከሁለት ክልሎችና ከአንድ ከተማ አስተዳደር ማለትም ከአዲስ አበባ አስተዳደር ፣ ከሱማሌ እና አፋር ክልል ውጪ ከሁሉም ጋር የውል ስምምነት ተፈርሟል። ከእነዚህ ወረዳዎች የሚመጡ ታካሚዎች በስምምነቱ መሠረት የህክምና አገልግሎቱን እንዲያገኙ ይደረጋል። ይህም ጠንካራ የሆነ የህሙማን ቅብብሎሽ ሂደት እንዲፈጠር አድርጓል። ለዚህ ደግሞ ከአማኑኤል፣ ቅዱስ ጳውሎስ፣ ቅዱስ ጴጥሮስ፣ ጥቁር አንበሳ፣ የካቲት 12፣ ዳግማዊ ምኒልክ፣ አለርት ሆስፒታል ጋር ስምምነት በመፈራረም እየተሠራ ይገኛል።

ከሆስፒታሎች ጋር ስምምነት ተገብቶ መሠራቱ ጠንካራ የሆነ የህሙማን ቅብብሎሽ ሂደት ፈጥሯል። ለምሳሌ የውል ስምምነቱን በፈረሙት ወረዳዎች የሚገኙ ጤና ተቋማት የጤና መድህን አባል የሆነ አንድ ታካሚ ጉዳይ ከእነሱ አቅም በላይ ሊሆን ይችላል። ይህ ሲሆን ጤና ተቋማቱ ከአቅማቸው በላይ መሆኑን በመግለጽ ለታካሚው ሪፈር ይጽፋሉ። የተላከለት ሆስፒታል ህሙማኑን በፍጥነት ወደ ህክምና አገልግሎት እንዲገባ ያደርጉታል። ታካሚው የህክምና አገልግሎት ያለምንም ክፍያ ያገኛል። በዚህ መልኩ የህክምና ሂደት ከተጠናቀቀ በኋላ፤ በጤና መድህን አገልግሎት ለክፍያ አስተዳደር ክፍል ተቋሙ የአገልግሎትና ሌሎች ወጪዎችን አስልቶ የክፍያ ጥያቄ ያቀርባል። የክፍያ አስተዳደር ክፍሉም ሂደቱን አጣርተን ክፍያ እንፈጽማለን። ይህ መሆኑ በጤና መድህን አገልግሎት ውስጥ የክፍያ አስተዳደር ክፍል መፈጠሩ ቀደም ሲል በጤና አገልግሎት ክፍያ ላይ የሚታዩ በርካታ ችግሮች ቀርፏል።

በዋነኝነት ግን አሠራሩ መዘርጋቱ በሁለት መንገድ ችግሮችን ቀርፏል። የመጀመሪያው የአስተዳደር ወጪ ጫና እንዲቀንስ አድርጓል። ወረዳዎች የአስተዳደር ወጪ አላቸው። ለምሳሌ አንድ ሰው ከባሌ ጊኒር ሪፈር ቢባል ወረዳው እዚህ አዲስ አበባ ድረስ መጥቶ ክፍያ ይከፍላል። ይህ መሆኑ የአስተዳደራዊ ወጪ ጫና የሚፈጥር ሲሆን ፤ ቀደም ሲል የነበረውን አሠራር መቀየሩ ችግሩን አስቀርቶታል። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ህሙማኑን በቅርበት መከታተል አስችሎናል። ታካሚ ቅሬታ ቢያቀርብ ቅሬታውን በፍጥነት ምላሽ መስጠት ያስችላል። ለምሳሌ አገልግሎቱ ከተጀመረ ሁለት ዓመት የሆነው ሲሆን፤ በእነዚህ ዓመታት የተለያዩ ቅሬታዎችና ችግሮች ነበሩ። በዋነኝነት ይነሳ የነበረው ደግሞ የመድኃኒት በሆስፒታሎች አለመገኘት ነው። ለዚህም መፍትሄ ከነሐሴ 07 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ከከነማ ጋር ውል ተፈራረምን ። ስለዚህ ታካሚው መድኃኒት ቢታዘዝለትና በሆስፒታል መድኃኒቱ ባይኖር በአቅራቢያው ከሚገኝ ከነማ መድኃኒት የጤና መድህን አባልነት መታወቂያ ካርዱ በነፃ ይወስዳል። በዚህ መልኩ ታካሚው የተሟላ የህክምና አገልግሎት ያገኛል። በአጠቃላይ የጤና መድህን ሥርዓት ሀገራችን ሁሉን አቀፍ የጤና ሽፋን ለማረጋገጥ ለምታደርገው ጥረት ዓይነተኛ ማሳለጫ መንገድ ነው ። የክፍያ አስተዳደር ደግሞ በጤና ተቋማት ተጠያቂነትን በማስፈን በዘርፍ ላይ ጥራት ያለው አገልግሎትን እንዲሰፍን በማድረግ የራሱን ሚና እየተጫወተ ይገኛል።

# ከኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም
## ጋር በመተባበር በየሣምንቱ የሚታተም

# አስተዳደራዊ በደሎችን የመከላከል ተልዕኮ በጋምቤላ

ራስወርቅ ሙሉጌታ

በኢትዮጵያ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ብሎም የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበራቸውን መከታተል ይቻል ዘንድ መንግሥት የተለያዩ የዴሞክራሲ ተቋማትን መስርቷል። ከነዚህ መካከል አንዱ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ካሉት ስምንት ቅርንጫፎች የጋምቤላ ክልል ቅርንጫፍ አንዱ ሲሆን ለዛሬው ዝግጅታችን የቅርንጫፉ እንባ ጠባቂ የሆኑትን አቶ ጀምስ ዴንን አነጋግረን በክልሉ የተሠሩ ሥራዎችን እንደሚከተለው ይዘን ቀርበናል።

በአንድ ሀገር ውስጥ ጠንካራ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሥርዓት ለመፍጠር ከሚያስፈልጉ ቀዳሚ ነገሮች መካከል መልካም አስተዳደር አንዱ ነው። በመንግሥትና በሕዝብ መካከል መተማመንና መተጋገዝን መሠረት ያደረገ ግንኙነት ለመፍጠር የሚቻለው የመንግሥት ሥርዓት አስተማማኝ የመልካም አስተዳደር ሥርዓት ሲኖረው ነው። በአሁኑ ወቅት መንግሥት የልማትና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን ለመመለስ በስፋት በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል። የኢትዮጵያ ሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም የጋምቤላ ቅርንጫፍም ከተቋቋመበት ከ2006 ኢ.ም ጀምሮ ከሕዝብና ከመንግሥት የተጣለበትን ኃላፊነት ግምት ውስጥ ባስገባ ሁኔታ በተለይም የመረጃ ሕግን በማስተግበር ረገድ በርካታ አበረታች ተግባራትን አከናውኗል።

ጽሕፈት ቤቱ በክልሉ ሥራውን እንደጀመረ ቀዳሚ ሥራው ያደረገው ለሚመለከታቸው የመንግሥት ሥራ አስፈጻሚ አካላት ከክልልና ዞን አመራሮች ጀምሮ ወረዳ ድረስ የግንዛቤ ማስጨበጫ በመስጠት ነው። የግንዛቤ ማስጨበጫው አጠቃለይ መረጃን ለኅብረተሰቡ በምን ዓይነት መልኩ ተደራሽ ማድረግ እንዳለባቸውና የሕዝብን መረጃ የማግኘት መብት እንዲሁም የተቋሙንም ኃላፊነትና ተግባር ያካተተ ነበር። በተመሳሳይ የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም ለኅብረተሰቡም የግንዛቤ ማስጨበጫዎች ተሰጥተዋል። ከዚህ ጊዜ አንስቶም ኅብረተሰቡ አስተዳደራዊ

**በአንድ ሀገር ውስጥ ጠንካራ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሥርዓት ለመፍጠር ከሚያስፈልጉ ቀዳሚ ነገሮች መካከል መልካም አስተዳደር አንዱ ነው። በመንግሥትና በሕዝብ መካከል መተማመንና መተጋገዝን መሠረት ያደረገ ግንኙነት ለመፍጠር የሚቻለው የመንግሥት ሥርዓት አስተማማኝ የመልካም አስተዳደር ሲኖረው ነው።**

በደል ተፈጽሞብኛል ብሎ ሲያስብ ዝም ብሎ ከመቀመጥ ይልቅ ወደ ኢትዮጵያ ሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም በመምጣት ቅሬታና አቤቱታ ማቅረብ ጀምሯል። ተቋሙም ባሉት ሦስት ባለሙያዎች የመጣውን አቤቱታ በዝርዝር በማየት ጉዳዩ በተቋሙ ሊታይ የሚችል መሆኑንና አለመሆኑን ይወስናል። የመጣው ቅሬታ በተቋሙ ስር ሆኖ መታየት የሚችል ከሆነ አስፈላጊውን መረጃ በመሰብሰብና የሚመለከታቸውን አካላት በማነጋገር ተገቢውን ምርመራ ያከናውናል። ከምርመራው ውጤት በመነሳትም በትክክል አስተዳደራዊ በደል ተፈጽሟል ተብሎ ከታመነ ቅሬታ ወደቀረበበት መስሪያ ቤት በመሄድ እንዲያስተካክል ምክረ ሀሳብ ይሰጣል። የተሰጠውን ምክረ ሀሳብ ለመቀበልና ለመተግበር ፈቃደኛ ያልሆኑ ተቋማት ካሉ ለክልሉ ምክር ቤት በተለይ ለአፈ ጉባኤው ጉዳዩ ቀርቦ እንዲታይ ይደረጋል። በዚህ ዓይነት ከቀረቡትና ውሳኔ ከተሰጣቸው መካከል አስተማሪ ይሆናሉ ያሏቸውን አቶ ጀምስ እንደሚከተለው ነግረውናል።

ጋምቤላ ክልል አስራ ሦስት ወረዳዎች አሉት ባለፈው አመት ከአኮቦ ወረዳ በመምህራኖች የቀረበ ቅሬታ ነበር። ቅሬታውን ያቀረቡት 250 መምህራኖች ሲሆኑ በሀገር አቀፍ ደረጃ የደመወዝ ማስተካከያ ሲደረግ ቅሬታ አቅራቢዎቹ ውዝፍ ደመወዛቸው ሳይከፈላቸው ቀርቶ ነበር። ቅሬታቸውን ለያኮቦ ወረዳ ቢያቀርቡም አጥጋቢ ምላሽ ሳያገኙ ይቀራሉ። ወደ እንባ ጠባቂ ተቋም መጥተው ጉዳዩን በማስረዳታቸው ተቋሙ የወረዳውን ተወካዮች ጠርቶ ሲያነጋግር ጉዳዩን እንደሚያስተካክል ተናግረው ይመለሳሉ። ነገር ግን የወረዳው ኃላፊዎች ከተመለሱ በኋላ ቃላቸውን በማጠፍ በ250 መምህራን የተወከሉትን ሰባት መምህራን እንዲታሠሩ ያደርጋሉ። ተቋሙም ጉዳዩን ከክልሉ ምክር ቤት ጋር በመሆን ተከታትሎ ከአራት ወራት ውጣ ውረድ በኋላ እስረኞቹም እንዲፈቱ መምህራኑም ውዝፍ ክፍያቸውን እንዲቀበሉ ማድረግ ችሏል።

በተመሳሳይ በላሬ ወረዳ ያሉ አራት መቶ አንድ መምህራን የደመወዝ ጭማሪ ባለማግኘታቸው ያቀረቡትን አቤቱታ ተከትሎ የማጣራት ሥራ በጽሕፈት ቤቱ ተከናውኗል። በሂደቱም ችግሩን እዚያው በንግግር ለመፍታት ብዙ ቢሞከርም ፋይናንስ ቢሮና ወረዳው ብሎም ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ አንዱ በአንዱ እያሳበበ ሊፈታ ባለመቻሉ ለክልሉ ምክር ቤት እንዲቀርብ ተደርጓል። የክልሉ ምክር ቤት አፈጉባኤም ጉዳዩን በመመልከትና አስፈላጊውን ውሳኔ በማስተላለፍ በፍጥነት ያልተከፈለው ደመወዝ እንዲከፈል ማድረግ ተችሏል።

በግለሰብ ደረጃ የደረሱ አስተዳደራዊ በደሎችን በተመለከተ ከተሠሩት ብዙ ሥራዎች መካከልም የሚከተለው አንዱ ማሳያ ነው። የጋምቤላ ትምህርት ቢሮ ለወረዳ ትምህርት ጽሕፈት ቤቶች የትምህርት ዕድል በመስጠት ከአስራ ሦስቱም ወረዳዎች አንድ አንድ ሰው እንዲላክለት ይጠይቃል። ወረዳዎች በታዘዙት መሠረት ትምህርቱን መከታተል የሚችል ሰው መልምለው ቢልኩም የትምህርት ቢሮው ኃላፊ ግን አንዲትን መምህር እርስዎ የምንፈልገው ሰው አይደሉም በማለት አልቀበልም ይላል። ምክንያቱ ደግሞ የሚመለመለው ሰው የክልሉ ተወላጅ መሆን አለበት የሚል ነበር። እንዳይማሩ የተከለከሉት መምህርት አስካለም ጉዳዩን ይዘው ወደ እንባ ጠባቂ ያመራሉ። የጽሕፈት ቤቱ ባለሙያዎችም ወደ ትምህርት ቢሮው በመሄድ መጀመሪያ የተላከውን ደብዳቤ ሲያዩ አቤቱታ አቅራቢዋ ባቀረቡት መሠረት መስፈርቱ መምህርነት ብቻ እንጂ ተወላጅ መሆን አልያም ብሔር የማይጠይቅ ሆኖ ያገኙታል። በመሆኑም ጉዳዩን በመከታተል መምህርቷ ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ለማድረግ ችለዋል።

በሌላ በኩል በግምገማ ሰበብ ከ2004 ኢ.ም ጀምሮ ከከንቲባ ቢሮ አላግባብ የተባረረ ሠራተኛም ነበር። ሠራተኛው ለዘጠኝ አመት ያህል ብዙ ውጣ ውረዶችን ካሳለፈ በኋላ ጉዳዩን ለጋምቤላ ክልል እንባ ጠባቂ ጽሕፈት ቤት በማቅረቡ ጉዳዩ እንደአዲስ መታየት ይጀምራል። ነገር ግን በቦታው ላይ የነበሩት አዲስ የመጡ ኃላፊዎች ግን የተወሰነው ውሳኔ ስህተት መሆኑን ቢያምኑም በእነሱ የአስተዳደር ዘመን የተፈጸመ ባለመሆኑ ለማስተካከል ፈቃደኛ ሳይሆኑ ይቀራሉ። ነገር ግን ጉዳዩ እንደተቋም መታየት ስለነበረበት በጽሕፈት ቤቱ በኩል ይህንን በማስረዳት ከአስር አመት በኋላ ሠራተኛው ወደሥራ ገበታው እንዲመለስ ማድረግ ተችሏል። ከላይ የተጠቀሱትና በተመሳሳይ ቅሬታ የተፈታላቸው ዜጎች ለተቋሙ በአካል በስልክና በደብዳቤ በርከታ ምስጋናዎችን አቅርበዋል።

ይህም ሆኖ ሁሉም ሥራዎች ሲሠሩ ለጽሕፈት ቤቱ መንገዶች ሁሉ አልጋ በአልጋ አልነበሩም። የመጀመሪያው ችግር በጽሕፈት ቤቱ የሚሰጡ የመፍትሄ ሃሳቦችን ተቀብለው የማይተገበሩ አንዳንድ የመንግሥት ሥራ አስፈጻሚዎች መኖራቸው ነው። ሁለተኛው ደግሞ ክልሉ ሰፊ ከመሆኑ አንጻር እስከ ደቡብ ሱዳን ድንበር ድረስ እየሄዱ ጉዳዮችን በአካል በመገኘት ለመከታተል በአካባቢው የጸጥታ ችግር ከመኖሩም አንጻር የመጓጓዣና በአንዳንድ አካባቢዎች የባለሙያ ችግርም ይጠቀሳል ሲሉ አቶ ጀምስ ተናግረዋል።